# ለክርስቶስ ተሰቃየሁ

**RICHARD WURMBRAND**



# ለክርስቶስ ተሰቃየሁ ።

ደራሲውና ባለታሪኩ
ሪቻርድ ኡምብራንድ

ተርጓሚው
ተስፋዬ መስፍን


፲፱፻፹፫ ዓ. ም.
አዲስ አበባ ።

Love In Action Society
V-31, Green Park, New Delhi-110016.

**"Tortured for Christ"**
**(Amharic-Ethiopian)**
**by**
**Rev. Richard Wurmbrand**

1st Edition 1973 1000 Copies
2nd Edition 1991 5000 Copies

«እንደገና የማሳተም መብቱ የተርጓሚው ነው ።»

Printed and Published by Dr. P.P. Job for The Love In Action Society at Sabina Printing Press, 387/24, Faridabad, Haryana, India.

# ካለማመን ወደ ማመን ።

የተወለድኩት ሃይማኖትን ከሚቃወሙ ቤተሰቦች ነበር ፤ ስለዚህም አንዳችም ስለ ሃይማኖት ወይም ስለ ሃይማኖታዊ ሥርዓት የማውቀው አልነበረኝም ። እን ዲያውም በ፲፩ ዓመቴ እግዚአብሔር የለም የምል (ኤቲስት) ነበርኩ ፤ ገና የልጅነት ጊዜዬን ሳልጨርስ እናት አባቴ በሞት ስለተለዩኝ ራሴን ለመርዳት መጣ ጣር አስፈለገኝ ። ማንኛውም የሙት ልጅ እንደሚሆ ነው ሁሉ ብዙ ተቸገርሁ ። በአንደኛው የዓለም ጦር ነት ምንም እንኳ ልጅ ብሆንም ጦርነቱ ያመጣውን ጠንቅ መካፈል ግዴታ ሆነብኝ ።

ዛሬ የኮሚኒስት ድጋፊ ወጣቶች እንደሆኑት ሁሉ እግዚአብሔር ወይም መንፈሳዊ ዓለም እንደሌለ ይመስለኝ ነበርኩ ። እግዚአብሔር ያለመኖሩን የሚያ ስረዱና በእግዚአብሔር ማመን ከፍርሃት የመነጨ እንደሆነ የሚያስረዱ በተለያዩ ደራሲያን የተጻፉ አያሌ መጻሕፍትን አነብቤአለሁ ። ይህም በጠቅላላው «ሃይማኖታውያን ሁሉ በከንቱና በማይረባ ተረት በመሙላት አእምሮን የፍርሃት ተገዥ ያደርጉታል» የሚል አስተሳሰብን ስለፈጠረብኝ በሃይማኖትና በሃይ ማኖታውያን ላይ ያለኝን ጥላቻ አበረታው ። በኋላ ግን እያደር እንደተረዳሁት እኔ ራሴ እግዚአብሔር እንዳ ለና በእርሱ እንደተመረጡት እንደሱ ልጆች የምሆንበት ሃሣብ በጭላንጭል ታየኝ ። እንዴትና በምን እንደሆነ ግን አላወቅሁም ። አስቀድሞ እንዳልኩ እግዚአብሔር የለም ባይ ነበርኩ ፤ ሃይማኖታውያንንም በጣም እቃወ ማለሁ ። ቢሆንም የማልረዳው ኃይል ወደ ቤተ ክርስ ቲያን እንድገባ ይገፋፋኝ ነበር ፤ እንኳን ውስጡ ጉብቼ

እንደመሃይማን ከምገምታቸው አማኒያን ጋር መደባለቅ ቀርቶ በበሩ ማለፍን እንኳ አያስወድደኝም። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እንደሚደረግ አላውቅም ፤ ስብከቶችን ግን ሰምቼአለሁ ፤ ቢሆንም የሰማኋቸው ስብከቶች ለኔ ፍጹም ተረት ነበሩ ፤ እግዚአብሔር እንደሌለ እርግጠኛ የሆንኩ ከሚመስለኝ የተነሳ «ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባሃል» የሚለውን ሃሣብ አላገጥኩበት ፤ ቢሆንም በውስጤ የማያቋርጥ ጭንቀት ነበረብኝ ፤ ነፍሴ የምትታመንበትን አፍቃሪ ወዳጅ ለማግኘት በውስጤ ትቃትት ነበር ። አንድ እርህሩህ የሆነ ወዳጅ በዚህ ሰፊ ዓለም እምብርት ውስጥ እንዲኖረኝ ተመኘሁ ። እግዚአብሔር የለም በሚለው ፍልስፍና አእምሮዬ ከመመረዙ የተነሳ ተጨነቅሁ ፤ ይህም መጥፎ ሃሳብ እንዲፋቅልኝና እንደሌሎች በእግዚአብሔር አማኝ እንድሆን ወደድኩ ። እንደተማርኩትና እንደማምንበት እግዚአብሔር የለም ፤ ታዲያ አፍቃሪና አዛኝ የሆነ አምላክ ለእኔም የሚያስብልኝ ወዳጅ ከየት ሊመጣ ይችላል? በጣም ተጨነቅሁ ። ከዚህ ከንቱ ትምህርትም የሚያላቅቀኝ ኃይል ፈለግሁ ።

አንድ ቀን ስፈራ ስቸር ወደ አንዲት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ገባሁ በዚያ ሰዎች በማርያም ሐውልት ስር ተንበርክከው «አ ፤ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ሆይ ከልጅሽ ጸጋን ለምኝልን» በማለት በኅብረት ይጸልዩ ነበር ፤ ምናልባት አንድ ለውጥ ይስጥ እንደሆን በማለት ጸሎቱን በጥንቃቄ እየተከተልኩ መድገም ጀመርኩ ፤ ቢሆንም ጸሎቴ መልስ አላገኘም ። በጣም አዘንኩ ። አንድ ቀን እንዲህ ብዬ ጸለይኩ ፤ «እግዚአብሔር ሆይ አንተ እንደሌለህ እርግጠኛ እንደሆንኩ ይመስለኛል ። ምናልባት ብትኖርም እንኳ ራስህን መግለጽ ያንተ ፈንታ ሲሆን ማመን

ደግሞ የኔ ፋንታ ይሆናል ። እባክህን ጌታ ሆይ ራስህን ግለጽልኝ ። አልኩት ። እግዚአብሔር የለም የምል ከሐዲ ነበርኩ ፤ ይህም ጭንቀቴን አበረታው እንጂ ለሚቅበዘበዘው ልቤ እረፍትን ሊሰጠው አልቻለም ።

እኔ ይህን በመሰለ ጭንቀት በነበርኩበት ጊዜ በሩማንያ ውስጥ በአንድ ተራራማ ቀበሌ ይኖር የነበረ አንድ አናጢና በትውልዱ አይሁዳዊ የሆነ በጣም ያረጀ ሽማግሌ እንዲህ እያለ ይጸልይ ነበር ፤ ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ በምድር አገለገልኩህ በምድር እንዳገለገልኩህ እንዲሁ ዋጋዬን በምድር ስጠኝ ያም እንድትሰጠኝ የምፈልገው ዋጋ አንድ በክርስቶስ የማያምን አይሁዳዊ እርሱን ወደማመን እንዳመጣ ነው ። ጌታ ሆይ! ይህን ለማድረግ አይሁዳዊያን ወደሚኖሩበት ለመሄድ እንደማልችል አንተ ታውቃለህ ፣ ዓይኔ ፈዞአል ፣ ጉልበቴ ደንግዞአል ፤ ስለዚህ ከየትም ይሁን ከየት ከመሞቴ በፊት እዚሁ ቤቴ (መንደሬ) ድረስ አንድ አይሁዳዊ ላክልኝ ።»

በሩማንያ ውስጥ ፲፪ሺ መንደሮች ነበሩ ፤ ታዲያ አንድ ቀን ያለምክንያትና ዓላማ ይህ አይሁዳዊ ወደሚኖርበት ተራራማ ቀበሌ ሄድሁ (እኔ ራሴ አይሁዳዊ ነኝ) ያም ሽማግሌ እኔን እንዳየ በቀጥታ የእኔ ወደ ርሱ መሄድ «አይሁዳዊ ሰው ላክልኝ» እያለ ይጸልየው ለነበረው ጸሎት መልስ እንደሆነ በማመን ወደቤቱ እንድገባ ጋበዘኝ ። ስለክርስቶስም መሰከረልኝ ። ከዚያ በኋላ ወደ ቤቴ ለመሄድ ስነሳ አንድ ያረጀ መጽሐፍ ቅዱስ አውጥቶ ሰጠኝ ። እርግጥ መጽሐፍ ቅዱስን ከዚያ በፊት አንብቤ ነበር ፣ ይህ ሽማግሌ የሰጠኝ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሰውን የልብ ደንዳናነት የሚወጋበት ፣ ስለ ኃጢአት የሚወቅስበት ልዩ ሃይል ነበ

ረው ፣ እያንዳንዱ ቀለም በነፍሳት ፍቅርና በጸሎታችን ኃይል መንፈስን የሚያነቃቃ እሳት ነበረባት ። በዚያ መጽሐፍ የተገለጸውን የዓለም አዳኝ የሆነውን የክር ስቶስን ሕይወት በኃጢአት ከረከሰው ከእኔ ሕይወት ጋር ሳስተያየው በርግጥ ክርስቶስ ከሰው የተለየ እን ደሆነ ተረዳሁ ፤ በውስጡ የተጠቀሱትን ሰዎችን ስለ ኃጢአት የሚወቅሱትን የሚያስጠነቅቁትን ባነበብኩ ጊዜ በመጽሐፉ ላይ ተደፍቼ አነባ (አለቅስ) ነበር ፣ ፍጹምና እውነተኛ ፍቅርን በክርስቶስ ሕይወት ለመ ጀመሪያ ጊዜ አገኘሁ! ሕይወቴን ለጌታ ኢየሱስ ክር ስቶስ አሳልፌ ሰጠሁ ፤ እግዚአብሔር የለም በማለት ያሳለፍኩዋቸው እነዚያ ያለማወቅ ዘመናት አስቆጩኝ ፣ እኔ ክርስቲያን እንደሆንኩ ሚስቴም ደግሞ በኔ ስብከት አማካኝነት ክርስቶስ እውነተኛ መሢሕ እን ደሆነ አመነች ፣ ብዙ ነፍሳትንም ወደ ክርስቶስ አመ ጣች ፣ ስለዚህም አዲስ የሉተራውያን ክርስቲያናዊ ጉባዔ ተመሰረተ ።

ይህ በሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አምባ ገነን የሆኑት የናዚ ተከታዮች በታላቅ ጭከና አይሁዳውያ ንን እንዲሁም ፕሮቴስታንቶችና (ክርስቲያኖች) ለሃ ሳባቸው ተቃራኒ የሆኑትን ሁሉ ያሳድዱ ፣ ያሥሩ ፣ ይገድሉ ጀመር ፣ በዚህ ጊዜ ገና ወጣት ለነበረችው ቤተክርስቲያን መሥራችና መሪዋ ነበርኩ ፣ በምእመ ናኑ ሁሉ ላይ ሃላፊነት ነበረብኝ ፣ ምንም እንኳ ናዚ ስቶች እምነትን ማስፋፋታችንን ቢቃወሙም እኛ ግን በታማኝነት ነፍሳት ለክርስቶስ ውሳኔ እንዲያደ ርጉ እናስተምር ነበር ፣ ትእዛዛቸው እንዳልተከበረ ባዩ ጊዜ የናዚስቶች ቁጣ በላያችን ላይ ነደደ በታላላቅ መሪዎች ፊት ቀርበን ቅጣትና ማስጠንቀቂያ ተሰጠን

ወህኒ ገባን ፣ ልዩ ልዩ ሥቃይን ተቀበልን ፣ ግርፋትም ተፈረደብን ፣ እኛ ግን የአምላካችንን ሥራ በታማኝ ነት እንሠራ ነበር! በናዚስቶች ስለ እምነቴ ተሰቃይ ቻለሁ ፣ በኮሚኒስቶችም እንደዚሁ ደርሶብኛል ፣ ታዲያ ናዚስቶችንና ኮሚኒስቶችን ማለት በሁለቱም የደረሰ ብኝን ፍዳ ሳወዳድረው የእኩለ ሌሊትን ድቅድቅ ጨለ ማነት ሳያይ ጸሐይ ከጠለቀች በኋላ ለዓይን ያዝ የሚ ያደርገውን ድንግዝግዝ እንደሚያማርር ሰው እንደነ በርኩ ይገባኛል ፣ አባባሌን በይበልጥ ግልጽ ማድረግ ቢያስፈልግ በኮሚኒስቶች ልንቀለበው ያለንን ታላቅ መከራ ሳናይ ናዚስቶች ያደረሱብንን ችግር የችግር መጨረሻ አድርገን ገምተን ነበር ፣ አሁን ግን ሁለቱ ንም ካየን በኋላ የኮሚኒስቶች እንደሚብስ ለመረዳት ቻልን ። ስጋታችን በእምነታችን ብቻ ሳይሆን ሚስ ቴና እኔ አይሁዳውያን በመሆናችንም ጭምር ነበር፣ ልጄ ሚሐይ አይሁዳዊ መሆኑ ታውቆበት ታድኖ እን ዳይገደል ስሙን ቀየርንለት ።

ናዚስቶች ምንም እንኳ ያደረሱብን መከራ ታላቅ ቢሆንም አንድ ታላቅ ትምህርት አስተምረውን አል ፈዋል ። ይኸውም በሥጋ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጭን ቀት መንፈሳችን ሁሉን በሚችል አምላክ ሃይል ከበረታች መከራንና ጭንቀትን ለመቃወም የሚያስች ለውን ሃልይ እንደምናገኝ ነው ፣ ይህንንም ለመጀመሪያ የተረዳነው ያኔ ነው ። አዎን የእግዚአብሔር ኃይል ስለእምነታችን መከራን ለመቀበል እንድንችል አበረ ታን ፣ ያስተማሩን ይህን ብቻ አልነበረም ወንጌልን መስበክ ስለተከለከለ በሚስጥር የምናስፋፋበትን መን ገድ ማወቅ አስፈለገን ። ይህም ከነሱ ይልቅ የወንጌል

ተቃዋሚዎች በሆኑት መካከል ሃይማኖትን በሚስ ጥር የምናስፋፋበት ጥበብ ሰጠን ።

## አገልግሎቴ በሩሲያውያን መካከል

እኔ ኢቲስት ማለት አምላክ የለሽ በነበርኩ ጊዜ የነበረኝ ጭንቀት ምን ያህል ታላቅ እንደነበር ስለ ማውቅ ጭንቀቴን ሁሉ ያጠፋልኝን ክርስቶስን ካመ ንኩበት ከመጀመሪያይቱ ቀን ጀምሮ ይህን እኔ ያገ ኘሁትን አዳኝ እንዲያገኙ እግዚአብሔር የለም በሚል አጉል ፍልስፍና በተመረዙ በኮሚኒስቶች መካከል ለመሥራት አቀድሁ ፣ አንድ ቀን ምኞቴ የሚፈጸም በት ቀን መጣ ፣ ብዙ ሩሲያውያን የሆኑ የጦር እስረ ኞች ወደ ሩማንያ መጡ ፣ ስለዚህ ክርስቶስን በመካከ ላቸው ለመስበክ መልካም አጋጣሚ ነበር ፣ አንድ ሩሲ ያዊ ከሆነ ኢንጂኔር ጋር ስለ ክርስቶስ ከመነጋገሬ በፊት በእግዚአብሔር ያምን እንደሆነ ጠየቅሁት ። ምንም መልስ ሳይሰጠኝ ቀና ብሎ ካየኝ በኋላ «እን ዲህ ያለ ትእዛዝ ከአለቆቼ አልተቀበልኩም እንጂ በእግዚአብሔር ለማመን ደስተኛ ነበርኩ» በጣም አሳ ዘነኝ ። እምባ ከአይኖቼ ጐረፉ ። ያ እፊቴ የቆመው ትሁት ሰው አእምሮው በከንቱ ፍልስፍና ተሞል ቷል ። ሙሉ በሙሉ በአለቆቹ እንዲተማመን ከመደ ረጉ የተነሳ በራሱ አይተማመንም ። ምንም መልካምና አስፈላጊ ቢሆንም አለቆቹ የሚቃወሙት ከሆነ አያ ደርገውም ፣ አይፈልገውም ። ይህ ሰው ታላቅ አምላክ የሰው ልጆች ሁሉ እንዲድኑበት ያዘጋጀውን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራውን መንገድ (ክርስቶስን) አያውቅም ። ይህም ሃዘኔን አባሰው ።

ኮሚኒዝም በእምነት ላይ ያመጣውን ጠንቅ ካስተዋልኩ በኋላ አገልግሎቴን በነዚህ እግዚአብ ሔር የለም በሚሉ ወታደሮች መካከል ለማድረግ ወሰንኩ ፤ አገልግሎቴንም ሕያው አምላክ ማለት የሰማ ይና የምድር ፈጣሪ እንዳለና ያም አምላክ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑበት አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመ ስቀል እንዲሰቀል የዓለሙን ኃጢአት እንዲያስተሰ ርይ እንዳደረገ ማስተማር ነው ።

በነሐሴ ፳፫/፲፱፻፵፬ ዓ. ም. ከ፩ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የሩሲያን ወታደሮች ወደ ሩማንያ መጡ ፤ ይህ ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኮሚኒስቶች በሩማንያ ሃይል ማግኘት ጀመሩ! ናዚስቶችን አማረን ነበር ፡ ያመጣ ውን ጠንቅ ግን ከሩሲያውያን ጋር ስናወዳድረው በጣም ቀላል ነበር ። በዚህ ጊዜ ፲፰ ሚሊዮን ሕዝብ ካለበት መንደር ፲ ሚሊዮን ሕዝብ በግዴታ የኮሚ ኒስቶች ደጋፊ ሆነ ። ቪሻስንኪ የተባለው የሶቪየት የውጭ ጉዳይ ጸሐፊ ወደተወደደው የሩማንያ ንጉሥ ሚካኤል ቀዳማዊ መጥቶ ኮሚኒስቶች በሃገሪቱ አስ ተዳደር ውስጥ እጃቸውን እንዲያገቡ ጠይቀው ይበ ልጡ ሕዝብ ደጋፊያቸው ስለሆነ ምንም ማድረግ አል ተቻለም ፤ ሕዝቡን በመበደልና በሌላም ልዩ ልዩ ጥበብ ኮሚኒስቶች ሃይላቸውን ያስፋፉ ነበር ።

ይህም ሲሆን ብሪቲሾችና አሜሪካኖች ኃይል ከሰጡዋቸው ወገኖች ነበሩ ፡ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የሚጠይቁት በእጃቸው ስለሠሩት ኃጢአት ብቻ ሳይሆን በእጅ አዙር ሌላውንም ስለሚያሠሩት ኃጢአትም ጭምር ነው ። እነዚህ ክርስቲያን መንግሥ ታት ክርስቲያን ወንድሞቻቸው ኮሚኒዝም በላያ

ቸው ላይ ኃይል እንዲያገኝ እንደተደረገባቸው ሁሉ ዛሬ በኮሚኒዝም ተጽእኖ ሥር ላለው የሩማንያ ሕዝብ ወደ ክርስቶስና ወደ ወንጌሉም ብርሃን እንዲመጡ መር ዳት ይኖርባቸዋል ።

## የፍቅርና የማታለል ንግግር

ኮሚኒስቶች በሩማንያ ኃይል ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ቤተክርስቲያን መስፋፋትና ማደግ ዓላማ እንዳ ላቸው አስመስለው በማወጅ የሕዝቡን ልብ ሰረቁ ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ልባዊ ፍቅርንና አፍአዊ ፍቅርን መለየት የማንችልበት ደረጃ አለ ። ብናውቀው ኖሮ ግን ኮሚኒስቶች ሃሳባቸውን ካሟሉ በኋላ ገፍትረው ሊጥ ሏት የቤተ ክርስቲያን እድገት ደጋፊዎች መስለው የሰበኩንን ለመረዳት በቻልን ነበር ።

ለምሳሌ አንዲት ልጃገረድን የትዳር ጓደኛ እንድት ሆነው የሚፈልግ ሰውና በአፍ ጥበብ አታሏት ምኞ ቱን ከፈጸመ በኋላ ላይኑ እንኳ የሚጠላት ጐረምሳ ሁለቱም ልጃገረዲቱን ሲቀርቧት የልባቸውን በልባ ቸው ይዘው በተመሳሳይ ቃል ማለት «ወደድኩሽ» በማለት ነው ፤ ኮሚኒስቶችም በርሷ ትከሻ ኃይል ካገኙ በኋላ ያላቸውን አቅድ በውስጥ ደብቀው የቤተ ክርስ ቲያን እድገት ደጋፊዎች እንደሆኑ በሰፊው ያወሩና ያስወሩ ጀመር ። ለዚህ ነው ጌታችን «የበግ አጐዛ ለምድ ለብሰው ከሚመጡት ተኩሎች ተጠበቁ ያለን» ። ተኩላ አጐዛ ለብሶ በግ ሊመስል ይችላል ፤ ዳሩ የበ ግና የተኩላ ተፈጥሮ የተለያየ ነው! ቤተ ክርስቲያንን ሁለት ድምፆች «እንወድሻለን» ይሏት ነበር ። አንዱ

ከልቡ ወዳጅዋ ነው ፤ አንዱ ግን ፈቃዱን ከፈጸመ በኋላ ሊያጠፋት ነው ። ውሸታሙን ከውነተኛው ለመለየት ችግር ሆነባት ፡ ምእመናኑም ቤተ ክርስቲያንን እወድሻለሁ ያለ ሁሉ የሷ ወዳጅ መስላቸው እንዲያው በአንድ ፩ ሺህ የሃይማኖት ሰዎች ባሉበት ስብሰባ ላይ በአንድ ወገን በሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች (ክርስቲያኖችና) ለቤተ ክርስቲያን መዘጋት ምክንያት የሆነውን ደግሞም የአምላክ የለሽ እንቅስቃሴ (ዘ ጐድለስ ሙቨመንት) መሪ የነበረውን በአንድ ወገን ግን ለቤተ ክርስቲያን ማደግ ታላቅ ምኞት እንዳለው አስመስሎ የሚሰብከውን ጆሴፍ ስታሊንን የዚያ ጉባዔ ፕሬዚዳንት እንዲሆን በታላቅ ድምጽ መረጡት ። በታላቅ የንግግር ችሎታው አስተሳሰባቸውን ስለለወጠው ታላላቅ የቤተክርስቲያን መሪዎች ኮምኒዝም እና ክርስትና ወንድማማች እንደሆኑ ለጉባዔው በንግግራቸው መግለጽ ጀመሩ ። አንዱ ከሌላው በመቀባበል ሃሣቡን አጸኑት ፤ መጪው የአስተዳደር ዘመን የደስታ የፍስሐ ጊዜ እንደሚሆንና ቤተ ክርስቲያንም በዚያ ጊዜ ታላቅ እድገት እንደምታገኝ በውሸት ተስፋ የሰሚዎቻቸውን አእምሮ ሞሉት ፡ እኔና ባለቤቴ በዚያ ጉባዔ ተገኝተን ነበር ። ሚስቴም ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብላ «ሪቻርድ ተነሳና በክርስቶስ ፊት ላይ የሚተፉትን ምራቅ ጥረግ አለችኝ ፤ እኔም መለስ አደረግሁና ስሚ ይህን ባደርግ አንቺ ባል አልባ ሴት እንደምትሆኚ ስለማውቅ ነው እንጂ በክርስቶስ ላይ ማላገጣቸውን ባለማወቅ መሰለሽ? አልኳት ። ለውነትና በእውነት ለጌታው ክብር የማይቆምን ወንድ ባሌ ብዬ ለመጥራት አልመኝም ፡ ደግሞም ፈሪ ባል ከሚኖረኝ የቀረው ይሻለኛል አለችኝ ። የሚስቴ ንግግር ቀድሞ ያልነበረኝን ድፍረት ሰጠኝ ። በዚያ ታላቅ ጉባዔ ፊት ቆሜ «እና

ንተ ክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጌታ ያለውን አስተውሉ» «አንድ ሰው ለሁለት ጌታ ሊገዛ አይችልም» እናንተ ግን ያን እንዲያደርጉ ክርስቲያኑን ሕዝብ ትገፋፋላችሁ ። ኮሚኒዝምን ታመሰግናላችሁ ፤ ያም የምታመሰግኑት ኮሚኒዝም የብዙ ክርስቲያኖች ገዳይና የብዙ አብያተ ክርስቲያኖች መዘጋት ምክንያት እንደሆነ የዘነጋችሁ ይመስላል ፤ ታዲያ ኮሚኒዝም የብዙ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ገዳይ ሲሆን ሳለ እንዴት ልናመሰግነው ይገባል? ክርስቲያኖችን እንዲገድልና ቤተ ክርስቲያኖችንም እንዲዘጋ ሃይል እንዲያገኝ እንርዳውን? አሁንም ቢሆን ስለ አምላካችንና ስለ ሃይማኖታችን ክብር ልንቆም ይገባናል ፤ ክርስቲያን ሆይ ፤ «ለጌታህ ቁም» የሚለውን ድፍረት ያለበትን ንግግር አሰማሁ ፤ ያ ንግግር ተሰብስበንበት ከነበረው የፓርሊያሜንት አዳራሽ በቀጥታ ወደ የቤቱ በሬዲዮ ይተላለፍ ነበር ። ብዙ ካህናት ኮሚኒዝምና ክርስትና ተስማምተው ሊኖሩ ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ተቀበሉት ።

እንዲያውም አንድ ቄስ የኮሚኒስቶች አርማ የሆነውን «ማጭድና መዶሻ» በካባውና በቆቡ ላይ ለጥፎ በቅስና ማዕረግ ስም ሳይሆን የኮሚኒስት መሪዎች በሚጠሩበት የማዕረግ ስም እንዲጠሩት ለፈፈ ።

አንድ ቀን ሬዚታ በምትባለው መንደር ያለውን የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ለመካፈል ሄጄ ነበር ፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የመስቀል ምልክት ሳይሆን የኮሚኒስቶች አርማ የሆነው ቀይ ባንዲራ ይውለበለብ ነበር ። ውስጡ የተሰበሰቡት ሰዎች የሚዘምሩት ክርስቲያናዊ መዝሙር ሳይሆን የኮሚኒስቶችን መዝሙር ነበር ፤ የቤተ ክርስቲያኑም መሪ ተነስቶ

ስለስታሊንና ሌኒን ብዙ ከተናገረ በኋላ እርግጥ ስታ ሊንና ሌኒን የብዙ ሰው ገዳዮች መሆናቸው የታወቀ ነው፥ ቢሆንም ይህን ያደረጉት ሰዎች በመልካም ሁኔታ እንዲኖሩ ለማድረግ ስለሆነ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከመፈጸማቸው በቀር ምንም አልበደሉም ሲል ንግግ ሩን ደመደመ፣ እንደ አንድ ታላቅ ነብይ እንደ አንድ ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር አድርጐ የስታሊንን ስም ለጉባዔው አወጀ ። እንደነ ፓትራሲያኑ የመሳሰ ሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቅስናቸው ላይ ተደ ራቢ አድርገው የሚስጥር ፖሊሶች የሆኑ የሉተራ ዊት ቤ/ክ መሪዎች በየቲዮሎጂው ት/ቤት እግዚአ ብሔር ለዓለም ማለት ለሰው ልጆች ደህንነት ሶስት መገለጥን ሰጥቶአል፥ ይኸውም፥ ፩/ በሙሴ፥ ፪/ በክ ርስቶስ፥ ፫ኛ/ በስታሊን፥ ይኸውም የመጨረሻው ከቀደሙት ከ፪ቱ ይልቅ ታላቅ መገለጽን አግኝቶአል። ለራሱ የሚል ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳ የሆነ ትምህ ርትን ማስተማር ጀመሩ ። ምንም እንኳን አንዳንዶች ጊዜያዊ ጥቅምንና ማዕረግን በመሻት ከእምነታቸው ቢናወጡም ሌሎች ክርስቲያኖች ስለእምነታቸውና ስለጌታቸው ክብር ቆሙ ። ቀድሞ የቤ/ክ/መሪዎች አሁን ግን የኮሚኒስት ደጋፊዎች የሆኑ ሰዎች እነ ዚህን እውነተኞች ክርስቲያኖች በመወንጀል ልዩ ልዩ ስቃይን አበዙባቸው፥ በሩሲያ ያሉ እውነተኞች ክርስ ቲያኖች ከምድር በታች ቤ/ክ/ እንደሰሩ እንደሰማን እኛም በሩማንያ ያለን ክርስቲያኖች ያንን እንድናደ ርግ ጊዜውና ሁኔታው አስገደደን ። ስለዚህ ቆራጥ የሆኑ ክርስቲያኖችን ሰብስቤ ጉዳዩን ካዋየኋቸው በኋላ የምድር በታች ቤ/ክ/ መሥራትን ጀመርን ። በዚያ ጊዜ በሕብረተ ሰቡ ታዋቂ የሚያደርገኝ ሥራ ስለነበረኝ በድብቅ ለማድርገው የቤ/ክ/ መስፋፋት

ሥራ እንደመሸፈኛ ሆነልኝ። የሉተራውያን ቤ/ክ መሪ ነበርኩ እንዲሁም በሩማንያ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ወኪል ነበርኩ፤ አዲሱ አገልጎሎቴ ሁለት ክፍሎች ነበሩት ፩ኛ/ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሩሲያውያን ወታደሮች መካከል ክርስትና መስበክ፤ ፪ኛ/ በኮሚኒስቶች ሥር ለተያዘው የሩማንያ ሕዝብ የወንጌል ነጻነት በሞላ እንዲደርስ በሚስጥር ማስፋፋት ነበር።

## ሩሲያውያን ለወንጌሉ ቃል የተጠሙ ናቸው

ወንጌልን በተለያዩ ቦታ ለተለያየ ሕዝብ ሰብኬ ዋለሁ፤ ዳሩ ከሁሉ እኔን የሚያስደስተኝ በሩሲያውያን መካከል ወንጌልን መስበክ ነው፤ ምንኛ ለወንጌሉ ቃል የተጠሙ መሰሏችሁ! በሕይወታቸው ኮሚኒዝም ሊያረካው የማይችለው ጥማት ነበራቸው፤ ያም ጥማት ሊረካ የሚችለው በወንጌሉ ብቻ መሆኑን የተረዱ የኮሚኒስት ወታደሮች አብዝተው መሥራቹን ሊሰሙ ይሹ ነበር፤ ይህ ነው በነሱ መካከል የማደርገውን አገልጎሎቴን ተወዳጅ ያደረገው። አንድ ቀን ጓደኛዬ የሆነ ኦርቶዶክሳዊ ቄስ የሩሲያ ቋንቋ ስለማያውቅ ወደ ቤቴ ስልክ ደውሎ ለአንድ የሩሲያ ወታደራዊ ኦፊሰር የሆነ ሰው ስለ ክርስቶስ እንድመስክርለት እንደላከው ገለጸልኝ። ይህን ኦፊሰር መጀመሪያ ስለ እምነት ማንም አልነገረውም፤ ግን ወደዚያ ኦርቶዶክሳዊ ቄስ ቤት ሄዶ ኃጢአቱን ተናዘዘ። ብዙ ለማወቅ ብዙ ለመስማት ፈልጎ ነበር፤ ግን ያ ቄስ የሚያውቀው ቋንቋ ከርሱ ጋር ስላልተግባባ የሩሲያን ቋንቋ ወደሚያውቅ ሰው እንደተላከ ከቄሱ በሰማ ጊዜ በጣም

ደስ አለው በማግስቱ ወደ ቤቴ በተነገረው ምልክት አማካይነት መጣ ያ ሰው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ስለ ክርስቶስ የሚያውቀው ምንም አልነበረም ቢሆ ንም እግዚአብሔርን በጣም ይወዳል ። ሊያገለግለውም ፈቃደኛ ነበር ። ያለ ምንም ገለጻ ያን ያህል ልቡ ለሃ ይማኖቲዊ ትምህርት የተከፈተ መሆኑ አስደነቀኝ ። የተ ራራውን ስብከትና ጌታ በምሳሌ ካስተማረበት ክፍል አስረዳሁት ውብ የሆኑትን ጌታ ለሰው ልጆች ሁሉ የገለጸውን የመዳንን መንገድ በሰማ ጊዜ በደስታ ዘለለ ፡ ምንኛ ደስ የሚሉ! ምንኛ የማጽናናት ሃይል ያላቸው ቃላት ናቸው! እያለ ይጮህ ነበር ። ወንጌልን ለመስበክ የመጀመሪያዬ ባይሆንም ሰው የወንጌሉን የምሥራች ሰምቶ በደስታ ሲፈነድቅ ለማየት ገና ጀማሪ ነበርኩ ፡ ወዲያው የዚያን የኦፊሰር ደስታ የሚያቋርጥ መርዶ ነገርኩት ፡ ይኸውም አንዳች መሠረት ሳልሰ ጠው ያ ምን ዓይነት አዳኝ ነው! ምን ዓይነት የፍቅር አምላክ ነው! ይለው የነበረው ጌታ እንደተሰቃዬ ፡ መከራ እንደተቀበለ ፡ እንደሞተ ከሚያስረዱት ክፍ ሎች አነበብኩለት ። ይህን ሰው ስለጌታ አዳኝነት ለሰው ልጆች ስለሰጠው ተስፋ ብቻ አነበብኩለት ስለዚህ ም የሰው ልጅ ይህን አዳኝ እንደሱ በደስታ የሚቀ በሉት መስለው ። ከመጣበት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ መከራ ለመቀበል እንዲያውም ለመሞትና በሞቱም የሰው ልጆችን ከሞት ለማዳን እንደሆነ አላወቀም ፡ አሁን ግን በድንገት የእውነተኛ መምህር እንደተገ ደለ ስነግረው በጣም አዘነ ፡ ጮሆ አለቀሰ ። እስኪ አስቡት ስለ አንድ ስለችግራችሁ ስለሚቆረቆር ከጭ ንቀታችሁ ሊታደጋችሁ ስለሚወድ ሰው ሰምታችሁ ያ ሰው በድንገት ሞቱን ቢያረዷችሁ ምን ይሰማች ኋል? በእንባ የሚታጠበውን የዚያን ኦፊሰር ፊት አተ

ኩሬ ስመለከት ጌታ በተሰቀለበት መስቀል እግር ስር ተደፍታ ታነባ የነበረችው የማርያም መግደላዊት ታሪክ ትዝ አለኝ ። ወዲያው ለማጽናናት በመሞከር ስማ! የዚያን አዳኝ ታሪክ እኮ አልጨረስኩልህም አዎን ስለ ትምህርቱ ፣ ለሰው ልጆች ስለሰጠው ተስፋ፣ ስለመከራው ፣ ስለስቅለቱ ፣ ስለሞቱ ፣ ስለመቀበሩ ፣ እን ደነገርኩህ አውቃለሁ ። አሁን ያ አዳኝ ምን እንደሆነ ልንገርህ? በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ ። ስለ ትንሣኤው ከሚያስረዱት ክፍሎች አነበብኩለት ፣ በዚህ ጊዜ በመ ጀመሪያ ስለ አዳኝነቱና ለሰው ልጆች ስላዘጋጀው የመዳን መንገድ ስነግረው ከሆነው የበለጠ ተደሰተ፣ ዘለለ ደስታው ምን ያህል ታላቅ እንደነበረ ልገልጽ አልችልም ፣ እንድንጸልይ ነገርኩትና ለመጸለይ ሁለ ታችንም ተንበርክከን ሳለን ይጸልየው የነበረው ጸሎት «እግዚአብሔር ሆይ ምንኛ ታጋሽ ነህ አንተ እኔን እኔም አንተን ወደመሆን ብንቀያየር ስላደረግኸው ኃጢአት ምንም ይቅር አልልህም ነበር ፣ ዳሩ አንተ ምህረትህ የበዛ መዓትህ የራቀ ቸር ሁሉን ቻይ አም ላክ ስለሆንክ ይቅር አልከኝ ስላደረግኸውም ውለታ ታናሽ ከሚሆን ከባርያህ ምስጋናን ተቀበል» የሚል ነበር ። ይህን ከተሰበረ ልብ የሚወጣውን ጸሎት ለመ ስማት በሰማይ ያሉ አእላፋት መላእክት ሁሉ የሚ ሰሩትን አቁመው ጆሮዋቸውን ወደዚያች አነስተኛ ክፍል እንዳዘነበሉ መሰለኝ ። ያም ሩሲያዊ ኦፊሰየር ከዚያች ቀን ጀምሮ ሕይወቱ ተለውጦ በጌታ በኢየ ሱስም የሚያምን ክርስቲያን ሆነ ።

አንድ ቀን ደግሞ በአንድ ሱቅ ውስጥ ሳለሁ አንድ ሩሳዊ ካፒቴን ከሚስቱ ጋር ዕቃ ለመግዛት መጥ ተው ሳለ ከባለ ሱቁ ጋር ለመግባባት የቋንቋ ችግር

እንደነበር አወቅሁና እንድተረጉምላቸው ፈቃዳቸውን ከጠየቅሁ በኋላ በሩሲያና በሩማንያ ቋንቋ እተረጉም ላቸው ጀመር ። ስለዚህም በመካከላችን ማለት በእኔና በሩሲያዊው መካከል መግባባት ተፈጠረ ፡ በዚያው ቀን እነዚያን ባልና ሚስቶች እቤት ምሳ እንዲጋበዙ ጠየ ቅኋቸው ፈቃደኞች ሆኑ ። ምሳ ከመብላታችን በፊት ያላችሁት ክርስቲያኖች ቤት ነውና ከመብላታችን በፊት መጸለይ ይገባናል አልኳቸው ። በሩሲያ ቋንቋ ሁሉንም በመወከል ጸለይኩ ። ከዚያ በኋላ በሚበሉት ምግብ ተደሰቾች አልነበሩም ። ምን ማድረጌ እንደነ በር ስለእግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እያከታተሉ ይጠይቁኝ ጀመር ። ካጠያየቃቸውም እንደተረዳሁት ስለ ሃይማኖት ቀቂት እንኳ እውቀት አልነበራቸውም ። ለእነዚህ ሰዎች ወንጌልን መስበክ ቀላል አልነበረም ። መቶ በጐች ስለነበሩትና ከመቶም አንዲቷ ብትጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን ትቶ አንዲቷን ፍለጋ ስለሄደው ሰው ታሪክ ነገርኳቸው ፡ ይህን ሲሰማ ካፒቴኑ አሃ! እንዴት መቶ በጐች ሊኖሩት ቻለ? እየ ዞሩ ከሚገባው በላይ ሀብት ሲኖረው ለመንግሥት ውርስ የሚያደርጉ ሰዎች እንዴት አልወሰዱበትም? ይህ ክርስቶስ የምትለው ለራሱ ብቻ ሀብትን የሚሰ በስብ ለሌሎች ጉዳት ግን የማያስብ ጨካኝ ገዥ ነዋ! ስለ ወይኑ ቦታና ስለ ሠራተኞቹ ነገርኳቸው ፡ የወ ይኑ ሠራተኞች በማመጻቸው መልካም አደረጉ ምክን ያቱም ያ ወይን የግል ንብረት ሳይሆን ለመንግሥት መስጠት ነበረበት ፡ የምናገረው ሁሉ የማይጥማቸው ነበር ።

የዓለም አዳኝ የሚሆን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ከማርያም ሥጋን ነስቶ እንደተወለደ ስነግራ

ቸው ሁለቱ በመተያየት ከት ብለው ከሳቁ ፤ በኋላ አዲስ ነገር መጣ ፡ ለመሆኑ ይህች ማርያም የምትሏት የእግ ዚአብሔር ሚስት ናት አሉኝ ። ከነዚህ ሰዎች ባደረግ ሁት ውይይት የተረዳሁት ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር ስለሃይማኖት ስምተው ለማያውቁ ሰዎች ለማስተማር በጥንቃቄና በጥበብ ደረጃ በደረጃ መናገር መልካምና ውጤት ያለው መሆኑን ነው ፤ ለነሱ በሚስማማ ቃላት ሃሳባችንን ልንገልጽላቸው ይገባል ።

ለምሳሌ ወደ ሴንትራል አፍሪካ ሄደው ወንጌል የሚሰብኩ ሰባክያን «ኃጢአታችሁ እንደ ቅርምዝ ብትቀላ እንደ በረዶ ትነጻለች» ፡ የሚለውን የነቢዩን የኢሳይያስን ቃል ለሰሚዎቹ በሚስማማ ቃላት ለመና ገር «ኃጢአታችሁ እንደቅርምዝ ብትቀላ እንደኮክናት ስብ ትነጻለች» ፡ ወደሚል መተርጐም አለባቸው ፤ ምክ ንያቱም በሴንትራል አፍሪካ በረዶ የሚባል ነገር ፈጽሞ ባለመኖሩ ነው ። እኛ በኮሚኒስት አገር የምንኖር ወን ጌላውያን መጀመሪያ ክርስትና ከማርክሲዝም ጋር የሚ ስማማበትን መንገድ ከገለጽንላቸው በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ወንጌሉ ብርሃን መምራት የሚያስችለንን ጥበብ ማወቅ አለብን ፡ ያ ካፒቴንና ሚስቱ ከብዙ ማስረጃና ክርክር በኋላ በክርስቶስ አመኑ! ከዚያም በኋላ የክር ስቶስን ወንጌል በሩሲያ ወታደሮች መካከል በሚስ ጢር በምናስፋፋበት ሥፍራ ተካፋዮች ሆኑ ፤ ብዙ ወን ጌሎችንና ሃይማኖታዊ ጽሑፎችን በወታደሮች ካምፕ ለማደል ረዱን ። በሥራውም ተባባሪ በሆኑ ወታደሮች አማካይነት ሥራውን ይበልጥ አስፋፉን ።

ሩሲያኖች በጦርነት ላይ ስለሆኑ ከናት ከሚስትና ከልጅ ከተለዩ ብዙ ዓመታቸው ስለሆነ የሚስቶቻቸ ውና የልጆቻቸው ናፍቆታቸው ከፍ ያለ ነበር ፡ ስለ

ዚሀ ቢጨክኑ ቢጨክኑ በሕፃናት እንደማይጨክኑ ስላወቅን ብዙ የክርስቲያኖች ልጆችን ሰብስበን በአደባባይ በመናፈሻና በካምፑ ውስጥ እንዲበትኑዋቸው ብዙ ወንጌሎችንና መጽሐፍ ቅዱሶችን በቦርሳ እያስያዝን እንልካቸው ነበር ፣ እነዚህ ሕፃናት በቀጥታ ወደ ካምፑ ይገቡና ከወታደሮቹ ከተግባቡ በኋላ ሩሲያኖች እንደልጆቻቸው ስለሚያዩዋቸው ለሚሰጡዋቸው ከረሜላ ወረታውን የሚመልሱት መጽሐፍ ቅዱስ በመስጠት ነበር ፣ እነዚያ ቸኰላት እነዚህ ግን መጽሐፍ ቅዱስን! ለኛ በጣም የሚያዳግተንን ሥራ በነዚህ ሕፃናት አማካይነት ዕለት ዕለት ቁጥራቸው በርከት ያሉ ወንጌሎችን ለወታደሮች እናድል ነበር፣ ውጤቱም እጅግ አስደሳች ነበር ።

## የወንጌል ስብከት በካምፕ ውስጥ

ለሩሲያኖች ወንጌልን የምንሰብከው አንድ ወይም ሁለቱን በማነጋገር ብቻ ሳልሆን በርከት ያሉ ወታደሮችንም ሰብስበን በማስተማር ነው ። በካምፕ ውስጥ በወታደሮች ከብዙ ሰዎች የተዘረፉ ሰዓቶች ስለነበሩ ማንም ጥሩ ጥሩ ሰዓቶችን በርካሽ መግዛት ቢፈልግ ወደ ወታደሮቹ ካምፕ መሄድ ነበረበት ። ለእኛ ካምፕ ውስጥ መግባት ምክንያት የሆነንም ይኸው ነበር ። በአንድ የኦርቶዶክስ በዓል ቀን ሰዓት የምገዛ መሆኔን ለዘቡ ከገለጽኩ በኋላ ወደ ካምፕ ውስጥ ገባሁ ፤ ለመጀመሪያ መግባቢያ እንዲሆነኝ ይህ ስንት ነው? የዚያቸው ዋጋ በዛ ይኸኛው ደግሞ ትልቅ ነው ፤ ይልቅስ ይህን ቀንስልኝና ልግዛህ በማለት ደርሶ ሰዓት እንደሚገዛ እከራከር ጀመር ። ሰዓት ገዥ ስለመሰልኳቸው ያላቸውን ልዩ ልዩ ሰዓት ለማ

የት ብዙ ወታደሮች ከበቡኝ ። ጉባዔው በርከት ማለ ቱን ካየሁ በኋላ ንግግሬን በቀልድ ለመጀመር ለመ ሆኑ ስማችሁ ጴጥሮስ ወይም ጳውሎስ የሆናችሁ አላ ችሁን? አልኳቸው ። አንዳንዶች እንዳሉ ገለጹልኝ ። ታውቃላችሁ ዛሬ ኦርቶዶክሶች የጴጥሮስ ወጳውሎስ ቀንን የሚያከብሩበት በዓል እንዳላቸው አልኳቸው በዕድሜ ገፋ ያደረጉ ወታደሮች እንደሚያውቁት ነገ ሩኝ ። ታዲያ እነዚህ ጴጥሮስና ጳውሎስ የተባሉት ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩና የሠሩትስ ታላቅ ሥራ እን ዲያስረዱኝ ጠየቅሁዋቸው ። ሁሉም ዝም አሉ ፤ እኔም የሠሩትን ታላቅ ሥራ ለመግለጽ ፈቃድ ከጠየቅሁ በኋላ ስለ ሥራቸው አስረዳቸው ጀመር ፤ ካረጁትም ሰዎች አንዱ አንተ እዚህ ካምፕ የመጣኸው ሰዓት ልትገዛ ሳይሆን ሃይማኖት ልትሰብክ ነውና ፤ ስለዚህ አረፍ በልና አስረዳን አለኝ ፤ እኔም በገጠመኝ ዕድል በመገረም ሳመንታ ሳለሁ ቀጠል አድርጐ ተጠንቀቅ! እኛ እዚህ ካለነው ሰዎች ሌላ የምንጠራጠረው ሰው ከመጣ ንግግርህን እንድታቆም የምነግርህ እጄን ጉል በትህ ላይ በማድረግ ነው ፤ ስለዚህ እጄን እጉልበትህ ላይ ሳደርግ ቶሎ ንግግርህን ለውጠህ ስለሰዓት ዋጋ እንነጋገር አለኝና ከጀመርኩበት እንድቀጥል ነገረኝ ። እኔም ስለ ጴጥሮስና ጳውሎስ እነሱም ንጉሥ ጌታ አምላክ ፤ አዳኝ እያሉ ለሰዎች ያስተማሩትን ክርስቶ ስን ሰበኩላቸው ። ሰው እርሱን በማመን የዘለዓለም ሕይወትን እንደሚያገኝ ነገርኳቸው ። አንድ የማይተ ማመኑበት ሰው ወደኛ ይመጣ ጀመር ፤ በዚህ ጊዜ እን ደውላችን እጁን ጉልበቴ ላይ በማድረግ ንግግሬን እንድቀይር ጠቆመኝ ፤ እኔም ይኸ ውድ ነው ፤ ይህ መናኛ ነው ፤ እባክህን አምስት ብር መልስልኝ በማለት ሰዓት እንደሚገዛ እከራከር ነበር ፤ ያም ሰው ስለ ሰዓት ብቻ

እንደምንነጋገር ስለሰማ በመጣበት አኳኋን ጥሎን ሄደ ። እኔም እንደገና ስብከቴን ቀጠልኩ ። ያን ንግግሬን (ስብ ከቴን) ከሰሙ ብዙዎቹ በክርስቶስ አመኑ ። ብዙ ወን ጌሎችንም በሚሰጥበት በካምፕ ውስጥ ላሉ ወታደ ሮችም የምናድልበትን መንገድ አስረዱን ። ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች መጽሐፍ ቅዱስንና በሃይማኖታዊ ጽሑፎችን በመበተን ሥራ ላይ ተባባሪዎች ናችሁ በመባል ታሰሩ ። ለዚህ ሥራ ተጠያቂ እኔ መሆኔን ቢያውቁም እንኳ ሊያጋልጡኝ አልፈለጉም ። እኛ በሩ ማንያ ያለነው ክርስቲያኖች ወንጌልን እንዲህ በመ ሰለ መንገድ ስናስፋፋ በሩሲያ ያሉ ክርስቲያን ወገ ኖቻችን በቆራጥነት ስለጌታቸው ክብር እንደሚቆ ሙና ወንጌልን በትጋት እንደሚያስፋፉ ስንሰማ በጣም ተደሰትን ። በይበልጥ ሊያስደስተን የቻለው ግን እነ ዚያ ይህን የሚሰሩት ቆራጥ ክርስቲያኖች ከኮሚኒ ስት ዩኒቨርሲቲ የተመረቁና ራሳቸው ኮሚኒስቶች መሆ ናቸውን ስንረዳ ነው ፣ ምንም እንኳ አሳ ጨውማ በሆነ ውቅያኖስ ቢኖርም ገላው የጨውን ጣእም እንደማ ይወስድ ሁሉ እነዚህም ምንም እንኳ አምላክ እንደ ሌለ ከሚያስተምር ትምህርት ቤት ቢመረቁም እም ነታቸውን ግን ያ ከንቱ ትምህርት አልበከላቸውም ፤ በሩሲያ እንዲህ ያሉ ስለጌታ ክብር የሚቆሙ ክርስ ቲያኖች ነበሩ ፣ በታላቅ ሀዘን እንዲህ ይሉ ነበር ። የም ናደርገው የመዶሻና የማጭድ ምልክት የክርስቶስ ጠላት ምልክት እንደሆነ እናውቃለን ፣ ቢሆንም ክር ስቲያንነታችን እንዳይታወቅና ይህን ውብ የሆነውን ወንጌል ለሚጠፉት ነፍሳት ከማዳረሳችን በፊት እን ዳንገደል በማለት እናደርገዋለን! እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ሥራቸው መልካም ውጤት የሚያገኝና በየቀ ኑም የሚስፋፋ ቢሆንም እንኳ ፍጹም ደስተኞች አል

ነበሩም ። አንድ ቀን አንዱን ክርስቲያን ለምንድነው ደስታችሁ የተሟላ ያልሆነው? ሁልጊዜ ፊታችሁ ላይ ሃዘንን አያለሁ የሃዘናችሁ መነሻ ምንድነው? አልኩት ።

እኛ ክርስትናን የምናስፋፋ በመሆናችን በዚህ በጭንቅ ምድር ደግሞ የወንጌሉ ተሸካሚዎች የመ ሆንን ዕድል በማግኘታችን በጣም ደስተኞች ነን ፤ ግን ደስታችንን የተሟላ እንዳይሆን የሚያደርገው ምን ይመስልሃል? ክርስትናን ማለት ሃይማኖትን በትጋት እንደምናስፋፋ ካወቀ የቤተ ክርስቲያናችን መሪ ራሱ ለኮሚኒስቶች አሳልፎ ይሰጠናል ። ምክንያቱም ራሱ የቤተ ክርስቲያን መሪ የተባለው በኮሚኒስቶች ለዚሁ ተግባር የተሾመ ነው ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን መሪ ራሱ በጐችን ለተኩላ አጋልጦ የሚሰጥ እረኛ ሲሆን እንዴት ደስታችን የተሟላ ሊሆን ይችላል? ምንም እንኳ ይህን የመሰለ ችግር መቋቋም ቢኖር ብንም የክርስቶስ የማዳኑ ሃይልና የመንፈሱ የማጽ ናናት ብርታት ለውስጣዊ ሰውነታችን ደስታን ይሰ ጠዋል ፤ በውጫዊው ሰውነታችን ግን ይህ ነው የማይ ባልን ሃዘንን መሸከም አለብን ።

ክርስትናን ወይም ወንጌልን መስበክ ለኛ በኮ ሚኒስት አገር ለምንኖር ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ከባድ ቢሆን እናንተ በክርስቲያን ምድር የምትኖሩ ወደቤተ ክርስቲያን አንድን ሰው ስታመጡ ሕያው ወደ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንዳመጣችሁት በማ መን ደስታችሁ ከፍ ያለ ነው ። እኛ ክርስቶስን ለኮሚ ኒስቶች ስንሰብክ ግን መከራ ፣ እስራት ፣ ግርፋትና ሞት እንደሚጠብቀው ሳናስረዳ አናልፍም ። ሚስቱ ባል አልባ ፣ ልጁ የሙት ልጅ ይሆን ይሆናል ፤ ይህን ያህል መከራ በሚበዛበት ቦታ ክርስቲያን መሆኑ በጣም

ከባድ ቢመስልም ሰዎች ከእለት ወደእለት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተጨመሩ ናቸው ፤ ይህን በመሰለ ቦታ ክርስቲያኖች የኮሚኒስቶችን አርማ በመለጠፍ ወንጌልን ያስፋፋሉ ። ከዕለታት አንድ ቀን ሥራቸው ቅርጻ ቅርጽ የሆነ ባልና ሚስቶችን አነጋግሬቸው ነበር ። የንግግሬም መክፈቻ እንዲሆን «በእግዚአብሔር ታምናላችሁን» አልኳቸው እግዚአብሔር የለም ፤ እኛ ቢዝቦሽንኪ ማለት «አምላክ የለሽ» ነን ቢሆንም በኔና በሚስቴ መካከል አንድ ክርክር ተነስቶ ነበር ።

የስታሊንን ሐውልት በምንሠራበት ጊዜ ሚስቴ እንዲህ አለችኝ ባሌ! ስለ አውራ ጣት ምን ታስባለህ (አውራ ጣቷን እያሳየችኝ) አውራ ጣትን ከሌሎች ጣቶች ሳናስተባብር መዶሻ ፤ መጋዝ ፤ መጽሐፍና የመሳሰሉትን ለማንሳት አንችልም ። ስለዚህ ይህ አውራ ጣት ሰው በሕይወቱ እስካለ ድረስ ምን ያህል እንደሚጠቅመው አስታውስ ፤ ይህን አውራ ጣት ማን ፈጠረ? እንደምታውቀው እኔም ሆንኩ አንተ በማርክሲዝም ትምህርት መሠረት ሁሉም ካለማንም ፈጣሪ ኃይል የተፈጠረ እንደሆነ እንጂ እግዚአቤሔር ያለመኖሩን ተነግሮናል ። አሁን የምነግርህ ምንም እንኳ እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ አይደለም ብለህ ብትከራከረኝም የአውራ ጣት ፈጣሪ መሆኑን ግን ልትክደኝ አትችልም ፤ የአውራ ጣት ፈጣሪ መሆኑ ከታመነም ስለ ትንሿ አውራ ጣት ሊመሰገን ይገባዋል ። ብዙ ጊዜ ኤሌክትሪክን ፤ ቴሌፎንን እና የባቡር ሐዲድን በመሥራታቸው ኤዲስንና ቤልና ስተፌንሰንን እናመሰግናቸዋለን ። ግን ያለ እርሱ ምንም እንኳ ለመሥራት የማንችልበትን ለአውራ ጣት ፈጣሪ ለምን ምስጋና አናቀርብም? ታውቃለህ ኢዲስንና ሌሎችንም

ታላላቅ ሣይንቲስቶች ምናልባት አውራ ጣት ባይኖ ራቸው ምንም ሊሰሩ አይችሉም ነበር ፡ ስለዚህ አሁ ንም የአውራ ጣት ፈጣሪ የሆነ እግዚአብሔርን እናመስግን አለችኝ ። እኔም ብዙ ጊዜ ባሎች የሆንን ሚስቶቻችንን በቁጣ እንደምንናገራቸው ሁሉ እባክ ሽን ደደብ አትሁኝ ፡ የተማርሽው እግዚአብሔር ያለ መኖሩን ነው ፤ ከሌለም የሰማይና የምድር እንዲሁም የሰው ፈጣሪ ሊሆን አይችልም ። «ሁሉም ከምንም ተገኘ» ታዲያ ከሌለ እንዴት ይመሰገናል ፡ ለጊዜው እኔን ብዙ ላለማስቆጣት ብላ ዝም ብትልም ከዚያ ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር የትንሿ አውራ ጣት ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን የታላላቅ ፍጥረታት ማለት የጸሐይ ፡ የጨረቃ ፡ የከዋክብት ፡ የአበቦችና የሰው በጠቅላላው ለሚታዩት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ማመን ጀመረች ። ቢሆንም ስለ እግዚአብሔር የምታውቅ አልነበረ ችም ። ታሪኩን በርጋታ እንዳዳመጥኩ ጳውሎስ ወደ እናቴ በሄደ ጊዜ በቤተ መቅደሱ ውስጥ «የማይታ ወቅ አምላክ» የሚል ጽሑፍ እንዳነበበ ትዝ አለኝ ። ይህችም ሴት ያን እግዚአብሔር ማመናቸው ካለማ ወቅና ከፍራት የመነጨ ሳይሆን በርግጥ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሚገባ ስነግራቸው በጣም ተደሰቱ ። እርግጥ እንዳላችሁት እግዚአብሔር በሰማይ ብቻ አይደለም ያለው ። እርሱ መንፈስ ስለሆነ በሰማይና በምድር የተ ንሰራፋ ጊዜና ቦታ የማይወስነው አምላክ ነው ። ያም አምላክ ፍቅር ከመሆኑ የተነሳ እርሱን በማመን የሰው ልጆች ሁሉ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያገኙ ዘንድ አንድ ልጁ በመስቀል ተቸንክሮ የዓለምን ኃጢአት እንዲ ያስወግድ ላከው ። እነዚህ ሰዎች አምላክ ለሰው ሁሉ ልጆች ስላለው ዓላማ ባያውቁም የፍጥረት ዓለም ጌታ የሆነ አምላክ መኖሩን አውቀው በፈጣሪነቱ አምነው

ነበር ። የሰው እምነቱ የተሟላ እንዲሆን ግን እግዚአ ብሔር ወደ ዓለም በላከው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይገባል ።

አንድ ቀን ደግሞ አንዲት ሩሲያዊት ወይዘሮ በመንገድ ስታልፍ ጠጋ ብዬ ይቅርታ ከጠየቅሁዋት በኋላ እኔ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን መሪ ነኝና ፈቃድሽ ከሆነ ስለ ክርስቶስ ላውጋልሽ አልኳት ። እርሷም ደስ በሚሉ ዓይኖቿ እያየችኝ ለመሆኑ ክርስ ቶስን ትወዳለህን? አለችኝ ። እንዴታ በሙሉ ልቤ እንጂ አልኳት ። ወዲያው እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ ፥ የአ ስተቃቀፏ ሁኔታ ተመልካችን ስለሚያስጠረጥር ምና ልባት ዘመዱ ናት እንዲሉ በማለት እኔም አቅፌ ሳም ኳት ። ብዙ ከተጫወትን በኋላ «ክርስቶስ» ከሚለው ስሙ በቀር ስለ ሥራው ወይም ስለ ትምህርቱ ምንም የምታውቀው አልነበረም ፥ በጣም ተደነቅሁ የሠራውን ፥ ያደረገውን ፥ ያስተማረውን ሳያውቅ ማን ሊያምን ይችላል? ይህች ሴት ግን «ክርስቶስ» የሚለውን ስሙን ብቻ በማወቋ ፍቅሯ ታላቅ ነበር ። የክርስቶስን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ከየት እንደሰማች ጠየቅኳት ። እንዲህ አለችኝ ፥ የተማርኩት በኮሚኒስቶች ት/ቤት ነው ። ስለ ኮሚኒዝም አስተዳደርና ሥርዓት በደንብ አውቃለሁ ። ሕፃን በነበርኩበት ጊዜ አያቴ በግድግ ዳው ላይ ለተሰቀለው ሥዕል በመንበርከክ የጧትና የማታ ጸሎቷን ስታደርስ እመለከት ነበር ፥ እስከ አሁን ድረስ በልቤ ውስጥ ፍቅር የተተከለው ሥዕሉ ሳይ ሆን ክርስቶስ የተሰኘው ስሙ ነው ። እያደር በማላው ቀው ኃይል የዚህ ስም ታላቅነት እውነተኛ እየሆነ ብኝ ሄደ ። ያ ስም ምርኩዜ ፥ በችግሬ መጽናኛዬ ፥ ሆነ ። ይህን ታሪክ እንደሰማሁ «ጉልበት ሁሉ ለክርስቶስ

ስም ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ክቡር ስሙን ያመሰ ግናል» የሚለው ጥቅስ ከመቸውም ይልቅ ሃይል ያለው መስሎ ታየኝ ። በርግጥ ከንቱ ፍልስፍና የሰዎችን ሕሊና ያጨልማል ፣ የክርስቶስ ስም ግን ሰዎችን ወደ ብርሃን የሚመራ ኃይል አለው ። ይህች ሴት ቀድሞ በስም ብቻ ታውቀው የነበረውን ፣ ክርስቶስን ዛሬ የደህንነ ትን ደስታ በልቧ ይዛ ታገለግላዋለች ። ከሩሲያኖች ጋር ያሳለፍሁት ጊዜ ሁሉ በጣም ደስ በሚል አስደናቂ ተአምራት የተሞላ ነው ። አንድ ቀን በባቡር ጣቢያ አካባቢ የምትኖር ክርስቲያን እህቴ ስለ ክርስቶስ እንድነግረው በማለት አድራሻዬን ሰጥታ አንድ የኮ ሚኒስት ወታደሮች አለቃ የሆነን ሰው ላከችልኝ ። ይህም ሰው እቤቴ የመጣው ማታ ነበር ፤ ሻይ ከጋበዝ ኩት በኋላ በምን እንዳገለግልህ ትፈልጋለህ አልኩት ፣ «ስለ ብርሃን ለማወቅ መጥቼአለሁ አለኝ» የሕይወ ትን ትርጉም ለማየት ያለው ምኞት ታላቅ መሆኑን በመረዳት ኢየሱስ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተ ለኝ ሁሉ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል» ብሎ ካስተ ማረበትና ከሌላም ከልዩ ልዩ ክፍሎች አነበብኩለት ። በጥንቃቄ ካዳመጠኝ በኋላ እኔ ራሴ በጨለማ ባሉ ሰዎች መካከል የምኖር ራሴም በጨለማ ያለሁ ሰው ነኝና የምታነብልኝ በርግጥ ሰውን ሁሉ ወደ ብርሃን የሚመራው የእግዚአብሔር ቃል ነውን? አለኝ እንደ ሆነም አረጋገጥኩለት ፣ ያም ሰው በጌታ አመነ ። ደስ ታውም ከፍ ያለ ነበር ፣ ሩሲያኖች ከሌሎች ሕዝብ ይልቅ ሃይማኖታዊ ስብከትን ለመቀበል ልበ ደንዳ ኖች አይደሉም ። በያዙት ነገር የሚተማመኑ ጽኑ ሕዝብ ናቸው ፣ ተቃዋሚ ከሆኑም ያን የሚቃወሙትን ለማ ጥፋት ምኞታቸው ታላቅ ነው ። ስለዚህ ነው የሩሲያ ክርስቲያኖች በቆራጥነትና በጀግንነት የክርስቶስን

ወንጌል የሚያውጁት ። የያዙትን ሃይማኖት አክባሪ ዎች ናቸው ። ሩሲያ የወንጌል ዘር እንዲዘራባት ምቹና ለም የሆነች የለሰለሰች ምድር ናት ። እነርሱ ከተለወጡ ማለት ክርስቲያን ከሆኑ መላውን ዓለም ይለውጡ ታል ። እንዲለውጡም የመለወጥ ኃይል ያለውን የእግ ዚአብሔርን ቃል እንስጣቸው ፣ ምንም እንኳ የወንጌ ሉን ተስፋ ለመስማት የተራበ ልብ ቢኖራቸው ሊሰሙ አይችሉም ። አንድ ቀን በባቡር ውስጥ ተሳፍሬ ሳለሁ አንድ ሩሳያዊ አፌሴር እፊቴ ተቀምጦ ነበር ፣ እኔም ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ስለ ክርስቶስ ነገርኩት ። ከዚ ያም እግዚአብሔር ያለመኖሩን ሊያስረዳኝ ከነቦል ቴር ፣ ከነማርክስ ፣ ከነሊኒንና ከነ ዳርዊን መጻሕፍት እየጠቀሰ ያስረዳኝ ጀመር ። እንዳቋርጠውና እንድጠይ ቀው እንኳ ጊዜ አልሰጠኝም ። ምናልባት የተናገረው ለ፩ ሰዓት ይሆናል ፣ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ግን እሺ እግዚአብሔር መኖሩን የማታምኑ ከሆነ በችግራችሁ ጊዜ ለምን ትጸልያላችሁ? አልኩት ። ሌባ በተያዘ ጊዜ እንደሚያፍር ድንግጥ ብሎ እንደምንጸልይ ማን ነገ ረኽ? አለኝ ። እኔም ጥያቄዬን በጥያቄ ከመመለስህ በፊት ቅድም ለጠየቅሁህ ጥያቄ መልስ ስጠኝ አል ኩት ፣ አዎን በጦር ግንባር ላይ በነበርንበት ጊዜ ጀርመ ኖች ሲከቡን ፣ የምናደርገው ሲጠፋብን «እግዚአብሔር ሆይ ፣ አውጣን የማማ (የእናታችን) መንፈስ ሆይ እር ዳን ፣» እንል ነበር ። አዎን የቃላትን ማማር ሳይሆን የልብን ጭንቀት በሚያነብ አምላክ ፊት መልካም ጸሎት ነበር ። ለሩሲያኖች የምናደርገው አገልግሎት እየሰፋ ሄደ ፣ አስታውሳለሁ ፒተር የተባለው የ፳ ዓመት ወጣት በድብቅ ወደምንሰበሰብበት ቤተክርስቲያን መጥቶ ጌታን ከተቀበለ በኋላ ለመጠመቅ ፈቃደኛ እንደሆነ ገለጸልኝና ከተጠመቀ በኋላ በክርስቶስ ለማ

መን የቀሰቀሰህ የትኛው ጥቅስ ነው አልኩት ። አንድ ቀን ሲነበብ የሰማሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ያም የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፬ ከቁጥር ፲፪ ጀምሮ ነው ። ከዚያ እንደምንረዳው ጌታ ወደ ኤማሁስ መንደር ከሚሄዱት ሁሉ ደቀመዛሙርት ጋር አብሮ ይሄድ ነበር ። እነዚያም ደቀ መዛሙርት ወደ ሚፈልጉበት መንደር ከደረሱ በኋላ ጌታ ምንም እንኳ አብሯቸው ሊያድር ቢፈልግም እስቲ ጋብዙት ድረሰ ወደቤታቸው አልገባም እንዲገባ ከፈቀዱለት በኋላ ግን እነርሱ ቤት ገባ ። እንደኔ አገላለጽ በዚያ ክፍል ላይ ግሩም ሆኖ የተገለጸ ነገር ቢኖር የክርስቶስ ጨዋነት ነው ። እኔንም የእርሱ ተከታይ እንድሆን ያደረገኝ ጨዋነቱ ነው ፤ ክርስቶስ በልባችን በር ላይ በጨዋነት ቆሞ ያንኳኳል እስከምንከፍትለትም ይጠብቃል ፤ ኮሚኒስቶች ግን ባለጌዎች ናቸው ። በዛቻና በማስፈራራት በአንጐላችንና በልባችን ይገባሉ ፤ በግዴታ ከጧት እስከ ማታ የሚያሰሙትን ስብከት እንድንሰማ ያዙናል ። ይህንንም በት/ቤታችን ፣ በሬዲዮ ፣ በጋዜጦችም ፣ በሲኒማ ሁሉ ያሰራጩታል ፣ ማንም ፈቃደኛ ቢሆንም ባይሆንም ሃይማኖትን በመቃወም የሚያደርጉትን ንግግር ማዳመጥ አለበት ። ክርስቶስ ግን የሰውን የመምረጥ መብት አይጋፋም እርሱ በሚያስተምርበት ጊዜ «ብትወዱኝ ተከተሉኝ» አለ እንጂ ጉልበቱን አልተጠቀመበትም ። ታዲያ የእርሱን ትምህርት ከኮሚኒዝም ጋር ሳወዳድር በትምህርቱ ይበልጥ ሕይወትን አገኘሁ ። ይህ ወጣት ጌታን ካመነበት ጊዜ አንስቶ ወንጌልን ሌት ተቀን ያስፋፋ ነበር በኋላ ግን ተይዞ ታሰረ ። የማውቀው ነገር ቢኖር እስከ ፲፱፻፶፱ ድረስ በእስር ቤት መኖሩን ነው ። እስከ አሁን ታስሮ ይሆን ወይስ መልካም ገድል በመጋደል ላይ ይሆን

ወይስ ሩጫውን ጨርሶ የድልን አክሊል ለመቀበል ሄዶ ይሆን? እኔ አላውቅም ። ሁሉን የሚያውቀው ጌታ ግን ያውቃል ። የሩሲያ ክርስቲያኖች ጥሩ አማኖች ብቻ ሳይሆኑ ያመኑበትንም የሚያስፋፉ ጉበዝ ፣ ታማኝ፣ ሠራተኞች ናቸው ። ይህንንም ድካማቸውን በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአታቸው ተቸንክሮ ለሞተው ከጌታ ስቃይ ጋር ብናወዳድረው በጣም ቀላል ነው ይላሉ ።

## የክርስቶስ ወንጌል በባርነት ላሉ ነፍሳት ነፃነትን አወጀ

ለሩሲያኖች ወንጌልን እንደምንሰብክ ሁሉ በሩማንያ ላሉ ኮሚኒስቶችም እንሰብክ ነበር ። አስቀድሜ እንዳልሁ ኮሚኒስቶች የቤ/ክ/ትድገት ደጋፊዎች መስለው ብዙ ካወሩና ካስወሩ የክርስቲያኑም ሕዝብ በሃሰተኛ ተስፋ እንዲሞላ ካደረጉ በኋላ በርግጥ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ስደትን አስነሱ ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ታሰሩ ፣ ቤተክርስቲያኖችም ተዘጉ ፣ የክርስቶስን አዳኝነት መስበኩ እንደ ታላቅ ወንጀል ተቆጠረ ፣ በሩሲያ ባሉ ክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን መከራ እኛ በሩማንያ ያለነውም ቀመስ ነው ። እኔ ራሴ ከብዙ ክርስቲያን ወገኖቼ ጋር ታስሬ ነበር ። አብረውኝ ከታሰሩት ክርስቲያኖች አንዱ ስድስት ልጆቹንና ሚስቱን ትቶ ታስሮ የነበርና ምናል ባት ይህ ሰው ሚስቱን ሆነ ልጆቹን ተመልሶ የማየት እድል ላይገጥመው ይችላል ።

ወደዚህ ሰው ጠጋ ብዬ በክርስቶስ እንድታምን በማመንህም እንድትታሰር ያደረግሁህ እኔ ነኝና በእኔ

ላይ ማለት ይህን ለእሥራት ያበቃህን እምነት ስለነ ገርሁህ ጥላቻ አለህን? አልኩት ። በክርስቶስ እንዲያምን ወንጌልን ለርሱ በመስበኬ አመሰገነኝ ፡ ደስታው ቀድሞ ከነበረው በጣም ከፍ ያለ እንደሆነና እኔን ለማመስ ገን ቃል እንደሚያጥረው ነገረኝ ። እምነትን ለማስፋ ፋት ብዙ ጽሑፎችን እንበትን ነበር ፡ ከምንጠቀም ባቸው ዘዴዎች አንዱ በሽፋናቸው ላይ የካርል ማር ክስን ፎቶና ጥቅሶች በማሳየት ውስጡን ግን በመጽ ሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመሙላት ነበር ። በዚህም አገል ግሎታችን ሰዎች ብዙ ጊዜ ጌታን ወደማመን ይመጡ ነበር ፡ ከነጋዴዎችና ከሌሎችም ባለ ንብረቶች ንብረታቸ ውን ይነጥቁ የሃሳባቸው ተቃዋሚ የሆኑትን ሁሉ ያስሩና ያሰቃዩ ጀመር ፡ ሰላምን የሚሰብኩ ሲሆኑ ራሳቸው ይገድላሉ ፡ ምድርን ኤደን ገነት ለማድረግ የተነሱ ሕዝ ባቸውን በረሃብ ያሰቃያሉ ፡ ጭንቀት በዛ ፡ መከራ በረ ከተ ፡ በዚያ ጊዜ ይህን ሁሉ ያዩ ሰዎች እንዴት እግዚ አብሔር የፍቅር አምላክ ቢሆን ይህን ዓመጽ በድ ሃው ሕዝብ እንዲፈጸም ይፈቅዳል? በማለት በእግዚ አብሔር ላል ያጉረመርም ነበር ።

## እውነተኛ ክርስቲያኖች ወንጌልን ያስፋፋሉ

ክርስቲያኖች ይሰበሰቡ የነበሩት በግል ቤት ፡ በጫካ ፡ አንዳንዴም ከከተማ ወጣ ብለው ነበር ፡ አን ዳንዴም ገላጣ በሆነ አደባባይ ላይ በድፍረት ለሰዎች ወንጌልን ይሰብኩ ነበር ፡ ሚስቴን በአደባባይ ላይ መዝ ሙር ስትዘምር ከሚስቴ መዝሙር በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ይገቩ እሰብክ ነበር ፡ የኔ ሚስት ማላኮስ በሚ ባል ፋብሪካ በር ላይ ለተሰበሰበው የፋብሪካው ሠራ

ተኖች ትዘምርና ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ትመሰክርላ ቸው ነበር ፡ ከፋብሪካው ሠራተኞች ብዙዎቹ ኮሚኒ ስቶች ሕዝቡን ከእምነት ለማግለል የሚያደርጉትን ጥረት ስለተቃወሙ ብዙዎቹ ተረሸኑ ። መጥምቁ ዮሐ ንስ ጌታ ከመምጣቱ አስቀድሞ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ይሰብክ እንደነበር ዛሬም በዳግም ምጽአቱ ዋዜማ የሚኖሩ ታማኝ ክር ስቲያኖች የመጥምቁ ዮሐንስን ስብከት በመስበክ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡና በነፍሳት ዳኛ ፊት ለመቆም የሚያስችላቸውን መንገድ እንዲወስኑ ያው ጃሉ ። አንድ ጊዜ ጆርጂሁ ደጅ ለሚለው ጠ/ሚኒ ስቴር ከኃጢአቱ እንዲመለስና ክርስቲያኖችን ማሳ ደዱን እንዲያቆም ለመንገር ሁለት ክርስቲያን ወን ድሞች ወደቢሮው በድፍረት ገቡ ። ያም ጠ/ሚኒስቴር የሁለቱን ክርስቲያኖች ተግባር እንደድፍረት ስለቆ ጠረው ወህኒ እንዲያገቡዋቸው አዘዘ ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ይኸው ጠ/ሚኒስትር በጠና ታመመ እነ ዚያ ቆራጥ ክርስቲያኖች በልቡ ማሳ ላይ የዘሩት የወ ንጌል ዘር ፍሬን ሊያፈራ ጀመረ በተለይም «የእግዚ አብሔር ቃል ሁለት ልሳን ካለው ሰይፍ ይልቅ የተ ሳለ ነው» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በይበ ልጥ ያሰላስለው ጀመር ። ከዚህ በኋላ ይህ ሰው ቀድሞ ወህኒ አስገብቷቸው የነበሩትን ክርስቲያኖች አስጠ ርቶ የጀመሩለትን ስብከት እንዲጨርሱለት ነገራቸው ። ወዲያው በጌታ በኢየሱስ አመነ ። «ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋል» በሚለው ቃል ተነክቶ ኃጢአቱን ተና ዘዘ ፤ ስለአለፈው ጥፋቱ አለቀሰ ፤ ይህን ባደረገ በጥቂት ጊዜ በፈሰሰው በጌታ ደም ለሚያምኑ ሁሉ ወደሆ ነው ወደ እግዚአብሔር ሄደ (ሞተ) ክርስቲያኖች የሚ ጠብቃቸውን እያወቁ የወንጌልን ዘር ይዘሩ ነበር ።

ጌታም በዚህ ሁሉ ከበረ ። ኮሚኒስቶች እነዚህ ለጌታ ቸው ክብር የሚቆሙ ክርስቲያኖችን የሥራቸውና የዓ ላማቸው ተቃዋሚዎች መስለው ስለታዩዋቸው ከማ ንኛውም ጊዜ ይልቅ ወንጌላውያንን እያደኑ ያሥሩ ጀመር ። ይህች አነስተኛ ቤ/ክ/ ከሥሯ ተነቅላ ካልጠ ፋች ትምህርታቸው በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እን ደማይኖረው ተረዱት ። ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ለማ ሰርና ለማሰቃየት ቢችሉም በእግዚአብሔር ላይ ያላ ቸውን እምነት ሊያስሩ አይችሉም ። ጳውሎስ እንዲህ አለ ፣ «እኔ ብታሰር እንኳ የእግዚአብሔር ቃል አይታ ሰርም» አዎ ፣ ይህማ በመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እለት እለት ይስፋፋ ብዙም ተቀባዮችም ይኖሩት ነበር ።

ምንም እንኳ የክርስቲያን ተቃዋሚዎች የሚያ ደርጉትን ማጭድና መዶሻ ያለበትን መለዮ ቢያደር ግም ከኮሚኒስቶች ወታደሮችና ከሚስጥር ፖሊሶች ውስጥ ብዙ በጌታ የሚያምኑ ነበሩ ። በክርስቲያኖች ላይ ክፉ ትእዛዝ ሲወጣ አስቀድመው ይነግሩንና እን ዘጋጅ ነበር ፣ እነዚህም ኮሚኒስቶች ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቲያኖች ያላቸው ፍቅር ታላቅ ነው ፣ እኔ ራሴ ማንም በማያውቀው በሚስጥር በአንድ ደባቃ ቦታ ታስሬ በነበረበት ጊዜ ብዙዎች እንደሞትኩ ገም ተው ነበር ፣ አንድ ክርስቲያን የነበረ ዶክተር ግን እኔ ያለሁበትን ቦታ ፈልጎ ለማግኘት ተነሳ ፣ ይህንንም ምኞቱን ለመፈጸም ከሚስጥር ፖሊሶች ጋር መተባ በር አስፈለገው ሆኖም ስላገኘው በዚሁ ክፍል ውስጥ በዶክተርነት እንዲያገለግል አመለከተ ፣ ወዲያው ከሚ ስጥር ፖሊሶች ጋር በመተባበር በዶክተርነት ይሠራ ጀመር ። ቀድሞ ማለት ከሚስጥር ፖሊሶች ጋር ሳይተ

ባበር ያውቁት የነበሩትን ክርስቲያኖች የሚስጥር (ፖሊሶችን የማዕረግ ልብስ ለብሶ ሲያዩት ከፍተኛ ፍራቻ አደረባቸው ። በመንገድም ሲያዩት ይሸሹት ነበር ፤ ያ ክርስቲያን ወንድም ግን ይህን ቢያደርግም ስለእኔ ትክክለኛውን ነገር ለማወቅ መሆኑን ብዙዎች አልተረዱትም ። ይህ ሰው የሚስጥር ፖሊስ አባል ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ለብዙ ጊዜ ሲጠይቅና ሲያስጠይቅ ከሰነበተ በኋላ ተስፋ ወደ መቁረጫው ገደማ በአንድ ጨለማ በሆነ ጠባብ ጉድጓድ (አዘቅት) ውስጥ ተጥዬ አገኘኝ ። በሕይወቴ መሆኔንም ለማወቅ በስሜ ጠራኝ ። እኔም በሕይወት መሆኔን በደከመና በለሰለሰ ድምጽ መለስኩለት ። ያም ዶክተር ባለፉት ስምንት ተኩል የእሥራት ዘመኔ ለመጀመሪያ ያገኘሁት ክርስቲያን ወንድሜ ነበር ። በሕይወት መሆኔን ከተረዳ በኋላ ሞቷል ብለው እርማቸውን አውጥተው ለነበሩት ክርስቲያን ወንድሞቼና እህቶቼ ስለኔ መኖር ትክክለኛውን ገለጸላቸው ።

በኋላም በ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. በአይዘንአወር ክሩቼብ አዛዥነት እኔና ሌሎቹም በተለያየ ቦታ ታስረው የነበሩ ሁሉ ተፈታን ። ቀድሞ ሞቷል ብለው እርማቸውን ያወጡ ክርስቲያኖች በሕይወት መኖሬንና የእሥራት ጊዜዬን ጨርሼ እንደወጣሁ ሲሰሙ ደስታቸው እጥፍ ድርብ ሆነ ። ይህ ክርስቲያን ዶክተር በእግዚአብሔር ሰውን ከጭንቀት ለማዳን እንደሚላክ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው የምገምተው ። ምክንያቱም ይህ ሰው እኔ ያለሁበትን ቦታ ለማወቅ ጥረት ባያደርግና ከዚያም በላይ ተረስቼ እንዳልቀር ባያስታውስ ኖሮ ምናልባት ዛሬ ከሕያዋን ምድር አልገኝም ነበር። ስለኔ ሕይወት ያደረገው ተጋድሎ ታላቅ ነው ። ጌታ

ብድሩን ይስጠው ፤ ዛሬም ቢሆን ስለ ክርስቲያኖች በጉነት የሚጨነቁ በሚስጥር ፖሊሶች ውስጥ ደጋፊዎች አሉን ፤ እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ የሚስጥር ፖሊሶች ተባባሪዎች ቢሆኑም በሚስጥር ደግሞ ወንጌልን የሚያስፋፉ ክርስቲያኖች ናቸው ፤ አንድ ቀንም የሁሉ ዳኛ የሚሆን ጌታ ዋጋቸውን በግልጽ ይከፍላቸዋል ። ምንም እንኳ ከሚስጥር ፖሊሶች ውስጥ በክርስቲያኖች ሊመጣ ያለውን ስደት አስቀድመው ለኛ በመንገር እንድንጠነቀቅ የሚያደርጉን ቢኖሩም ከኛ መሐል ክርስቲያን የነበሩና አሁን ግን ለጌታ ጀርባቸውን የሰጡ ከሐዲያን ክርስቲያኖች አጋልጠው የሚሰጡና ከዚህም ሌላ ጌታውን በገንዘብ ተደልሎ የሸጠውን የይሁዳ ተከታዮች የክርስቲያኖችን መጥፋት ከሚፈልጉ ሰዎች ገንዘብን በመቀበል ክርስቲያኖችን የሚያሳስሩ ነበሩ ፤ ነገሩ በጣም የሚገርም ነው ። እኛን ለማሰር ለመግረፍ ለማሰቃየት ሥልጣን ካላቸው ከሚስጢር ፖሊሶች ውስጥ የተጣለባቸውን አደራ በመናቅ ክርስቲያንን ማሳደድ ዋና ተግባራቸው ሲሆን እነሱ ግን ክርስቲያኖችን ሲደግፉ ወንድሞች ከምንላቸው ከክርስቲያኖች መሃል ግን ለኛ መኖር ተቃዋሚ የሆኑ ተነሱ ፤ ቢሆንም በታማኝነት በምናደርገው አገልግሎት ጌታ ይከበራል ።

## ምዕራፍ ፬

ይህን በመሰለ መንገድ እስከ የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ድረስ ወንጌልን በታማኝነት አስፋፋ ነበር ፣ አንድ እሁድ ቀን ግን እንዲህ ሆነ ወደ ቤ/ክ/ ስሄድ ሳለሁ በድንገት በሚስጥር ፖሊሶች ተይዤ ወደመኪናቸው እንድገባ ተደረግሁ ። አራት ሰዎች ከመ ኪናው ወጥተው ወደ ውስጥ ወረወሩኝ ። በዚያች እሁድ የታሰርኩት እኔ ብቻ ሳልሆን በተለያየ ሥፍራ የነ በሩ ክርስቲያኖችንም አስረዋቸው ነበር ፣ ከዚያ በኋላ እኔ ራሴ እንኳ ወደማላውቀው ስፍራ ተወሰድሁ ። ለስም ንት ተኩል ዓመት ማንም ልኑር ልሙት የሚያውቅ አል ነበረም ፤ አንድ ቀን የሚስቴን ልብ በሃዘን ሊሰብር የፈለገ ወታደር ሄዶ እኔ እንደሞትኩና በቀብሬም ሥነ ሥርዓት ላይ እንደነበረ ነገራት ። ይህ ምን ዓይነት መርዶ (ሃዘን) እንደሆነ እናንት ባሎቻችሁን ወይም ሚስቶቻችሁን የምትወዱ አስቡት ፣ በዚያች እኔ በታሰርኩባት ዕለተ ሰንበት ብዙ ክርስቲያኖች በሚስጥር ከሚያደርጉት የስብሰባ ቦታ ተይዘው ታሰሩ ። የታሰሩት የቤተ ክርስ ቲያን መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ምዕመኑ ፣ ሕፃኑ ፣ ጐልማ ሳው ፣ አሮጌቶችና ሽማግሌዎች እንዲሁም ጡት ያል ጣለ ልጅዋን የያዘች እመጫት እንኳ አልቀረችም ፤ በክርስቲያኖች ላይ ይህ ነው የማይባል መከራ ደረሰ ፣ ቢሆንም ክርስቲያኖች ያን ሁሉ በትእግስት ቻሉ ።

## የማይነገር ፍዳ

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በጋሉ ቢላዎችና ሹል ብረቶች እየተሰቃየ ታስሮ ነበር ። በታሰረበት

ጠባብ ክፍል ውስጥ በቁቦ ተደርገው መጠን ስፍር የሌላቸው የተራቡ አይጦች እንዲገቡ ይደረጋል ። ይህ ሰው ለመተኛት ፈጽሞ ጊዜ የለውም ፣ አይጦች እንዳ ይበሉት ለሕይወቱ መከላከል ነበረበት ። ይህን በመ ሰለ መንገድ ለሁለት ሣምንታት ያህል እንዲሰቃይ ተደረገ ። ይህ ሁሉ ስቃይ በዚህ በተለየ የቤተ ክርስቲ ያን መሪ የተፈጸመበት ክርስቲያኖች የት ቦታ እንደ ሚገኙ ለፖሊሶች በመንገር ሌሎች ክርስቲያን ወን ድሞቹን አጋልጦ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው ። ይህ ቆራጥ ክርስቲያን ወንድሞቹን አጋልጦ ከመስ ጠት ይልቅ ርህራሔ በሌላቸውና ሰው ለማሰቃየት ብቻ የተፈጠሩ በሚመስላቸው ሰዎች እጅ መሠቃ የትን መረጠ ፣ በዚህ ሁሉ ስቃይ ፍንክች እንዳላለ ባዩ ጊዜ ምናልባት ልጁን እፊቱ ብናሰቃየው ስለልጁ ስቃይ ሲል ይናገር ይሆናል በማለት የ፲፬ ዓመት የሆ ነውን አንድ ልጁን እፊቱ አምጥተው ይገርፉት ልዩ ልዩ በሆኑ ስቃዮችም ያሰቃዩት ነበር ፣ ያም ሰው የል ጁን መደብደብ መሰቃየት ሲያይ እንደ እብደት አደ ረገው ። ልጁ የሚገረፈው ግርፋት እጥፍ ድርብ ሆኖ ይሰማው ነበር ። በዚህ ጊዜ ተስፋ በመቁረጥና በመበሳጨት ልጁን ፣ አሌክሳንደር አንተን እፊቴ ሲያ ሰቃዩህ ለማየት ስለማልፈልግ የሚፈልጉብኝን መና ገሬ ነው አለው ። ልጁም አባቱን መለስ ብሎ ትንንሽ አይኖቹን ክብልል እያደረገ «አባባ ለምን ይህን ልታ ደርግ ታስባለህ? ሕያው ሆኜ የዚያ ሃይማኖቱን የካደ ሰው ልጅ ከምባል ወደናፈቅሁት ጌታዬ መሄድ መር ጬአለሁና ታገስ» ካለው በኋላ በገራፊዎች በደረሰ በት ስቃይ ሞተ ። አባትየውም የወለደው ልጅ ምን ያህል የጌታን ፍቅር የተጠማ መሆኑን ካየ በኋላ የራ ሱም እምነት ከመቸውም ጊዜ ይልቅ በጣም ከፍ ያለ

ሆነ ፣ የታሰርንበት ካቴና ከውስጥ በኩል ብዙ ሚስ ማሮች ነበሩበት ። ይወጉን ስቃያችንም እንዲበዛ ያደ ርጉን ነበር ። ክርስቲያኖች የዝቅዝቅ እየተሰቀሉ ይገ ረፋሉ ። እበረዶ ቤት ውስጥ ይጥሉንና በቅዝቃዜው ጽናት ወደሞት አፋፍ ስንደርስ ማለት የመሞትን ምል ክት ስናሳይ አውጥተው ለጥቂት ጊዜ ጸሐይ ያሞቁ ንና መልሰው እዚያው በረዶ ውስጥ ይጨምሩናል፣ ይህንንም በአንድ ቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ በመደጋገም ያደርጉ ነበር ። ይህ ብቻ አልነበረም ። በቁመታችን ልክ በሆነ ቁምሣጥን ውስጥ እንገባለን ። ያም ቁም ሳጥን ከግራና ከቀኙ ሰውነትን ለመዘንጠል በሚችሉ በጣም በተሳሉ ቢላዎች የተሞላ ነው ። ራሳችንን እንኳ ከአንድ ጐን ወደሌላው ለማዛወር አንችልም ፤ ያን ለማድረግ ብንደፍር እንኳ እነዚያ የተሳሉ ቢላዎች ሰውነታችንን በጭከና ይበጡት ነበር ። ከስቃይ ፋታ የምናገኘው ቀጥ ብለን የቆምን እንደሆነ ብቻ ነው ፤ ታዲያ ሰው እስከመቼ ቆሞ ይችላል ? ልንቀመጥ አንችልም ፤ ሌላ ቀርቶ ትንሽ ቅስቅስ ካልን ያለንበት ሳጥን በደም እስ ኪጨማለቅ ድረስ ሰውነታችን በነዚያ ስል ቢላዎች በመዘንጠል ይደማ ነበር ፤ አይ ስቃይ! በዚህ ሁሉ ስቃይ የክርስቲያኖች አምላክ አብሮን ነበር ።

ገራፊዎቹ አንዳንድ ርህራሔን ሳያሳዩ ክርስቲያ ኖችን ሲያሰቃዩ «እኛ ዲያብሎሶች ነን» እያሉ በመ ጮህ ነው ። ታዲያ የሚያስደንቀው ነገር ገራፊዎች ፊታቸውን ሲያጨልሙ ተገራፊዎች ግን ፊታቸውን በስማያዊው ደስታ ፈክቶ ማየቱ ነበር ። «እኛ ውጊያ ችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከጨለማ ገዥዎችና ከክፋት ሠራዊት ጋር ነው ።» ኮሚኒዝምን ከክፋት መን ፈሳውያን ሠራዊት የመጣ ትምህርት እንጂ በቀጥታ

ከሰው የመነጨ አይደለም በርግጥ ይህ ትምህርት የእግዚ አብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ከክፉት የመነጨ ኃይል ነው ፤ ሊገለበጥ ወይም ሊሸነፍ የሚችለውም በሥጋ ክንድ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው ።

አንድ ቀን አንዱን ወታደር ለመሆኑ እኛ እንደ ዚህ ስንሰቃይ ምንም ሃዘን አይሰማህም? ስል ጠየቅ ሁት ፤ «እንቁላሉን ለመጥበስ ሽፋኑን መስበር አለብን» የሚለውን ጥቅስ ነገረኝ ፤ እኔም መልሼ ይህን የጠቀስ ከውን ጥቅስ እኔ ራሴ ሌኒን እንደተናገረው አውቃለሁ ፤ ታዲያ እኮ ብታስብበት በሰውና በእንቁላል ትልቅ ልዩነት አለ ። እንቁላሉን ብትሰብሩት ብትጨፈልቁት እሳት ላይ ብትጥሉት ስሜት ስለሌለው ምንም አያ መውም ፤ እናንተ ግን የምታሰቃዩት እኛን እንደናንተ የሚያመንን ሰዎች ነው እኮ አልኩት ፣ ሰው ከሌሎች ነገሮችና ከእንስሳት ምንም ለውጥ የለውም በሚለው የማቴሪያሊስቶች ፍልስፍና ጭንቅላታቸው ተሞል ቷል ፣ ሁል ጊዜም እግዚአብሔር የለም ፣ ለክፉም ሆነ ለደግ ብድር መከፋፈያ የሆነች ይህች ዓለም ብቻ ናት እንጂ መንፈሳዊ ዓለም እንደሌለ ሊያስረዱ ይሞክራሉ ። አንድ ቀን አንዱ «የማላምንበት አምላክ እስከዚህ ሰዓት አደረሰኝ ። የልቤን ጭከና በነዚህ ክርስቲያኖች ላይ ለመግለጽ ስላበቃኝ በጣም አድርጌ አመሰግነዋ ለሁ» ሲል ሰማሁት ፤ ይህንንም ሲናገር በልቡ ያለው ጭከና ጎልቶ በፊቱ ላይ ይነበብ ነበር ፤ ምናልባት አዞ ሰውን እንደበላ ቢነግረኝ በጣም አዝናለሁ ፣ ቢሆንም አላደንቅም ። ምክንያቱም ተፈጥሮው ራሱ እንደዚያ እንደሆነ ስለማውቅ ነው ፤ ነገር ግን እንደኔ ሰው የሆነ እንደኔ የተሟላ ስሜት ያለው ሰው እኔን ማሰቃየት

እንዴት ደስ ሊለው እንደቻለ ገርሞኛል ፤ ሰብአዊ ፍጡር የሰውን ቅርጽ ይዞ የአውሬን ጭካኔ ይዞ ቢገኝ አያሳዝንም? ያሳዝናል ። ከዚያ ሰው ንግግር የተረዳሁት ሞራለ ቢስ መሆኑን ነው ። ኮሚኒዝም ምንም እንኳ ስለሞራል አብዝቶ የሚናገር ቢሆንም እንኳ እውነተኛውን የሰብአዊነትን ሞራል ከልባቸው ፍቆታል ። የምናምነውንም አዳኝ የክርስቶስን ወንጌል ለመቀበል እንደማይሹ ሁሉ እኛም ለኮሚኒዝም ማለት ኮሚኒስቶች መልካም ለሚሉት ትምህርት በልባችን ውስጥ ቦታ አልነበረንም ፤ ክርስቲያኖች በመስቀል ላይ ይታሰሩና ይሰቃዩ እንደታሰሩም ይደበደቡ ነበር ፤ ያንም የተሰቀሉበትን መስቀል በመትከል እዩ የናንተ ክርስቶስ እንዴት ያምራል? እንዴት የሚያስደስት ስጦታ ከሰማይ ይዞላችሁ መጣ? በማለት ያሾፉባቸው ነበር ፡ እንደዚህ ከተሰቃዩት የእምነት አርበኞች አንዱ ቄስ ሚላን ሃይሞቢኪ ነበሩ ፡ የታሰሩ ክርስቲያኖች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ በስማቸው ለማወቅ አዳጋች ነው በየቀኑ የእስር ቤትን ሕግ አፍርሳችኋል በመባል ከመኝታ ቤታቸው እየጠሩ ይገረፋሉ ። ይህ ቄስ ሚላን ግን ብዙ ጊዜ ስለሌሎች ማለት ለአንድ ሰው ጥፋት መደበኛ ቅጣት ፳፭ ጅራፍ ነው ። ብዙዎች ይገረፉ ነበር ፤ አንዱ የሚገረፈውን ግርፋት ሌላው ይገረፍለታል ፤ ይህ ግን ምን ዓይነት ፍቅር እንደሆነ ለመግለጽ ያዳግተኛል ።

አንድ ጊዜ እንዲት ልጃገረድ ወንጌልን ለወጣቶችና ለሕፃናት ያስተማረች መሆኑ በብዙ ምስክሮች ስለተረጋገጠባት እስራት ይገባታል በማለት ተፈረደባት ፤ ሰርጓም በቅርብ እንደሆነ ከተረዱ በኋላ ነገሩን ይበልጥ አሳዛኝ ለማድረግ በሰርጓ እለት ሊያስ

ሯት አቀዱ ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የዚያች ልጅ ሰርግ ደረሰ ፣ የሙሽራ ልብሷን ለብሳ ከሙሽራዋ ጋር ጐን ለጐን ተቀምጣ ሳለ በድንገት በሩ ተከፈተ ። ወዲያው ፖሊሶች ገቡና የያዙትን ካቴና እጅዋ ላይ አጠለቁላት ፤ ወንጌልን መስበኳ በብዙ ምስክሮች ስለተረጋገጠባት የረጅም ጊዜ እሥራት እንደሚጠብቃት አረዷት ። ወደ ሙሽራዋ ዞር ብላ እያየች ዛሬ በዚህ ቀን የሰማያዊው እጮኛዬ ቀለበት ስለደረሰኝ አምላኬን በጣም አመሰግነዋለሁ ካለች በኋላ የታሰረችበትን ካቴና ሳመች ። ወታደሮቹም ምንም እንኳ በነገሩ ልባቸው ቢነካም ትእዛዝ ነውና እያመናጨቁ ይዘዋት ሄዱ። ለአምስት ዓመታት በብዙ መከራ ስትሰቃይ ከቆየች በኋላ በአምስተኛው ዓመት እንድትፈታ ተደረገ ፤ ያ ታማኝ እጮኛዋም ለአምስት ዓመታት በታማኝነት ከጠበቃት በኋላ ተገናኝተው እንደገና የሠርግ በዓላቸውን አከበሩ ።

## ብሬንዎሽንግ ምን ዓይነት ነው

ምናልባት አንዳንዶች ስለ ብሬን ዎሽንግ የሰሙት በኮሪያና በቬትናም ጦርነት ጊዜ ብቻ ይሆናል ግን እንዴት እንደሆነ አያውቁም እኔ በእስር ቤት ብዙ የተሰቃየሁ ብሆንም እንኳ ከሌሎች ይልቅ በጣም የከፋ ሥቃይ ነው ፤ ክርስቲያኖች ብሬን ዎሽድ ሲደረጉ በየቀኑ ለ፲፯ ሰዓት ያህል እየጮሁ ፣

ኮሚኒዝም ጥሩ ነው ፣
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው

ኮሚኒዝም ጥሩ ነው
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው

ክርስትና ግን መጥፎ ነው

ክርስትና ግን መጥፎ ነው እንዲሉ ይደረጉ ነበር ። ብዙ ሰዎች በዚህ ስቃይ አማካይነት ሞቱ ፤ እኔም አራት የጀርባ አጥንቶቼና ሌሎችም ብዙ አጥንቶቼ ተሰበሩ በጋለ ብረት የተወጋሁት ለሌሎች ስለነገሩ እውነተኛነት ማስረጃ ሊሆን የሚችሉ ፲፰ ጠባሳዎች በሰውነቴ ላይ አሉኝ ። በኦስሎው ያሉ ዶክተሮች ስለ ጤንነቴ ሙሉነት ምርመራ ካደረጉ በኋላ በሰውነቴና በአጥንቶቼ የደረሰብኝ ጉዳት እንዲሁም በዚህ ስቃይ የለከፈኝን የሳንባ በሽታ ጠንቅ ባዩ ጊዜ ይህ ምንም ምክንያት ልሰንጠው የማንችለው ራሱን የቻለ ንጹህ ተአምር ነው አሉኝ ። በእርግጥ እንደሜዲካል ሳይንስ አባባል በሽታዬና የደረሰብኝን ስቃይ ለሞት የሚያበቃኝ ነበር ። ዳሩ አምላካንች የተአምራት አምላክ ነውና እስከአሁን ጠበቀኝ ፤ ምናልባት በዚያ ስቃይ ሞቼ ብሆን ኖሮ ዛሬ እናንተ ድምጼን አትሰሙም ነበር ነገር ግን የክርስቲያኖችን የእምነት ገድል ላላያችሁትና ላልሰማችሁት ለናንተ አውጅ ዘንድ ኃይል አምላክ አዳነኝ ።

## ከእሥር ቤት ስለ መፈታት

ለስምት ተኩል ዓመት በእስር ቤት ነበርኩ በደረሰብኝ ሥቃይ ብዙ ክብደት ቀነስኩ ፤ ብዙ አስቀያሚ ጠባሳዎች በሰውነቴ ነበሩ ፤ መልኬ ገርጥቶአል ፤ አጥንቴ ገጦ

አል ፤ የጀርባ አጥንቶቼ ስለተሰበሩ ጐብጬአለሁ ፤ ይህን ሁሉ ስቃይ አልፌ በ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. የተወሰነልኝን የእሥራት ዘመን ጨርሼ ከእሥር ቤት ወጣሁ ። ወደ ቀድሞው ጥፋቴ ማለት ወንጌልን እንዳልሰብክ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ ዳሩ ከጥቂት ጊዜ እረፍት በኋላ ከበሽታዬ ሳገግም እንደገና ወንጌሉን በአንድ ቦታ ስሰብክ እጅ ከፍንጅ ስለተያዝኩ እንደገና ለአምስት ተኩል ዓመት ተፈርዶብኝ ወህኒ ገባሁ ፤ የሁለተኛው የእሥራት ጊዜዬ ከመጀመሪያው በብዙ መንገድ የከፋ ነበር ።

## እኛ እንሰብካለን እነርሱም ይደበድቡናል ።

የመጀመሪያዎቹን ስምንት ተኩል ዓመታት ጨርሼ ስወጣ ወንጌልን እንዳልሰብክ አስጠንቅቀውኛል፤ እንደገና ወንጌልን ስሰብክ ብገኝ የሚደርስብኝንም አውቃለሁ ፤ ዳሩ እኔና አብረውኝ ተፈትተው የነበሩት ክርቲያኖች የተነገረንን ማስጠንቀቂያና ዛቻ ረስተን እንደገና ወንጌልን ለመስበክ ተዘጋጀን ። አብረውን ለታሰሩት እስረኞችም ወንጌልን እንሰብክ ነበር ፤ አንድ ቀን አንድ ክርስቲያን ወንድም አብረውት ለታሰሩት እስረኞች ወንጌልን ሲሰብክ ስለተገኘ ወታደሮቹ መጥተው ወደመግረፊያው ክፍል ከወሰዱት በኋላ ክፉኛ ደበደቡት ፤ ደም ከሰውነቱና ከራሱ ይጐርፍ ነበር ፤ አጥንቶቹም ተቀጠቀጡ ፤ በዚህ ሁሉ ስቃይ እንደ ሬሣ ተዘረጋ ። ገራፊዎቹም የሞተ መስሏቸው ጥለውት ሄዱ ፤ ወዲያው ያ ሰው ከወደቀበት ተነስቶ ወደ እስረኞቹ መጥቶ የደከመ ሰውነቱን ማሳረፍ ሲገባው ወንድሞቼ! ቅድም ገራፊዎቹ ሲወስዱኝ ምን ላይ ነበር

ያቆምኩት አላቸው ፤ ያቋረጠበትንም ቦታ ከነገሩት በኋላ ስብከቱን ቀጠለ ፤ እነሱ ይገርፋሉ ፤ ክርስቲያኖች ይሰብካሉ ፤ እነሱ መልካም ገራፊዎች ናቸው ፤ እኛም መልካም ሰባክያን ነን ። በአሜሪካና በሌሎችም አገሮች ብዙ ወንጌላውያን የሚሰለጥኑባቸው ት/ቤቶች አሉ ፤ እነዚህ እስረኞች ግን ስለወንጌል ወይም ወንጌልን ስለመስበክ ብዙ ችሎታ ሳይኖራቸው የሚሰብኩት ስብከት ኃይል ያለው ነበር ፤ በስብከታቸው ብዙ ነፍሳትን ወደ ጌታ ይመልሳሉ ፤ ታዲያ ለዚያም ዋጋ ይከፍሉበታል ፤ ዋጋውም መታሰር ፣ መገረፍ ፣ መሰቃየትና መገደል ናቸው ። በዚህ ሁሉ ክርስቲያኖች በጨለማ ላሉ ነፍሳት የወንጌልን ብርሃን ያበሩ ነበር ።

ግሄራ በሚል ስፍራ ባለው እስር ቤት ግሬኩ የተባለ ክርስቲያን ብዙ አሰቃቂ በሆኑ የሥቃይ ዓይነቶች ፍዳውን ያይ ነበር ፣ ብዙ ይደበድቡትና ሰውነቱን ስቶ ዝሎ ሲወድቅ ሕክምና ያደርጉለታል ፤ ለጊዜው መልካም ምግብ እየቀያየሩ ያበሉታል ፤ ሰውነቱ ከበረታ በኋላ ግን መልሰው ያሰቃዩታል ፣ ይህም የሚደረገው ሬክ በተባለው ሰው አዛዥነት ነበር ፤ ይህም ሰው ለዚያ በርሱ ለሚሰቃይ ክርስቲያን ወንድም በማሾፍ አነጋገር እንዲህ አለው ፤ ታውቃለህ? «እኔ አምላክ ነኝ በናንተ ላይ ሙሉ ስልጣን አለኝ ከኔ በላይ ግን ማንም የለም ልገድላችሁ ብፈልግ እገድላችኋለሁ ላድንችሁም ብወድ (የሕይወታችሁ ጌታ ነኝ) ላድናችሁ እችላለሁ ስለዚህ እኔ በሕይወታችሁ ሙሉ ሥልጣን ያለኝ የሕይወታችሁ ጌታ ነኝ» ። ያም ክርስቲያን እንዲህ ሲል መለሰለት «ለመሆኑ የምትናገረውን በርግጥ ታስታውሳለህ? አስተውለኸው ወይም ተረድተኸው ቢሆን ኖሮ በጣም ደስ ባለኝ ነበር ፣ ግን

አላስተዋልኸውም ። እወቅ! የሁሉ በላይ የሚሆን እግ ዚአብሔር አለ ። እርሱም አንተን ይህን ፍጥረተ ዓለም እንድትገዛ ፈጥሮሃል ማለት የአምላክነት ባህርይ ተሰ ጥቶሃል ታዲያ እኮ እሱ ያን የአምላክነት ስልጣን ያሰ ጠህ እንድትታዘዝ አልነበረም ፤ አንተ በእርግጥ አም ላክ ነህ እግዚአብሔር አንተን ይህን ሥልጣን የሰ ጠህ ግን ለመልካም ነበር ። አምነህ የመለኮታዊው ባህርይ ተካፋይ ለመሆን ተፈጠርህ እንጂ ለማሰቃ የት አይደለም» ። ሳውል የጠርሴሱ በፊቱ ይገደል የነ በረውን የእስጢፋኖስ ሰማዕቱን ምስክርነት ለማስማት ቸል እንዳለ ሁሉ ይህም ሰው የዚያን የክርስቲያን ምስክርነት አሾፈበት ፣ ዘበተበት ፣ ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ያ የሚሰቃየው ክርስቲያን ምስክርነት ዋጋ ያለው መሆኑን ተረዳ ፤ እራሱ በጌታ የሚያምን ክርስቲያን ሆነ።

በዚህ ሁሉ ስቃይ የተማርነው ትምህርት ነፍስ የሥጋ ገዢ ፣ አለቃ መሆንዋን ነው ፤ ነፍሳችን ሁሉን በሚችል አምላክ መንፈስ ስለምትበረታ ይህን ሁሉ ስቃይ የምንታገስበት ኀይል ሰጠን ፤ በዚያን ጊዜ ብቻ ችንን ሳንሆን የሚወደን አምላካችንም የመከራችን ተካፋይ ነበር ፤ አንድ ጊዜ አንድ ክርስቲያን የሞት ፍርድ ተፈረደበት ሳለ ከመሞቱ አስቀድሞ በአንድ መሳሪያ በያዘ ወታደር አጃቢነት ሚስቱንና ልጆቹን እንዲጐበኝ ተፈቀደለት ። ወደ ቤቱም ሄዶ የሚስቱንና የልጆቹን ጤንነት ከጠየቀ በኋላ ሊሰናበት ሲነሳ ሚስቱን እንዲህ አላት ። «ሚስቴ ሆይ ይኸውና የሞት ፍርድ ተፈርዶብኛል ። ሞት ለእኔ የከፋ ነገር ሳይሆን ከማይሻል ወደሚሻል ዓለም መረማመጃ ድልድይ ነው ። ወደጌታ እንደምሄድ ስለማውቅ በጣም ደስተኛ ነኝ ። ሚስቴ ዛሬ እንድታውቂልኝ የምፈልገው ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ ሥቃይ ያበቁኝ ኮሚኒስቶች

ቢሆኑም የሚያደርጉትን ስለማያውቁ በነርሱ ላይ ምንም ጥላቻ የለኝም ። አንቺንም የምለምንሽ ነገር የባሌ ገዳዮች እያልሽ በነሱ ላይ ጥላቻ ወይም ቂም እንዳይኖርብሽ ነው ፤ በሰማይ በአምላካችን ዙፋን ፊት እስክንገናኝ ድረስ ደህና ሁኚ» ብሎ ሚስቱንና ልጆቹን ስሞ ወደ ሰርግ ቤት እንደሚሄድ ሁሉ ደስ እያለው ወደ መገደያው ሲሄድ ነገሩን ሁሉ ልብ ብሎ ያዳምጥ የነበረው ወታደር በነገሩ ልቡ ተነካ ። ይህንንም ታሪክ የነገረኝ ያ ወታደር ከዚያች ቀን ጀምሮ ክርስቲያን መሆኑ ስለታወቀበት ወህኒ እንዲገባ ከተፈረደበት በኋላ አብሮኝ በእስር ቤት በነበረበት ጊዜ ነው ።

ፒርጉ አኬና ፡ በሚባል እስር ቤት ደግሞ አንድ ማቼቢክ የተባለ የ፲፰ ዓመት ወጣት ታስሮ ነበር ፤ ከሥቃዩም የተነሳ ክፉኛ የሳንባ በሽታ ለከፈው ። ወላጆቹም የልጃቸውን መታመም ሲሰሙ ምናልባት ያድነው እንደሆነ በማለት ጥቂት ብልቃጥ ስተርፕቶማሲን ላኩለት ፤ ያም መድሃኒትን የተቀበለው ኦፊሴር ልጁን በእስር ቤት አስጠርቶ እንዲህ አለው «አንተ አሁን ገና ምኑንም ያላየህ ወጣት ነህ ። ከእስር ቤት ልትወጣና እንደጓደኞችህ ይህን ሃይማኖት ትምህርትህን ልትቀጥል ይገባሃል ። በሌሎች ቦታ ያሉ ክርስቲያን ወንድሞችህ እንኳ እምነታቸው እንደማይጠቅም ስለተረዱ ሁሉም እርግፍ አድርገው ትተውታል ። ይኸውልህ እነዚህ ከዘመዶችህ የተላኩ በሽታህን ባንዴ ድራሹን የሚያጠፉልህ መድሃኒቶች ናቸው ፣ ዳሩ አለቆቼ ለምን ሰጠኸው ብለው እንዳይቆጡኝ ስለምፈራ አልሰጥህም ፤ ልሰጥህ ብችል እንኳ የሌሎች ያልታሰሩ ክርስቲያኖችን አድራሻ ከሰጠኸኝ በኋላ ነው ፤ ያኔ ለምን ሰጠኸው ቢሉኝ ግን የምፈልገውን የክርስቲያኖችን

አድራሻ ስለነገረኝ ነው ለማተት ምክንያት ይኖረኛል ፤ ስለዚህ እባክህን ለወጣትነት ጊዜህ እዘንለትና በድብቅ ወንጌልን የሚሰብኩትን የክርስቲያኖች አድራሻ ስጠኝ» ያም ወጣት ይህን ወንጀል በወንድሞቹ በክርስቲያኖች ላይ ፈጽሜ ከእስር ቤት ከምወጣና ሁል ጊዜ ከዳተኛነቴ ትዝ ሲለኝ ሳዝን ከምኖር በዚህ እስር ቤት ውስጥ በያዘኝ በሽታ ተሰቃይቼ መሞትን እመርጣለሁ ፤ ያም ኦፊሴር ስማ! በዕድሜ ካንተ የሚበልጡ ሰዎች እንኳ ክርስቲያንነታቸውን ትተው የኛ ተባባሪዎች በመሆን የሚስጢር ፖሊሶች ደኃፊዎች ሆነዋል ። ነገ አንድ ነገር ብታደርግ እንኳ አንተን አሳልፈው ከመስጠት አይመለሱም ። እነሱስ ብዙ አይተው ብዙ ሰርተው ነው ። አንተ ገና ምኑንም ያላየኸው ወጣት ምን በወጣህ ስለዚህ ከመሞት መኖርን ምረጥ በማለት በብዙ ቃል ያባብለው ነበር ፤ በምክሩ ምንም ሊበግረው እንዳልቻለ ባየ ጊዜ ወደ እስር ቤቱ ተመልሶ እንዲተኛ ነገረው ። ያም ወጣት ስለጠላቶቹ ከጸለየ ለእግዚአብሔርም ምስጋናን ከሰጠ በኋላ በዚያች ሌሊት ሞተ ። ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሕይወቱን አጣ ።

አንድ ድሃ ሰው ሙዚቃን ይወድ እንደሆነ የመጨረሻዋን ገንዘቡን እንኳ ሙዚቃን ለመስማት ይሰጣል ። ቢሆንም አያዝንም ፣ አይቆጭም ፣ የሚፈልገውን የሚወደውን ሙዚቃን ሰምቶአልና ፣ እኔም ስለምወደው ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብዙ ዘመናትን በእስራት ባሳልፍም እንኳ ምንም ቅር አይለኝም ። ከቅዱሳንና ከእምነት አርበኞች ጋር ስለ እምነቴ መከራን መቀበሌ ደስ ይለኛል ። ደስታ ፣ ዝማሬ ፣ ምስጋና ዕለት ዕለት ካፋችን አይለይም ። እስር ቤትም ከመግባቴ በፊትም ሆነ አሁን ጌታን በጣም እወዳለሁ ፣ ክቡር አካሉ የም

ትሆን ቤተክርስቲያንንም እርሱን በምወድበት መውደድ እወዳታለሁ ፤ ስለ ክርስቶስ የምታቀርበውን የፍቅር መስዋእት አይቼአለሁና ።

## የሚስቴና የልጆቼ ታሪክ

ወደ እስር ቤት ከተወሰድሁ በኋላ በሚስቴና በልጄ የደረሰባቸውን አላውቅም ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ሚስቴም ስለእምነቷ በሌላ እስር ቤት እንደምትሰቃይ ሰማሁ ፣ ክርስቲያን ሴቶችም በብዙ አሰቃቂ መንገድ ይሰቃዩ ነበር ። ሊሠራ በታሰበው ካናል ውስጥ ከባድ ሥራን እንዲሠሩ ይገደዱ ነበር ። ወንዶች እንደሚሸከሙት ከባድ ሸክምን ይሸከማሉ ፤ በረዶው ሣሩ ላይ በረጋበት በክረምት ጊዜ ሣር እንዲያጭዱ ይታዘዛሉ ፣ በነዚህ ክርስቲያኖች ላይ ሸርሙጦች የበላይ ተቆጣጣሪዎች እንዲሆኑባቸው ተሾሙ ። የኔ ሚስት በችግር ምክንያት እንደ ከብት ሣር በላች ። አይጥና እባብ በነዚህ በተራቡ እስረኞች ተበልተዋል ። እነዚህን ሴቶች ወደ ጠለቀ አዘቅት ውስጥ ይወረውሩዋቸውና መልሰው እንደ ዓሣ በመንጠቆ ያጠምዳቸዋል ። በሚያሳዩትም ጭንቀት ይስቁባቸዋል ። ያ ፣ አባት እናቱ እስረኛ የሆኑበት ከርታታው ልጅ ሚሐይ ያለምንም ምክንያት ከአደባባይ ከመዞር ሌላ ምንም ሥራ አልነበረውም ። ሚሐይ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለሃይማኖታዊ ጉዳይና ስለእምነት ገድል መስማት በጣም ያስደስተው ነበር ፤ አባትና እናቱ ገና በዘጠኝ ዓመቱ ከታሰሩበት በኋላ እሱም መከራን መቀበል ግድ ሆነበት ፣ በልጅ አቅሙ ብዙ ችግርን ስላየ የሃይማኖት ጥቅሙ ምንድነው? ይል ነበር ። ራሱን ለመርዳት በዘጠኝ ዓመቱ

መድከም ነበርበት ፣ የእስረኛ ክርስቲያኖችን ልጆች መር ዳት እንደ ወንጀል ስለሚቆጠር ምንም እንኳ ፈቃደኞች ቢኖሩም ሊረዱት አልደፈሩም ። ሁለት ወይዛዝርት እርሱን መርዳታቸው በኮሚኒስት አለቆች ዘንድ እንደ ወንጀል ስለተቆጠረ እንዲታሰሩና እንዲ ገረፉ ተፈረደባቸው ። ከስቃዩም ጽናት የተነሳ ከአለፉት ፲፩ ዓመት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሽባዎች ሆነዋል። አንዲት ወይዘሮ ደግሞ ሚሐይን ሲንከራተ አግኝታ ስለረዳችው ስምንት ዓመት እንድትታሰር ተፈርዶባት ከስቃይ የተነሣ ጥር ሶቿ ረገፉ ፣ ከአጥንቶቿም ብዙዎቹ ተሰበሩ ።

## ሚሐይ በክርስቶስ ስለማመኑ

በ፲፩ ዓመቱ ሚሐይ በአንድ መሥሪያ ቤት ራሱ ን ለመርዳት ተቀጠረ ፣ ባሳለፋቸውም ብዙ የመከራ ዘመናት አማካኝነት እምነቱ ተዳክሞአል ። ነገር ግን እናቱ በታሰረችበት በሁለተኛው ዓመት እንዲጐበ ኛት ተፈቀደለትና ወደኮሚስቶች እስር ቤት ሄዶ እናቱን ከብረት አጥር ወዲያ አያት ። በሥቃይ ምክን ያት ከስታለች ፣ ጠቁራለች ፣ መልኳም ገርጥቶአል አንድ ያረጀና የተበጣጠቀ የእስረኞች ልብስ ለብሳ ነበር ። ቢሆንም ሚሐይ እናቱን ከብዙ እስረኞች መግል መለ የት አላወከውም ፤ ያችም ለብዙ ጊዜ ተለይቷት የነበ ረውን ልጅዋን ባየች ጊዜ ስለጤንነቱ ወይም ስለኑሮው ከመጠየቋ በፊት «ልጄ ሚሐይ በክርስቶስ እመን» አለችው ። ዘበኖችም ከልጅዋ ጋር ከምትነጋገርበት ቦታ ነጥለው እያመናጬቁ ወሰዱአት ። ሚሐይ የእናቱን እንዲህ መሰቃየት በተለይም ርህራሄ በሌላቸው ወታ ደሮች ስትገፈተር ሲያይ ስቅቅ ብሎ አለቀሰ ። ቢሆንም

ምንም ለማድረግ እንደማይችል ይገባዋል ፡ በዚያች ደቂቃ ሚሐይ እንዲህ ሲል ከሕሊናው ይወያይ ጀመ ር ፡ ክርስቶስ ታማኞቹን በንደዚህ ያለ መከራ ጸንተው ስለክብሩ እንዲቆሙ ብርታትንና ትእግሥትን የሚ ሰጥ አምላክ ከሆነ በርግጥ እርሱ እውተኛ አዳኝ ነው ። በዚያች ቅጽበት ያለፈውን ኃጢአቱን ተናዘዘ ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም አመነ ።

ሰው በደስታ ጊዜ ሰውን ይወድ ይሆናል ፡ ዳሩ ክርስቲያኖች ግን በስቃያቸው እንኳ ነፍሳትን ወደ ጌታ ያመጣሉ ። ይህም የመጀመሪያይቱን ቆራጥ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በመላው ዓለም እን ድትስፋፋ ፡ እንድትንሰራራ ፡ አድርጓታል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሚሐይ ትምህርት ቤት ፈልጐ ገባ ፡ በትምህር ቱም ትጉህ ስለነበር እንደ ሽልማት አድርገው የወ ጣቶች ኮሚኒስት ፓርቲ አባሎች የሚያደርጉትን ቀይ ከረባት ሰጡት ፡ ሚሐይ ግን የክርስቶስ ወንጌል ተቃ ዋሚዎች የሆኑትን የኮሚኒስቶችን አርማ አላደርግም አለ ፡ በዚህም ከት/ቤት ተባረረ ፡ ያለ ትምህርት ጥቂት ዓመታትን ካሳለፈ በኋላ የክርስቲያን እስረኞች ልጅ መሆኑንና ከቀድሞ ት/ቤት የተባረረበትን ምክንያት ማንም እንዳያውቅ ልዩ ጥንቃቄ አድርጐ ት/ቤት እን ገባ ። በትምህርት ቤቱም ለተማሪዎች ሁሉ አንድ (ቴሲስ) ማለት የመጽሐፍ ቅዱስና የእምነት ተቃ ራኒ የሆነ ድርሰትን እንዲጽፉ ታዘዙ ። ሚሐይ የጻፈው ግን እንዲህ በሚል ነበር ፡ «ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተ ሰጡትን አስተያየቶች ሃሰተኞች ናቸው ። የተሰነዘረ ውም ነቀፋ ከእውነት የራቀ ነው ፡ በእርግጥም ፕሮፌ ሰሮቻችን መጽሐፍ ቅዱስን ወይም ክርስትናን ምን እንደሚያስተምር አልተረዱትም ፡ ቢረዱ ኖሮ ግን መጽ

ሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ ከሳይንስ ጋር እንደሚስማማ ባወቁ ነበር ፡» በዚህም ድርሰት አማካይነት ከት/ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ተባረረ ። ሁለት ዓመት ራሱን የሚረዳበትን አነስተኛ ሥራ እየሠራ ያለ ት/ቤት አሳለፈ ። በመጨረሻም በአንድ ሴሚናር ውስጥ እንዲያጠና ገባ ። ከዚያም የሚያጠናው ማርክሲስት ቲዎሎጂ ነበር ። አሁንም ሚሐይ ከእምነቱ ማለት ከክርስትና ጋር የሚጻረርን ትምህርት ሲያስተምሩ ስለሰማ በጉባዔ መሐል ቆሞ በድፍረት የትምህርታቸውን ስሕተተኛነት አስረዳ ። ከጉባዔውም ብዙዎቹ እርሱ በተናገረው ተባባሪዎች ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ያን ሰሚናሪ ሳይጨርስ ከት/ቤቱ ተወገደ ።

አንድ ቀን በአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ እግዚአብሔር ላለመኖሩ አንድ ፕሮፌሰር ንግግር ያደርግ ነበር ። ሚሐይም ጥያቄ ለመጠየቅ ስለፈለገ ፈቃድ ካገኘ በኋላ እንዲህ ሲል ጠየቀው ፣ አንተም ስትፈራ ስትቸር በተናገርከው ንግግር እነዚህን ወጣቶች ሁሉ ካሳትህ በኋላ ያ ፣ የለም የምትለው እግዚአብሔር የኖረ እንደሆነ በኋላ ለሚደርስባቸው ቅጣት ምን ዋስትና ትሰጣቸዋለህ ፣ አለው ። መልስ አልነበረም ፣ ከጉባዔው ብዙዎቹ ከሚሐይ ጋር ተስማሙ ፣ ይህም የሚያሳየን አንድ ሰው የመናገር ድፍረት ኖሮት በማንኛውም ቦታ ስለክርስቶስ ከመሰከረ ምን ጊዜም ደጋፊ እንደማያጣ ነው ።

ስለ አንድ ስድስት ልጆቹን ትቶ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ወህኒ የገባ ሰው ታሪክ ልንገራችሁ? ይህ ሰው ወንጌልን በሚስጥር ማስፋፋቱ ስለተረጋገጠ ፯ቱ ዕድሜያቸው ከ፲፮—፲፯ የሚሆኑ የደረሱ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆቹን ትቶ ወህኒ ገባ ። እነዚህ ልጆች

ሥራ ሊይዙ አይችሉም ፤ ምክንያቱም የክርስቲያን
እስረኛ ልጆች በመሆናቸው ነው ። የግል ሥራ ስለ
ሌለ ሊቀጥራቸው የሚችል አልነበረም ፤ ሥራን ሊሰጥ
የሚችለው መንግሥቱ ብቻ ነው ። እነዚህ የደረሱ ልጃ
ገረዶች በእናታቸው በእነርሱና በሌሎች እህቶቻ
ቸውና ወንድሞቻቸው የደረሰውን ችግር ለማቃለል
ምንም መንገድ ስላላገኙ እናታቸውን ለመርዳት ሲሉ
ሸርሙጦች ሆኑ ። ይህንን ሲያይና ሲሰማ የ፲፩ ዓመት
ወንድማቸው በድንጋጤ እራሱን ሳተ ። ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ግን የታሰረ አባታቸው ተፈታ ፤ በመፈታቱም
ደስተኛ አልነበረም ፤ እንዲያውም እለት እለት ይጸል
የው የነበረው «አምላኬ ሆይ እዚህ ሆኜ ይህ በሕ
ዝብህ የሚደረገውን አመጽ ከማየት እስር ቤት ተመ
ልሼ ስለክብርህ መሰቃየትን እመርጣለሁ» የሚል
ነበር ። ይህም ሰው እንደተመኘው አንድ ቀን በመን
ገድ ዳር ልጆችን ሰብስቦ ስለ ክርስቶስ ሲያስተምር
ስለተገኘ እንደገና ወህኒ እንዲገባ ተደረገ ። እነዚህ
ሴተኛ አዳሪዎች የነበሩ ልጆቹም ዛሬ የሚስጥር ፖሊ
ሶች አባሎች ናቸው ። ቀድሞ ክርስቲያኖችና የክርስቲ
ያን እስረኞች ልጆች እንደሆኑ በሚያውቋቸው ሰዎ
ች ቤት እየዞሩ ብዙ ክርስቲያኖችን አሳሰሩ ።

## ምዕራፍ ፫

ከታሰርኩ ፲፩ ዓመት ሆነኝ በነዚህ ጊዜያት መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌላ መንፈሳዊ ጽሑፍን አላየሁም ። ብዙ ያጠናኋቸው ጥቅሶች ተዘንግተውኛል ፤ ነገር ግን አሥራ አራተኛ ዓመቴን በሞላሁ ጊዜ በድንገት ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ ፤ ያም ያዕቆብ ራሄልን ስለሚወዳት አሥራ አራት ዓመት ተገዛላት ፤ ያም አሥራ አራት ዓመት ምንም አልረዘመበትም ፤ ምክንያቱም ይወዳት ነበርና የሚለው ነው ። ታዲያ እኔም ለሚወደኝና ለምወደው ለክርስቶስ ፲፩ ዓመትን ማሳለፌ እርሱ ካደረገልኝ ውለታ ጋር ሳስተያየው በጣም አነስተኛ መሆኑ ይሰማኛል ። በርግጥም ነው ያ አሥራ አራት ዓመት ከምን ጊዜውም እንደደረሰ አላውቅም ፥ ብዙ ጊዜ ካሳለፍኩ በኋላ ተፈታሁ ፤ ሚስቴም ለ፲፩ ዓመት በታማኝነት ቆየችኝ ፤ ምንም እንኳ ከመታሰሬ በፊት ብቁ ኑሮን ለመኖር የሚያስችል ሀብት ቢኖረኝም ፤ ያ ሁሉ እኔ ለመታሰር ወደወህኒ ሲወርድ ተወርሶ ነበር ። ስለዚህ እንደገና ኑሮን ለመቋቋም መታገል ነበረብኝ ፤ የተፈቱት ቄሶችና የቤተክርስቲያን መሪዎች በኮሚኒስቶች የበላይ ጥበቃ ስር የሆኑትን ትንንሽ ቤተ ክርስቲያኖች እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ ፤ እኔም በኦርሶቫ ያለችውን አነስተኛ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ እንድሆን እግዚአብሔር የለም ፤ ሃይማኖትም አይጠቅምም ፤ በሚሉ በኮሚኒስት መሪዎች ተሾምኩ ። አንድ የኮሚኒስት ድርጅት እንዲህ ሲል ማስጠንቀቂያ ሰጠኝ ፤ አሁን እንድታስተዳድራት በምንሰጥህ አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፴፭ ሰዎች አሉ ፤ ስለዚህ ፴፮ ሆነው ቢገኙ ልብ አድርግ ውርድ ከራስህ ነው ፤ ወጣቶችን ስለበክ ብገኝም

የሚደርስብኝንም ስቃይ ጽኑነት በማስፈራራትና በዛቻ ነገሩኝ ፤ ምን ዓይነት ሥልጣን ነው? ያሉት ሰዎች ፴፫ ናቸው ፴፮ እንዳይሆኑም ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ። ለመሆኑ ክርስቶስ ለተከታዮቹ እስከ ምድር ዳር ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ሲል ተናግሮ የለ? ታዲያ ፥ ትክ ክለኛ ትእዛዝ ሰጪ ማነው ፴፫ ሰዎች ላይ ፩ ተጨ ምሮ ፴፮ እንዳይሆኑ የሚፈልጉ የኮሚኒስት መሪዎች ወይስ በምድር ዙሪያ ሁሉ በርሱ እንዲያምኑና ከዘለዓለም ሞት እንዲድኑ ፈቃዱ የሆነ ክርስቶስ ሌሎች ጥያቄውን እንዳሻቸው ይመልሱት ፤ እኔ ግን ቢቻለኝ አለምን ሁሉ ክርስቲያን አደርግ ዘንድ ወን ጌልን እሰብካለሁ ፥ ይህ ብቻ ሳይሆን የቅስናን ልብስ ለብሼ በሚስጥር የነሱ ወሬ ጠቋሚ እንድሆንም አባ ብለውኛል ። ኮሚኒስቶች ይህን በመሰለና በሌላም ብዙ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን ይዋጓታል ወንጌልን ለሰዎች ብሰብክ ብዙዎች ወደ ጌታ እንደሚመጡ አውቃለሁ ። ይህን እንዳላደርግ ደግሞ ብዙ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ኛል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ወንጌልን በትጋት እሰብክ ነበር ፤ እግዚአብሔርም እርሱን በሚሹት መሃል በታ ላቅ ሃይል ተመላለሰ ፤ ታላላቅ ታምራትም ተደረጉ ፤ የጌታ ቤተ ክርስቲያንም ዕለት ዕለት ታድግ ነበር ።

አንድ ቀን በአንድ ገጠር ባለ ክርስቲያን ወን ድሜ ቤት አርፌ እንቅልፍ ሸለብ አድርጎኝ ሳለሁ በድንገት ያ ወንድሜ ቀስቅሶ ክርስቲያን ወንድሞች ከውጭ አገር ሊጐበኙህ መጥተዋል አለኝ ። ወደ እን ግዳ መቀበያ ክፍሉ ወጣ ብል እኛን ለማናገር የሚሹ ስድስት ሰዎችን አገኘሁ ። ብዙ አወጋን ከተነጋገርን ባቸውም ጉዳዮች ብዙ እናት አባታቸውን በኮሚኒ ስት እስር ቤት ያጡትን የክርስቲያን ሰማእታት ልጆ

ችን ለመርዳት ፣ መንፈሳዊ ጽሑፎችን ለመበተን ፣ ክር ስትናን ለማስፋፋት ነበር ። ከነዚህ ሰዎች እንደተነጋ ገርኩ በጣም ደስ አለኝ ። በአሜሪካ ፣ በእንግላንድና በስካንድኔቪያን አገሮች ክርስቲያኖች እንዳልተዘነጋን ገባኝ ። እንዲያውም ታላላቅ የጸሎት ስብሰባቸው በማ ድረግ እግዚአብሔር እኛን እንዲረዳን ይጸሙና ይጸ ልዩ እንደነበር ነገሩን ። ከብዙ ውይይት በኋላም ወደ አገራቸው ከመመለሳቸው በፊት ስለ አንድ ፲፬ ዓመት በኮሚኒስቶች እስር ቤት ስለታሰረ ክርስቲያን ሰምተን ነበርና ያን ሰው አግኝተነው እርሱን ለማነ ጋገር ስለምንፈልግ በዚህ እንድትረዳን አሉኝ ። እኔም ያ እናንተ ልታነጋግሩት የምትፈልጉት ፲፬ ዓመት በኮሚኒስት እስር ቤት ያሳለፈው ሰው እኔ ሪቻርድ ኡምብራንድ የምባለው ነኝ አልኳቸው ። ሊያምኑኝም አልቻሉም ፤ ብዙ ማስረጃዎችን አቀረብኩ ፤ ከመካከላ ቸው አንዱ እንዴት አንተ ያን ሰው ልትሆን ትችላ ለህ? እንደምናይህ በጣም ደስተኛ ነህ አለኝ ፤ አሁንም ቢሆን በርግጥ እኔ ሊያነጋግሩት የሚፈልጉት ሰው መ ሆኔን እንዲያውቁ በማለት ብዙ ነገርኳቸው ። የደስታዬ መነሻ ግን የእኛ በሌሎች ክርስቲያን ወንድሞቻችን አለመዘንጋታችን ነው ። በእስራት በነበርንበት ጊዜ ሌላው ዓለም ስለኛ ምንም የማያውቅ መስሎን ነበር ፤ አሁን ግን እንዳልተዘነጋን በክርስቲያኖችም ጸሎት እለት እለት እንደምንታሰብ ስንሰማ እንዴት ደስ አይለንም? ከነዚህ ሰዎች ጋር ይበልጥ ወንጌልን ለማ ስፋፋት ስለምንችልበት መንገድ ፕላን አወጣን ፤ በፕ ላናችንም መሠረት ብዙ መንፈሳዊ ጽሑፎችን ወንጌ ሎችንና መጽሐፍ ቅዱሶችን በተንን ። ውጤቱም በጣም አጥጋቢ ነበር ። እኔና ቤተ ሰቤ ያለ ክርስቲያኖች ጸሎ

ትና ድጋፍ እስከ አሁን ለመቆየት እንኳ ባልቻልንም ነበር ፤ ዳሩ ግን በችግር ያለ ሕዝብ ይረዱ ዘንድ መላእክትን የሚልክ ሃያል አምላክ እነዚህን ወንድ ሞች ላከልን ፤ እነሱ ለኛ ከአምላክ እንደሚላኩ መላእ ክት ናቸው ።

ያች ፴፰ ሰዎች የነበሩባትና ፴፮ የሆኑ እንደሆነ ከፍ ያለ ቅጣት አለብህ ተብዬ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ አስተዳዳሪ እንድሆን በኮሚኒስቶች የተሾምኩባት ቤተ ክርስቲያን ከመጠን በላይ ዕለት ዕለት ታድግ ነበር ፤ ስለ ዚህም ምናልባት ለሶስተኛ ጊዜ እንታሰር ይሆናል የሚል ስጋት በኔና በሌሎችም ዘንድ ነበር ።

የኖርዌጂያን ሚሲዮንና የቶብራዊያን ክርስቲያ ኖች ማኅበር በመባል የታወቁ ሁለት ድርጅቶች ለሩ ማንያ መንግሥት $ 2500 ከፍለው ከሩማንያ እንድ ወጣ ተደረገ ።

## ለምን ከሩማንያ ወጣሁ

ከሩማንያ የወጣሁት ምክንያት ዳግመኛ በመታ ሰር ፍራቻ አልነበረም ፤ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ኅብ ረት ችግራቸውንና ለሌላው ዓለም እንዳሰማላቸው አፈ ጉባዔ አድርገው ስለመረጡኝ ነው ። ምንም እንኳ በአካሌ በሩማንያ ካሉ ክርስቲያን ወንድሞቼ ርቄ ብሄድም ልቤ ዳግመኛ ከማጠይፋው ዘር በመወለድ ወንድሞቼ ከሆኑ ከክርስቲያኖች ጋር ነው ።

ከሩማንያ ወጥቶ የክርስቲያኖችን ችግር ለሌላው ዓለም ማስረዳት አስፈላጊነቱ ባይታየኝ ኖሮ እስከ

መጨረሻው ከሩማንያ የመውጣት እቅድ አልነበረ ኝም ።

ሩማንያን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ሁለት ጊዜ ወደሚስጥር ፖሊሶች ድርጅት ተጠርቼ በ $ 2500 ብር መሸጤን ነገረኝ ። ሩማንያ ኮሚኒዝም ባመጣበት ችግ ር ምክንያት የገዛ ልጆችዋን እንኳ እስክትሸጥ ድረስ የድሃ ሃገር ሆናለች ። በፊታቸው የቀረብኩባቸው ባለ ሥልጣኖች «ሂድ! ወደሌላው ዓለም ሄደህ ወንጌልን እንዳሻህ ስበክ ግን ተጠንቀቅ! እኛን አትንካን ፣ ስለእ ኛም ተቃራኒ ነገርን እንዳትናገር ፣ ከሩማንያ ከወጣህ በኋላ እንኳ ይህን አሁን የምነግርህን ቸል ብትል ምንም ወደሩቅ ሃገር ብትሄድ አፍነን መልሰን እንደ ምናመጣህ አይዘንጋህ» ። ማስጠንቀቂያው በጣም ከባድ ነው ።

አብሮኝ ታስሮ የነበረ ኦርቶዶክሳዊ ጳጳስ ከሩ ማንያ እንደኔ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከወጣ በኋላ ማስጠንቀቂያውን ቸል በማለት ስለኮ ሚኒዝም ክፉ ወሬን አስወርተሃል በመባል ወህኒ ከመ ግባቱም ሌላ በብዙ ልዩ ልዩ ሥቃይ ይሰቃይ ነበር ። አይኖቹ እያዩ የእጅና የእግሩ ጥፍሮች ተነቀሉ ፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ከበርሊን ፣ ከኢጣሊያና ከፓሪስ ታፍነው የተ መለሱ ብዙ ሰዎችን አውቃለሁ ፣ ከሩማንያ ስወጣ ኮሚ ኒስቶች የሰጡኝ ማስጠንቀቂያ አፍነው ሊወስዱኝ እንደሚችሉ ብቻ አልነበረም ። ነገር ግን ስለኔ ብዙ መጥፎ ወሬን በማስወራት ሞራሌን እንደሚሰብሩ ብኝ ነገሩኝ ። ይህ ሁሉ የማስጠንቀቂያ ጋጋታ ስለኮ ሚኒዝም መጥፎነት እንዳላወራ ለማድረግ ነው ፣ሌላም ይህን የመሳሰሉ ብዙ ማስጠንቀቃያዎች ከሰጡኝ በኋላ ወደፈለግሁበት ዓለም እንድሄድ ፈቀዱልኝ ፤ በጎ

ዳር ወር ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. እኔና ቤተሰቤ ሩማንያን ለቅ ቀን ወጣን ። ይህን ከማድረጌ ማለት ከሩማንያ ከመ ውጣቴ በፊት እንድታሰር ወደፈረደብኝ ኰሎኔል መቃብር ሄጄ አበባን አስቀመጥኩ ። ይህም ምንም እንኳ ኮሚኒዝምን ብቃወም የኮሚኒስቶች ግን ወዳጅ መሆኔን ሊያስረዳልኝ ይችላል ። በርግጥ ኮሚኒዝምን እጠ ላለሁ ፤ ኮሚኒስቶችን ግን እወዳቸዋለሁ ፤ ሃጢአትን እጠ ላለሁ ፤ ሃጢአተኞችን ግን እወዳለሁ ፤ ኮሚኒስቶች ክር ስቲያኖችን ሊገድሉ ይችላሉ ፤ በውስጣቸው ያለውን የክርስቶስን ፍቅር ግን ሊገድሉት ወይም ሊያጠፉት አይችሉም ። እኔ ሞራላቸውን የገደለው የዚያ የመጥፎ ትምህርት ተቃዋሚ ብሆንም የሰው ልጆች ሁሉ ወዳጅ ነኝ ።

## ምዕራፍ ፩

አይሁዶች አንድ ተረት አላቸው ፤ አባቶቻቸው ከግብጽ ከባርነት ምድር በወጡ ጊዜ በተቃዋሚዎ ቻቸው ላይ ብዙ መቅሰፍት ወርዶ ነበር ። ከነዚህም ታላላቅ ተአምራት አንዱ የእስራኤል ልጆች እንዲያ ልፉበት የኤርትራ ባሕር እንደ ግድግዳ መቆሙና እነርሱ ከተሻገሩና ዳር ከቆሙ በኋላ ግን የግብጻውያን ሠራዊት እነርሱን ለማሳደድ ሲገቡ በውሃው ሙላት ተበልተው ወደተራሮች ሥር እንደዘቀጡ የሚያስረዳ ነው ፣ ታዲያ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸው በውሃው ተደፍነው እንደ ሞቱ ባዩ ጊዜ ደስ ብሎአቸው ይዘምሩ ነበር ። መላእ ክትም አብረው ይዘምሩ ነበር ፤ ታዲያ ፣ የሁሉ አባት የሚሆን እግዚአብሔር መላእክትን በትዝብት እንዲህ አላቸው ፣ እስራኤላውያን ቢስቁ ፣ ቢደሰቱ ፣ ቢዘምሩ ፣ በጠላቶቻቸውም መጥፋት እጅግ ቢቦሩቁ ፤ ሰዎች ናቸው ። የእናንተ ግን ከነሱ ጋር አብሮ መደሰት መል ካም አይደለም ፣ ለመሆኑ እኔ የእስራኤላውያን ፈጣሪ እንደሆንኩ የግብጻውያንስ አይደለሁምን? አልወዳቸ ውምን? በእስራኤላውያን መዳን ስደሰት በግብጻው ያንም መጥፋት እንደማዝን ይህ ለምን ከናንተ ተሰ ወረ?» ኢያሱ በእያሪኮ በነበረ ጊዜ ዓይኖቹን አንስቶ የተመዘዘ ሠይፍ የያዘ መልአክን አየ ። ኢያሱም በድን ጋጤ እፊቱ ቆሞ የነበረውን መልአክ አንተ ለየት ኛው ወገን ነህ? ለኛ ወይም በጠላቶቻችን? አለው ። መጽሐፈ ኢያሱ ፭—፲፫ ይህ ኢያሱ ያየው መልአክ ሰው ቢሆን ኖሮ እኔ የናንተ ነኝ ወይም የጠላቶቻ ችሁ ነኝ ባለው ፣ ያንዱ ተቀዋሚ የሌለው ግን ደጋፊ በሆነ ነበር ፤ ነገር ግን እርሱ ከሌላ አካባቢ የመጣ ነበር ፤ እርሱ የመጣው ሁሉም በትክክለኛ ፍርድ ከሚጉበ

ኙበት አገር ነው፤ ስለዚህም ያ መልአክ ኢያሱን እኔ የናንተ ወይም የጠላቶቻችሁ ነኝ ከማለት ይልቅ «የእ ግዚአብሔር መልእክተኛ» እንደሆነ ብቻ ነገረው፤ እንደዚሁም ክርስቲያኖች ምንም እንኳ በሥጋ ሥጋ ውያን ከሚሆኑ እናትና አባት የተወለዱ ቢሆኑም በመ ንፈስ ግን ከእግዚአብሔር ተወልደዋል ፤ የመለኮታዊው ባህርይ ተካፋዮች ናቸው ።

በኮሚኒስቶች ብዙ ብሰቃይም በነርሱ ላይ ምንም ጥላቻ የለኝም ፡ ምንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ናቸው ፤ እርሱም ይወዳቸዋል ፤ ታዲያ እንዴት እጠላቸ ዋለሁ? የኮሚኒስቶች ጓደኛ ነኝ «እውነተኛ ጓደኝነት ማለት ሁለት ነፍሶች በአንድ ራስ ማለት ነው» ዳሩ ። በነፍስ ከነርሱ ጋር አንድነት የለኝም ። እኔ በነፍስ በመ ንፈሳዊ ዓለም (መንግሥተ ሰማያት) አምናለሁ ፤ እነሱ ግን አያምኑም ፡ እኔ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እነሱ ግን የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች ናቸው ። ምናልባት የኮሚኒስቶች ደጋፊ ወይም ተቃራኒ መሆኔን ብጠየቅ መልሴ የሚያሻማ ይሆናል ፡ እርግጥ ኮሚኒዝም በሰ ዎች አእምሮ ውስጥ ከንቱ ነገርን የተከለ ትምህርት ነው ። ስለዚህ እኔ የኮሚኒዝም ተቃዋሚ ነኝ ፡ እስኪ ጠፋም ድረስ እዋጋላሁ ፡ ነገር ግን በመንፈስ ከክርስ ቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጬአለሁ ማለት ያ ፡ መልአክ ከነበረበት አካባቢ ነኝ ፤ ኮሚኒስቶች ምንም እንኳ ቢያምጹ በፍቅር ከሚታዩበት አካባቢ ነኝ ። መላ እክት ሁሉ የሰው ልጆችን ለመርዳት ከሚላኩበት አካባቢ ነኝ ፤ ስለዚህም የምሥራቹ በኮሚኒስት አገር እንዲስፋፋ እተጋለሁ ፡ የክርስቶስን ወንጌልና እርሱ ንም በማመን የዘለዓለም ሕይወት እንደሚገኝ አው ጃለሁ ።

አምላኬ ኮሚኒስቶችን ይወዳቸዋል ፤ እሱ ራሱ ከመቶ በጐች አንዲቷ ብትጠፋበት እሷን በፈለገበት ፍቅር ኮሚኒስቶችንም እሱን እንዲያምኑና የዘለዓለም ሕይወት እንዲያገኙ ይሻል ፣ የእርሱ ሐዋርያትና ታላላቅ የክርስትና መምህራን የእርሱ ፍቅር «ዓለም አቀፍ» እን ደሆነና አንዱን ካንዱ የማይለይ ዓለም አቀፍ እንደ ሆነ አስተምረዋል ። ቅዱስ ማካሪ እንዲህ አለ ፣ «አንዱ ሰው ይህን እወደዋለሁ ያኛውን ግን እጠላዋለሁ እያለ በሰዎች መካከል ልዩነትን ቢፈጥር ራሱንም ክርስ ቲያን ነኝ እያለ ቢጠራ ያ ሰው ፍጹም ክርስቲያን አይደለም ። ምክንያቱም ያለው ፍቅር አንዱን አስወ ድዶ ሌላውን የሚጠላ ነውና» ። ቅዱስ አውጉሲጢ ኖስ ደግሞ እንዲህ አለ «ዓለም ሁሉ ጻድቅ አንድ ሰው ብቻ ግን ኃጢአተኛ ቢሆን ክርስቶስ ለዚያ ለኃ ጢአተኛ ዳግመኛ መጥቶ ሊሰቀልለት ይወዳል ፤ የእርሱ ፍቅር ሁሉም እንዲድኑ የሚሻ እንጂ በሰዎች መካ ከል ልዩነትን የሚያመጣ አይደለም» ። የክርስትና ትም ህርት ብዙ ሰዎች እንደሚያመካኙበት የተወሳሰበ ፣ ሊረዳ የማይችል ፣ ሣይሆን ግልጽና የተብራራ ነው ። ክርስቶስ የሞተው ስለ ፍቅር ፣ ለፍቅር ነው ፣ በመስ ቀል የተቸነከረውም ለሁሉም ነው ። ስለሆነም እርሱ የሞተላቸው ስለሆኑ ኮሚኒስቶችንም ይወዳል ፤ ስለዚህ እኛ የክርስቶስ የሆንን ኃጢአትን እንጥላ ፣ ኃጢአተ ኞችን ግን እንውደድ ። ኮሚኒዝምን ብንጠላም ኮሚ ኒስቶችን መውደድ ይገባናል ። በእስር ቤት ውስጥ ብዙ ፓውንድ በሚመዝን እግረ ሙቅ ታስረው በሌ ላም በብዙ መንገድ በኮሚኒስቶች ሲሰቃዩ ነበር ፤ ቢሆ ንም በውስጣቸው ያለው የክርስቶስ መንፈስ ግን ለሚ በድሉዋቸው የኃጢአት ሥርየት ይሆን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይቃትታል ፤ ክርስቲያኖችን ለሚያሰቃዩ

ዋቻው ለኮሚኒስቶች ይጸልያሉ ። ይህን የሚያደርገው በልባቸው የፈሰሰው የክርስቶስ ፍቅር ነው ፣ ጠባብ የሆነው የሥጋውያን አእምሮ ሊረዳው አይችልም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያሰቃዩን የነበሩት ኮሚኒስቶች በሚያደርጉት ጥፋት ተፈርዶባቸው ጥቂቶቹ አብረውን ታሰሩ ፤ አሰቃዮችና ተሰቃዮች ባንድነት ታሰሩ ፣ ክርስቲያን ያልነበሩት ሰዎች ቀድሞ ይገርፉአቸው ይደበድቧቸው የነበሩት ሰዎች እነሱ የቀመሱትን ስቃይ ስለ ቀመሱላቸው ደስ ሲላቸው ክርስቲያኖች ግን ለእነርሱ የሚሰጣቸውን ዳቦና መድኃኒት በሥቃዩ ጽናት ሕመም ለደረሰባቸው ለኮሚኒስቶች ይሰጡ ነበር ። ጌታን ተቀባዩ ክርስቲያን ከሆንክ ጀምሮ በመንገድ ለማያቸው ወንዶችና ሴቶች በልቤ ውስጥ የሚነሳው ጥያቄ እሷ ወይም እሱ ድነዋል? የሚል ነበር ። ላልዳኑ ነፍሳትና ለደከሙ ክርስቲያኖች ያልቀሰኩባቸው ቀናት ጥቂት አልነበሩም ፤ ነፍሳትን ሁሉ ወደ ደህንነት ለማምጣት ልቤ በፍቅር ይግል ነበር ፣ ያም ፍቅር በመላው ዓለም ክልል ስለሚዞር ኮሚኒስቶችንም ይጨምራል (ይወክላል) ። በእስር ቤት በጣም ተራብን እስክንዝልና እስክንወድቅ ድረስ በችጋር ተቆላን ። ልክ እንደአጽም ደርቀን ስለነበር የጌታን ጸሎት (አባታችን ሆይን) ለመጸለይ እጅግ ይረዝምብን ነበር ፤ በዚህ ሁሉ ድካም ስቃይ ሁሉ ደጋግሜ «ጌታ ሆይ እወድሃለሁ» እል ነበር ። ታዲያ አንድ ቀን ጌታ ግልጽ በሆነ ወደ አጥንት ጠልቆ በሚገባ ንግግር እጅግ ውብ በሆኑም ቃላት «አዎ ትወደኛለህ እንደምትወደኝም አውቃለሁ» እኔ ደግሞ አንተን እንዴት እንደምወድህ ላሳይህ? ወዲያው በሰውነቴ ውስጥ እንደሚነድ እሳት ነበልባል የርሱ ፍቅር ተቀጣጠለ ። አካልን አልፎ ወደ ሰውነት ዘልቆ እንደሚገባ ኃይለኛ የጸሐይ ጨረር

ነበር ። ትንሿ ልቤ ሁሉን በሚችል መለኮታዊ አም
ላክ ፍቅር ጋለች ፣ እኔም «እርግጥ ነው ጌታ ሆይ እኔ
አንተን ከምወድበት ፍቅር ይልቅ አንተ እኔን የም
ትወድበት ፍቅር እጅግ የጋለ ነው» አልኩ ፣ ሁለቱ ደቀ
መዛሙርት ወደ ኤማሁስ መንደር ሲሄዱ ጌታ ሲና
ገራቸው «ልባችን ነደደ» ያሉት ያን ፍቅር እኔም ተለ
ማመድኩት በርግጥ ዓለምን ሁሉ ለማዳን ራሱን ስለ
ፍቅር በመስቀል ለመሞት የሰጠው የፍቅር አምላክ
ኮሚኒስቶችን አልዘነጋቸውም ። ብዙ ውሃ ሐይቆ
ችና ጅረቶችም ውቅያኖስን የበላይ አዛዥ አድርገው
በፍቅር ላይ ዘመቻ ቢያደርጉም የመለኮታዊ ፍቅርን
ነዲድ ሊያጠፉ አይችሉም ። ፍቅር እጅግ ጽኑ ነው ፤
ጥላቻ ግን የመቃብርን ያህል ጨካኝ ነው ። መቃብር
ድሃንና ሃብታምን ፣ ሕፃንና አዋቂን ፣ ጐረምሳንና ኮረ
ዳን ፣ እሮጊትና ሽማግሌን ፣ ነጭና ጥቁርን ፣ አሽከርና
ጌታን እንደሚይዝ ሁሉ መለኮታዊውም ፍቅር የሰዎ
ችን ልጆች በእቅፍ ይይዛል ፤ ያም ፍቅር የልቡን መሻ
ት እስኪያደርግ አይጠፋም ። አንድ ቀን እኛ ወደአለ
ንበት እስር ቤት አንድ በደም የተጨማለቀ ክፉኛ
የተደበደበና ግማሽ ሙት የሆነ ሰው ተወረወረ ፤ ከሰው
ነቱና ከራሱ ላይ ደም በብዛት ይጐርፋል ፤ እኛም ስናጥ
በው ሳለን አንዳንዶች በዚህ ሰው ላይ ስላደረጉት
ጥፋት ኮሚኒስቶችን ይረግሙ ነበር ፣ ይህን ሲሰማ ያ
የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲህ አለ ፣ «እባካችሁ ክር
ስቲያን ወንድሞቼ አትርገሙአቸው ፣ ይልቅ ጌታ ይቅር
እንዲላቸው እንጸልይላቸው» ተንበርክኮም ጸለየ ።

## በእስር ቤት እንዴት ደስተኞች ሆንን?

ያለፉትን አሥራ አራት ዓመታት ሳስባቸው አን ዳንዴ በጣም እደሰት ነበር፤ ሌሎች ሰዎችና የእስር ቤቱ ዘበኞች ራሳቸው በዚያ ሁሉ ስቃይ ደስተኞች መሆናችንን ሲመለከቱ በጣም ነበር የሚገረሙት።

ዝማሬ ካፋችን አልተወገደም፤ ይህንንም በማድ ረጋችን ብንደበደብም ለእግዚአብሔር ምስጋና መስ ጠት ዋና ተግባራችን ነበር፡ አንዳንድ ጊዜማ ዘማርያን ወፎች ከእኛ ጋር እየዘመሩ ለመዝሙራችን ልዩ ውበት የሚሰጡት ይመስል ነበር፡ ምንም እንኳ መዝሙራ ቸውን ሳይጨርሱ በኮሚኒስት ፖሊሶች እንደሚቋ ረጡ ቢያውቁም የሆነው እስከሆነ ድረስ ዝማሬ ካን ደበታቸው አልተለየም። ይዘላሉ፡ ይደሰታሉ፡ እግዚአ ብሔርንም ያመሰግናሉ፣ እንዴት ይህን በመሰለ ስቃይ ክርስቲያኖች ደስተኖች ሆኑ? በእስር ቤት ሣለሁ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ «እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይ ኖች ብጹአን ናቸው» ያለበትን ምክንያት አሰላስል ነበር። ደቀመዛሙርቱ ያዩት ሕመምን፡ ረሃብን፡ ሃብ ታም ድሃን ሲበድል፤ እውነት በሐሰት እግር ስር ስት ጣል ነበር ያዩት። በዚያ ዘመን ፓሊስቲና በጨካኞቹ ሮማውያን እጅ ስለነበረች የሚዩያት ሁሉ የሚያስደ ስት አልነበረም። ቢሆንም ጌታ እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብጹአን ናቸው አለ፤ ያ «ደስ ይበ ላችሁ» የሚለው ቃል ስቃይን፤ ረሃብን፤ የፍርድ መጉ ደልን በማየታቸው ሳይሆን የሁሉ ሊቃኝ፡ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ፡ የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ የሚሆን ጌታን በማየታቸው ነበር።

ያች በብዙ ክለር ተዥጐርጉራ የምታምረው ቢራ ቢሮ አንድ ቀን ለዓይን በሚያስጠላ ቀፎ ውስጥ ነበ ረች ፤ ያ ቀፎ ሲሰበር ግን ውበቷን ይዛ ከቀፎው ለመ ውጣት ቻለች ፡ አንድ ቀን በችግር በጭንቀት ላሉ ክርስቲያኖች እንደዚህ ይሆናል ፤ ቀፎው ሲሰበር ነፍ ሳት ሁሉ ነጻ ይወጣሉ ፡ ብዙ የተሰቃየ ኢዮብን አስ ቡት ፡ ታዲያ ምን ሆነ? እግዚአብሔር ስለደረሰበት መከራ ሁሉ መልሶ ካሰው ። ሰውነቱ በቁስል የተመታ ውን ፡ ውሾች ቁስሉን ይልሱለት የነበረውን አልአዛ ርን አስቡት ። ታዲያ ምን ሆነ? በሞተ ጊዜ መላእክት የዘለዓለም ፍስሐ ወዳለበት ወደአብርሃም እቅፍ ወሰ ዱት ፤ ይህንን ሳስብ ለክርስቲያኖች የተነገረው የተስፋ ቃሉ ሁሉ ወለል ብሎ ታየኝ ። ዛሬ በብቱቶና በቁስል የተሸፈነው የክርስቲያን ሰማዕታት ገላ እጅግ ነጭ በሆነ የካህናት ነገሥታት ልብስ እንደሚሸፈን ትዝ አለኝ ። ሰዎችን አሁን እንዳሉበት ይዞታ ሳይሆን ወደ ፊት እንደሚሆኑበት መመልከት ፡ አሳዶችም እንደ ሳውል ተለውጠው ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆኑ ማየት ምንኛ ደስ ይላል!

በርግጥ ሲያሳድዱን የነበሩትን ብዙዎቹን ተመ ልሰው ክርስቲያን ሲሆኑ አይተናል ፤ ክርስቲያን በመ ሆናቸውም ወህኒ ቢገቡም ስለጌታ በመሰቃየታቸው በጣም ደስተኞች ነበሩ ፤ እንደዚህ ጳውሎስና ሲላስን ከብዙ ድብደባ እግራቸው ከግንድ ከተጠረቀ በኋላ እንዲጠብቃቸው ታዞ እንደነበረው የፊልጵስዮስ ወታ ደር «ወንድሞቼ ሆይ እንድድን ምን ላድርግ ብለው ቀድሞ ተቀዋሚዎቻችን የነበሩ ሰዎች ጠይቀ ውን እነሱም እኛ የምናምነውን አምላክ አምነው የወ ንጌሉ አስፋፊዎች እንደሆኑ ስናይ ምንኛ ደስ ይል ይመስላችኋል!

በክርስቲያኖች የሚያሾፉት በጐልጐታ እንደነ በሩ ሰዎች ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደረታቸውን እየደቁ ይህስ በውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው በማለት ሲናዘዙ መስማት ደስ አይልምን?

## ክርስቲያኖች መልሱን ይስጡ

ኮሚኒስቶች እንደሌላው ሁሉ የሥጋ ልብ ስላ ላቸው እነሱም በጌታ ወንጌል ሊያምኑና ተናዘው እርሱን ሊቀበሉ ይችላሉ ። ይህንንም የተረዳነው በእ ስር ቤት በነበርንበት ጊዜ ነው ። በነሱ መገረፍ ነው እነሱን ማፍቀር እንዳለብን የተረዳነው ። ከወገኖቼ ብዙዎች ተገድለዋል ፤ ቢሆንም ከገዳዮቹ ብዙዎቹ ጌ ታን የተቀበሉት በእኔ ቤት ነበር ። የእኛ አስተሳሰብ ፥ አስ ተያየት ፥ ከጉንዳን ወይም ከትንኝ በጣም ከፍ ያለ እን ደሆነ ሁሉ እግዚረአብሔርም ነገራችንን ሁሉ እኛ ከም ንገምተው በጣም በሚለይ እርቀት ያያቸዋል ። እርሱ ሰው እንደሚያይ አያይም ። ይህ ስቃይ ሁሉ ምንም እንኳ በኛ በሰዎች ጊዜያዊ አስተሳሰብ የከፋና የማይ ቻል ቢሆንም የነገሮችን መጨረሻ በሚያውቅ በአ ምላክ አይን መጨረሻቸው ብሩህ ነበር ።

ከግማሽ ክፍለ ዘመን ባላይ የተንሰራፋው ኃይል ምናልባት አንድ ሺህ ዓመት አንድ ቀን በሆነችለት በአምላካችን እንደ አንድ ቀን ትቆጠር ይሆናል ፤ ምንም እንኳ ሕዝቡ የሆኑትን ክርስቲያኖች የሚያሳድዱ ቢሆንም አምላክ ለዓለም ካለው ዓላማ ኮሚኒስቶችን አላስወጣም ። እርሱ የኃጢአተኛን ተናዞ መመለስ እንጂ በኃጢአቱ መጥፋቱን አይወድም ። የመንግሥተ ሰማያት በር አልተዘጋባቸውም ። የክርስቲያኖች እናት

የምትሆን ሰማያዊት ፅዮን ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ ጌታ እየሱስንም እንደግል አዳኛቸው ከተቀበሉ የነሱም እናት ትሆናለች ። የመንገደኛ መሪ የሆነው መብራት አልጠፋባቸውም ፣ በብርሃኑ መኖርን ከፈቀዱ ተፈቅዶላቸዋል ። እኛም ቀድሞ መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ «ንስሐ ግቡ» ብለው እንደሰበኩ ሁሉ ተመሳሳይ መልእክትን ልንሰጣቸው ይገባል ።

ኮሚኒስቶችን ሊለውጣቸው የሚችል ፍቅር ነው ፤ ስለዚህም የክርስቶስን ፍቅር እናበርክትላቸው።

በሃይል መቃወምን ካመጣን ሂትለር የኮሚኒስቶች ተቃዋሚ ነበር ፣ ጥላቻ አይኑን አሳወረው ። ብዙዎችን አሠረ ፣ ብዙዎችንም ገደለ ፣ ቢሆንም ሊያጠፋቸው አልቻለም እንዲያውም የዓለምን 1/3 ያህል እንዲበዙ መንገድን ከፈተላቸው ።

እኛ ግን ኮሚኒስቶችን በፍቅር ለማሸነፍ በፍቅር የተመሰረተ እቅድን በእስር ቤት አወጣን ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብንመረምር የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን መልእክቷን መልካም ውጤት እንዲያገኝ ያደረገችው አስቀድማ ለሕዝብ አለቆች ማለት ለነገሥታትና ለአለቆች ወንጌልን ትሰብካለች ። ከዚያ በኋላ የሕዝቡ መሪዎች የትምህርቱን መልካምነት ካዩ በኋላ ሕዝቡን እንዲያስተምሩ ሙሉ ነፃነት ይሰጡአቸዋል ፣ ይህን በመሰለ መንገድ ነው ወንጌል እንዲስፋፋ ያደረጉት ።

ለምሳሌ ኖርዌይ የክርስቲያን አገር የሆነችው እንዴት ነበር? ንጉሣቸውን አፍላን አስቀድሞ ክርስቲያን በማድረግ ነው ። ሩሲያን ክርስቲያን ለማድረግ

ሲታቀድ አስቀድሞ ንጉሣቸው ሐንጋሪን ክርስቲያን ለማድረግ ምን ተደረገ? በዘመኑ የነበሩ ወንጌላው ያን አስቀድመው ሲተፌንስን ለሚባለው ንጉሣቸው ሰበኩለት ፤ ይህን ካደረጉ በኋላ ክርስትናን በቀላሉ እስ ከዚህ ድረስ ሊያስፋፉ ቻሉ ።

በአፍሪካም ወንጌልን የሰበኩ ሰባክያን የሕዝቡ እራስ (አለቃ) የሆነው ከተቀበለ የተቀሩት ነገዶች በቀላሉ እንደሚቀበሉት ስለሚያውቁ በመጀመሪያ ወንጌልን የሚሰብኩት ለሕዝቡ ወይም ለነገዱ መሪ ነበር ። መሪው ከተቀበለው ሕዝቡም ይቀበለዋል ። ለዚህ ነው እኛም ለኮሚኒስት አለቆች በድፍረት የም ንሰብከው ።

ማኦ ሴቱንግ ወይም ብሬዥኒቭ ክርስቲያኖች ቢሆኑ ተከታዮቻቸውም በቀላሉ ይሆናሉ ።

## ኮሚኒዝምን በመንፈሳዊ ይዞታ እንዴት ልን ዋጋ እንችላለን

ኮሚኒዝም ማንንም ደስተኛ አያደርግም ፤ እኔ እራ ሴ ብዙ የኮሚኒስት አለቆችን አውቃለሁ ደስታ የለሽ ሰዎች ናቸው ። ታላቅ የጭንቀት ቀንበር በላያቸው ነው ። ያን ቀንበር ሊሰብር የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው ። ኮሚኒስቶችን በክርስቶስ ወንጌል ማሸነፍ ምናልባት ዓለምን ከኑክሊየር ጦርነት ማዳን ሊሆን ይችላል ። ሰዎች ዳቦን ሳይጠግቡ ካፋቸው የጦር መሣሪያን በብዛት ያከማቻሉ ይህንንም ማለት ወንጌልን ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች መስበክ ዓለምን «ዓለም አቀፍ» ከሆነ ጭንቀት ሊያድናት ይችላል ። እነሱን ወደ

ወንጌሉ የምሥራች መጥራት ጌታንና የሰማይን መል
አክት ያስደስታል ። ይህን ማድረግ ቤተክርስቲያንን
በድል ጕዳና መምራት ነው ። ጨካኝ ጕሣዎች በብ
ዛት በነበሩባቸው ቦታዎች ማለት እንደኒው ጉኒያ
ማድካስካር ፡ እና ሌሎችም ብዙ ክርስቲያኖች ሊፈሩ
በት ከቻሉ ዛሬም የሩሲያና የሌሎችም ኮሚኒስት አገ
ሮች የወንጌል ዘር እንዲዘራባቸው ለም ምድር ሊሆኑ
ይችላሉ ።

አስተውሉ! እግዚአብሔር የለም ይሉ የነበሩት
ብዙ ሰዎች ዛሬ በእግዚአብሔር ፍቅር እየተቃጠሉ
ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ይታገላሉ ፤ እኔ
ራሴ የአምላክ መኖርን የምክድ «ኤቲስት» ነበርኩ፤
ዛሬ ግን እኔ ቀድሞ እል እንደነበረው እግዚአብሔር
የለም በሚሉ መሃከል መኖሩንና ለሰው ልጆች ያለው
ዓላማ በልጁ አምነው የዘለዓለም ሕይወትን ያገኙ
እንደሆነ አስተምራለሁ ። በጌታ ያመኑ ክርስ
ቲያኖች ጌታን በጣም ይወዳሉ ። ምክንያቱም የበደ
ላቸውን ይቅርታ ሁሉን ከሚችል አምላክ ስላገኙ ነው።
ምንም እንኳ የሰው ልጆች በዘር ፥ በነገድ ፥ በቋንቋ
በሃይማኖትና በአስተሳሰብ የተለያዩ ቢሆኑም በእግ
ዚአብሔር ፊት ሁሉም ተመሳሳይ ደረጃ አላቸው ።
እሱ ያለም ልጆችን ሁሉ ከአንድ አፈርና ደም ፈጥ
ሮአቸዋል ። በርሱ ፊት ታላቅና ታናሽ ሕዝብ የለም።
ለተለየ ጕሣ የተለየ ዓላማ የለውም ።የክርስቲያን ወንጌላው
ያን መልእክት በዱር ለሚኖሩ ነገድ ብቻ መሆን የለ
በትም ። በተለይም ወደኮሚኒስት ምድር ማተኮር ይኖ
ርባቸዋል ። ኮሚኒስቶች ካመኑ ኮሚኒዝምን ባስፋፉበት
ቅናት ክርስትናንም ሊያስፋፉ ስለሚችሉ ነው ። የክ
ርስቲያኖች መሪ የሚሆን ክርስቶስ አገልግሎቱን በመ

ንደሮች ብቻ አልወሰነም ፤ የወንጌሉን ውጋጋን የዓለም መንፈሳዊ እንቅስቃሴ መዲና በምትሆን በኢየሩሳሌምና በከተሞችዋ ሁሉ አወጀ ፤ ተከታዮቹንም «ሂዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመኑ....... ይድናሉ» ሲል አዘዛቸው ።

የጌታውን ፈለግ የተከተለ ጳውሎስ ወንጌልን በይሁዳ ምድር በሰማርያ ብቻ እንዲወሰን ስላልፈቀደ ራሱን መስዋዕት በማድረግ እስከ ሮም ድረስ እንዲስፋፋ ይተጋ ነበር ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቶስ ስለተነገረለት ተስፋ እንዲሁ ይላል ፤

«የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል» እኛም ግን እባቡን ሆዱን እየረገጥን እንዲስቅና እንዲያሾፍብን እናደርገዋለን ፤ ራሱ ያለው ግን በመስኮብና በቻይና ነው ። በቱኒዝ ወይም በማድጋስካር አይደለም ፤ የመላው የወንጌላውያን ዓላማ ዓለምን በወንጌል ማዳረስ መሆን አለበት ። የጌታን ሥራ ማለት ወንጌልን የምንሰብክ ሰዎች በችልተኝነት መሥራትን እንተው ፤ በችልተኛ ሰው የተሠራ ሥራ ውጤቱ አያምርም መጽሐፍ ቅዱስ «የጌታን ሥራ በችልተኝነት የሚሠራ የተረገመ ይሁን» ይላል ።

ቤተ ክርስቲያን በፕላኗ ውስጥ የኮሚኒስትንም ዓለም ብታስብ ምንኛ መልካም ነው!

ጦርነት ሁል ጊዜ በመከላከል ሳይሆን በማጥቃትም መሆን ይኖርበታል ። ቤተክርስቲያን ግን እስከ አሁን ድረስ ከኮሚኒዝም ጋር ባደረገችው ውጊያ የምትጠቀመው በመከላከል ብቻ ነበር ። ቢሆንም

ድሉ የእርሷ አልሆነም ። አሁን ግን ዓላማዋን ለውጣ በመከላከልና በማጥቃት ልትዋጋ ይገባታል ውጤቱም ያማረ ይሆናል ፤ ክርስቲያኖች ሆይ (አምላካችንን ይዘን የመላውን የኮሚኒስት ዓለም በወንጌሉ ለማጥ ለቅለቅ እንታገል ። ይህን ማድረግ እንድንችልም ድሉ የወንድሞቻችን እንዲሆን በጸሎት እንርዳቸው ፤ አም ላካችን ፀሎትን ይሰማል ። ለጌታችን የብረት አጥር መስበር ቀላል ነው ።

የቀደመች ቤተክርስቲያን በእምነትና በድፍረት ትሠራ ነበር ፤ በዚህም ድልን አገኘች ፤ እኛም ዛሬ ወን ጌልን የምንሰብክ የቀደሙ አባቶቻችን በጥበብ ወን ጌልን ከሰበክን በአጭር ጊዜ ውስጥ መላውን ዓለም በወንጌል ለመለወጥ እንችላለን ።

በምዕራብ ያሉትን አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዳነጋገርኳቸው ለኮሚኒስት ተከታዮች ወንጌልን ለማዳረስ ምንም አቅድ የላቸውም ። ከዓላማ ቸው አውጥተውታል ። ጌታ ግን ወንጌልን ለተለዩ ሕዝብ ወይም ነገድ እንዲሰብክ አላስተማረም ። «ወደ ዓለም ሂዱና ...» እነዚህ ሰዎች ኮሚኒስቶችን ከአቅዳቸው ሠረዙዋቸው ።

እርግጥ ሰው ማመን አለበት ። ማመን መልካም ነገር ነው ። እምነትን በሥራ መግለጽ ግን አብልጦ መልካም ነው ። እውነተኛ አማኝ ለዚያ ላመነበት ነገር ሊሞት ሊገደል እንኳ የሚደፍር ነው ። ጳውሎስ ያምን ነበር ግን እምነቱን በሥራ የገለጸ ነው ። እንዲህ ዓይ ነቱ ቆራጥነት በቀደሙት ክርስቲያኖች ላይ ነበር ። የዛሬ ወንጌላውያን ግን ማመናቸውን መናገር ደስ ይላ ቸዋል ፤ ያመኑትን ግን በሥራ ላይ ሊያውሉት አይወ

ዱም ፤ ከምዕራባውያን የተረዳሁት ትልቁ ነገር ኮሚኒስቶችን አይወዱዋቸውም ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን እነሱን ወደክርስቶስ ወንጌል ብርሃን ለማምጣት ምንም ጥረት አለማድረጋቸው ነው ።

በቡዲስቶች ፣ በእስላሞችና በአይሁዳውያን መካከል የሚሠሩ ብዙ ወንጌላውያን ልከዋል ።

ካሪ ሕንዶችን ፣ ሐድሰን ቴለርም ቻይናውያንን ፣ በመውደዳቸው የደኅንነትን ወንጌል ሰበኩላቸው ። ስለወደዱዋቸውም ያ በእነርሱ ላይ ያላቸው ፍቅር ደኅንነትን እንዲሰብኩላቸው አነቃቃቸው ። በዚህም ብዙ ክርስቲያኖችን ለማፍራት ተቻለ ። እነሱን ግን ኮሚኒስቶችን አይወዱዋቸውም ።

ብዙ ጊዜ ፍቅርን ማሳየት ሲገባቸው ጥላቻን ማሳየታቸው በአጉል ዘለፋና ትችት መዋጋታቸው ኮሚኒስቶችን ይበልጥ ክርስትናን እንዲጠሉ አድርጎቸዋል ።

ኮሚኒስቶችን በወንጌሉ ኃይል ክርስቲያን ካላደረግናቸው እነሱ እኛን ኮሚኒስቶች ያደርጉናል ።

## የታሪክ ማስረጃነት አይረሳ

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስትና በግሩም ሁኔታ በሰሜን አፍሪካ ተስፋፍቶ ነበር ። ከዚያም ቅዱስ አውጉስጢኖስን ፣ ቅዱስ አትናትያስን ፣ ቅዱስ ሳይፕሪንን ፤ ቅዱስ ቴርቱሊያንን ፣ የመሳሰሉት የሃይማኖት መምህራን ተገኙ ።

በሰሜን አፍሪካ የነበሩት ክርስቲያኖች የዘነጉት ነገር ቢኖር እስላሞችን ወደክርስትና ማምጣት ሲኖር ባቸው ቸል ማለታቸው ነው ። እንዲያውም በጥቃቅኑ ዶክትሬን እየተለያዩ እርስ በርሳቸው ይከራከሩ ነበር ፤ ስለዚህም ዛሬ ያ ቀድሞ የክርስቲያን ምድር የነበረ ውን አገር እስልምና አጥለቅልቆታል ። ክርስትናም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አካባቢ የነበረውን ኃይል ሊያ ስመልስ አልቻለም ። እስኪ ከታሪክ እንማር!

በሪፎርሜሽን ጊዜ ሃስ ፤ ካልቪን ፤ ሉተር ሆነው ሕዝቡን በኢኮኖሚና በፖለቲካ ኃይል እየጨቆነ ይገዛ ከነበረው ከጳጳሱ ተፅዕኖ ነፃ ለማውጣት በአንድ ዓላማ ተነሱ ። ዛሬም የክርስትያን ቤተክርስቲያን ጨካኝ ከሆኑ የጨለማ ገዢዎች አስተዳደር ሰዎችን ነፃ ለማው ጣት መሥራት አለባት ። በዚህ በተቀደሰ ተግባር ክር ስቲያኖች ነን የሚሉ ሁሉ ሊተባበሩ ይገባቸዋል ። እኔም የክርስቲያኖችን ሕሊና ለዚህ በጎ ተግባር አነ ቃንቅ ዘንድ ተላክሁ ። ይህን ልናደርግ የምንችለውን በጥላቻ ኃይል አይደለም ። ይህንን ካልን ከጥላቻ የሚ በልጥ ኃይል ኒውክሊዬር ከኮሚኒስቶች ጋር ነው ። ከነሱ ጋር ወታደራዊ ጦርነትን ማወጅ ምናልባት ብዙ ሕዝብን የሚያስፈጅ አዲስ ዓለም አቀፍ ጦርነትን ማስነሳት ይሆናል ። እኛ ካንሰር ፤ ሣንባ በሽታ ፤ ኮሌራ ፡ ውንብድና ፤ ሌብነትን የመሳሰሉትን የማኅበራዊ ኑሮ ጠላት የሆኑትን እንዲጠፉ እንሻለን ። ይህንንም ለማ ድረግ በሰዎች አእምሮ መጥፎ ትምህርት የሚተክለ ውን ሐሰተኛ ፍልስፍና አስቀድመን ማጥፋት አለብን ።

ኮሚኒዝምን ሊገለብጥ የሚችል አንድ ኃይል ብቻ አለ ። ያም ኃይል የአረማውያን ምድር የነበረች ው ሮምን የገለበጠ ነው ። እሱም የጨለማ ኃይሎች

እንኳን ሊያጠፋት የማይችሉት የወንጌል ሰደድ እሳት ነው ።

ቲቶና ቫይኪንግ የተባሉትን ጨካኞችና ደም አፍሳሽ ሕዝቦችን የገለበጠ ምን ኃይል ነው? የወንጌል ኃይል አይደለምን? ያም ወንጌል ዛሬ በቆራጥ ክርስቲያኖች በኮሚኒስት አገሮች ይሰበካል ። እነዚያን ወንድሞች መርዳት ከሥቃያቸው መካፈል ብቻ ሳይሆን ከሚያገኙትም በረከት ተሳታፊ መሆን ማለት ነው ። ይህንንም ማድረግ የተራ ክርስቲያኖች ተግባር ብቻ ሳይሆን በሥልጣን ላይ ያሉ ክርስቲያኖችም መሆን ይገባዋል ።

ጆርጂሁ ደጅ የተባለው የቀድሞ የሮማንያ ጠ/ሚኒስትር ለብዙ ጊዜ የክርስቲያኖች አሣዳጅ ሆኖ ከኖረ በኋላ ራሱ በክርስቶስ አምኖ ኃጢአቱንም ሁሉ ተናዞ የሕይወት ዓላማውንም ለውጦ እስኪሞት ድረስ በክርስትና ኃይማኖት ፀንቶ ቆመ ። በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ብዙ ክርስትናን የተቀበሉ ክርስቲያን ወንድሞች አሉን ። ይህም እየበዛና እየተስፋፋ ነው ።

ከዚያ በኋላ መላውን የኮሚኒስት አባሎች ለመለወጥ ተስፋ ይኖረናል ። ያም ለውጥ ቲቶ ወይም ጉሙልካ እንዳደረጉት ሳይሆን ከዚያ የሚበልጥ ይሆናል ። እነሱ ለውጥ እንደሚያመጡ ሰበኩ ። እኛም ለውጥ እንደምናመጣ እንሰብካለን ፤ ቢሆንም እኛ በምናመጣው ለውጥና ኮሚኒስቶች ባመጡት ትልቅ የመለያየት ገደብ አለ ።

የእነሱ ለውጥ በሰዎች መካከል የወንድማማችነትን ፍቅር እንደሚያመጣ አስተማሩ ፤ ሆኖም ፍርቅመሆኑ ቀርቶ እርስ በርሳቸው ውሻ በአጥንት እንደሚጣላ ይጣላሉ።

ምድርን ወደ ኤደን ገነት ለመለወጥ ተነሱ ። ይህም ሰማያዊ መንግሥት አለ ብለው በሚያምኑት ላይ ለመዘበት ነው ። ዛሬ ግን ከካፒታሊስት አገሮች ስንዴ እስኪላክላቸው ድረስ ረሃብተኞች ናቸው ። ኮሚኒስቶች ምንም እንኳ አለቆቻቸው እንደሚሳሳቱና እንደተሳሳቱም ቢያውቁ በአለቆቻቸው ላይ ያላቸው እምነት ታላቅ ነው ፤ እነሱ ያለአለቆቻቸው ፤ «አውራ የለሽ ንቦች » ናቸው ።

በመላው እግዚአብሔር የለም በማለት በማቴሪ ያል ብቻ ራሳቸውን ደስተኞች ሊያደርጉ በሚጣጣሩ ሰዎች ልብ አንድ ባዶ ቦታ አለ ፤ ያም ባዶ ቦታ በክ ርስቶስና በወንጌሉ ምሥራች ብቻ ሊሞላ ይችላል ። የሰው ነፍስ በተፈጥሮ እግዚአብሔርን ለማግኘት ትጥራለች በወንጌሉ ውስጥ ሰዎችን ሊማርክ የሚችል አንድ የፍቅር ኃይል አለ ፤ ያ ኃይል ሲሠራ አይቼአለሁ ፤ ሊሠራ እንደሚችልም አምናለሁ ፡ በእስር ቤት የሚሰ ቃዩ ክርስቲያኖች ለሚያሳዩዋቸው ፍቅርን ያሳያሉ ። እጅግ ታላቅ በሆነ ስቃይ ውስጥ ሳሉ ፤ የክርስቶስን ፍቅር ያንፀባርቃሉ ። የክርስቲያኖች ፍቅር በዘር ፤ በቀ ለምና ፤ በነገድ ፤ መለየት የለበትም ፤ የሁላችን ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር ምንም እንኳ ከሰው ልጆች ውስጥ የሚታዘዙትና የማይታዘዙት እንዳሉ ቢያውቅም ክርስ ቶ እንዳስተማረው «ፀሐይን በጻድቃንና በሐጥአን ላይ ያበራል» የክርስቲያኖችም ፍቅር እንደዚህ መሆን አለበት ። የብዙ ክርስቲያኖች ገዳይ ቢሆኑም ኮሚኒስ ቶችን መጥላት የለብንም ። ጌታ «ጠላቶቻችሁን ውደዱ» ሲል «ወንድሞቻችሁን ጥሉ» ማለቱ አይደ ለም ።

በጀርመን ያሉ «የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንና» «የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለችግረኞች መርጃ የሚ ሆን ፻፷፩ ሚሊዮን ብር ለተራቡ አገሮች መርጃ እን ዲሆን ለገሱ ፤ እርግጥ መለገሳቸው መልካም አደረጉ ። በዓለም ላይ ብዙ የተራቡ ሰዎች አሉና ። ቢሆንም በኮሚኒስት ምድር ከሚሰቃዩ መጠጊያ አጥተው ከሚንከራተቱ የክርስቲያንን ሰማዕታትን ልጆች ያህል የተራቡ መኖራቸውን እጠራጠራለሁ ። እነዚህ የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉላቸው ይጠባበቃሉ ።

በአሜሪካ ፤ በብሪቲሽና በስካንድኔቪያን ያሉ ክርስ ቲያኖች ለችግረኞች መርጃ የሚሆንን ገንዘብ ተረዳድ ተው ቢያዋጡ ለያንዳንዱ በችግር ላይ ላለ ሰው በቂ እርዳታን ሊሰጡት ይችላሉ ።

ክርስትና ገና ሕፃን በነበረበት በአንደኛው ክፍለ ዘመን «ክርስትና የአይሁድ ብቻ ነው ወይስ የአሕ ዛብ» የሚል ጥያቄ ተፈጥሮ ነበር ፤ መልሱም በሐዋር ያትና በዘመኑ በነበሩት መልካም መምሕራን ተሰጠ ።

ዛሬ ደግሞ ያ ጥያቄ ራሱን ትንሽ ለወጥ አድ ርጎ ተነስቶአል ፤ ብዙዎች ክርስትና ለአንድ ለተለዩ ሕዝብ አደራ የተሰጠ ይመስላቸዋል ። እንዲህም ብለው ያስተምራሉ ፤ ዳሩ ክርስቶስ የአይሁድ ፣ የአሜሪካ ፣ የኢ ንግላንድ ፣ ወይም የሌላ ዲሞክራቲክ አገር ብቻ ሳይሆን መላውን የዓለም ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር የሚመራ «የመዳን መንገድ» ነው ። እርሱ በተሰቀለ ጊዜ አንዱ እጁ ወደ ምሥራቅ ሌላው ወደ ምዕራብ ነበር ፤ የወገንን ልዩነት ሳያደርግ መላውን የሰው ልጆች «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደእኔ ኑ እኔም እረፍትን እሰጣችኋ ለሁ» እያለ ይጠራል ።

የአይሁድ ንጉሥ ብቻ ሳይሆን የአሕዛብም ነው ። የምዕራባውያን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ቢቀበሉት የኮሚኒስቶችም ነው ፤ ጌታ እራሱ ሐዋርያቱን እንዲህ አላቸው «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ።

ክቡር ደሙ ለሁሉ ፈሰሰ ። ሁሉም ስለእርሱ ሊሰሙና በርሱም ሊያምኑ ይገባቸዋል ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ለኮሚኒስቶች ያላቸው አስተያየት ከክርስቶስ በጣም የተለየ ነው ። ይጠሉዋቸዋል ። ያ ጥላቻ ግን ምንም ሊያደርጋቸው አልቻለም እንዲያውም ይበልጥ አስፋፋቸው ፤ ሊለውጣቸው የሚችለው ፍቅር ነው ።

## ከተፈታሁ በኋላ

ከእስር ቤት ከተፈታሁ በኋላ ሚስቴን አገኘኋት ፤ ለወደፊቱ ያለኝን እቅድ ነገርኳት ። የሱዋም እንዲኔ ነበር ፤ ጌታ ስለራሱ ዳግመኛ መመለስ ሲናገር «የሰው ልጅ (እኔ) በማታስቡት ጊዜና በማትገምቱት ሰዓት አመጣለሁ» ሲል አስተምሮ ነበር ። እኛም በችግር ውስጥ በነበርንበት ጊዜ ባላሰብነውና ባልጠረጠርነው ጊዜ ወደእኛ መጣ! የእስር ቤቱም ግድግዳ እንደ ዕንቁ አንፀባረቀ ምንም እንኳ ሥጋችን የሥቃዩን ሕመም ቢሸከምም ነፍሳችን ግን በጌታ ሐሤት ታደርጋለች ። አንድም እንኳ የመሣሪያ ውጊያ እንዲኖረኝ አልመኝም ። ዳሩ ግን ምኞቴ የክርስቶስ ማደሪያ የሚሆን ሕያው ቤተ መቅደስን ለመገንባት ነው ። ያም በርሱ አምነው ልባቸውን የሚከፍቱለት የአማኞች ልብ ነው ።

ምንም እንኳ ከእስር ቤቱ ስቃይ ከወጣሁ ብዙ ዓመታት ቢያልፍም ዛሬ ክርስቲያኖች ያለባቸውን ኃላፊነት ጥለው ሳይ በይበልጥ ያሳዝነኛል ። በተለያዩ አገሮች ያገኘኋቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለክርስ ቶስ ወንጌል ክብር ከመቆም ይልቅ በባለጸግነት ምኞት ተይዘዋል ። ከዚህም ሌላ ሃይማኖታውያን ነን የሚሉ አንዳንዶች ከመካከላቸው ክርስቲያን ወንድሞቻቸውን ለእሥራት አሣልፈው ይሰጣሉ ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተብለው ከተሾሙት ብዙዎች የተሾሙት የእግ ዚአብሔርን ሕልውና በሚቃወሙ በኮሚኒስቶች ነው ። የቤተክርስቲያን መሪዎች የተባሉትም ዓላማቸው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ሳይሆን ፈጽሞ እንድትወድቅ ነው ። ከምዕመናን አንዱ ወንጌልን እንደሚያስፋፉ ካወቀበት የቤተክርስቲያኑ መሪ ራሱ የሚስጢር ፖሊ ሶች ጠቋሚ ስለሆነ ያስይዘዋል ።

በየመንደሩ የኮሚኒስት መሪዎች መልእክተኞች አሉ ። ሲያስፈልግም ማንንም ቄስ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ጠርቶ ማን አዲስ ሰው ወደ ቤተክር ስቲያን እንደመጣ ማን ቅዱስ ቁርባንን እንደ ወሰደ ማን ሃይማኖትን ለማስፋፋት ይበልጥ እንደሚሠራ ይጠይቅና ያስፈለገውን ሊያስር ፣ ሊቀጣ ይችላል ። (ይህን ሁሉ አመፅ ነግሶ ሳይ ጌታ እንዳለው «የዓ መጽ ርኩሰት በተቀደሰችው ቦታ መቆሙን» አስተዋ ልኩ ።

የታሪክ ማስረጃነት እንደሚነግረን ምን ጊዜም መጥፎና መልካም የሃይማኖት መሪዎች በቤተ ክርስቲ ያን ተነስተዋል ። ዛሬ ግን በክርስትና ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው ይደረጋል ፤ ካህናትና ቀሳውስት የእግዚአብሔርን ሕልውና በሚክዱ በኮሚኒስቶች

ይሾማሉ ። ምን ለማድረግ? እምነትን ለማስፋፋት? አይደለም እምነትን ከሥሩ ነቅሎ ለመጣል ።

ሌኒን እንዲህ አለ «እያንዳንዱ» ሃይማኖታዊ ሃሳብ፤ እጅግ አደገኛ ከመሆኑ የተነሣ የበሽታ አይነቶችና ማንኛውም ዓይነት አመጽ ሃይማኖት ከሚያመጣው ጠንቅ ሊወዳደር አይችልም» የኮሚኒስት ፓርቲ የተባሉት ሁሉ ፤ ሌኒናውያን ወይም ሌኒን የተናገረውን በሞላ የሚቀበሉ ናቸው ፤ እንደነሱ አስተያየት ሃይማኖት ከሣንባ በሽታ ከካንሰር እንዲሁም ከማንኛውም የአባለ ዘርዕ በሽታ ይልቅ መጥፎ ነው ።

ታዲያ ፤ እንዲህ ያለ ግምት ባላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩ ካህናት ቢሾሙ ውጤቱ ምንድ ነው? ውድቀት ። ሕፃናትን ገና በልጅነታቸው እግዚአብሔር የለም በሚል አጉል ፍልስፍና ይመርዙአቸዋል ።

—

በዋና ከተማችን በቡካሬስት ውስጥ በቤተክርስቲያን ወይም በእሁድ ት/ቤት ውስጥ ወጣቶችን ለማየት አይቻልም ፤ ኮሚኒዝምን የምጠላው በኔ ላይ ስለፈጸመው ተግባር ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር ተቃዋሚ በመሆኑ ነው ።

የገዛ መሬታቸው በኮሚኒስቶች ተወስዶባቸው በገዛ መሬታቸው ከተዘራው እህል እንኳ በደንብ የማያገኙ ብዙ ሰዎች መጥተው አነጋገሩኝ ። ዳቦ ሳያገኙ ጦም የሚያድሩበት ቀን አለ ። ሕፃናቶቻቸው ወተት የላቸውም ። አገራችን ግን የቀደመው ከነዓን እንደነበረው ሁሉ ለም ምድር ናት ። እንዲህ ባለው አስተዳደር ስር መሆን ብዙዎችን ሌቦች እንዲሆኑ አደረጋቸው፤ በገዛ መሬታቸው ከተዘራው እህል ይሰርቃሉ ።

በፋብሪካ ከሚሠሩ ከአንዳንድ ሰዎች ላይ በካፒታሊስት አገሮች ላይ እንኳ የሌለ የጉልበት ሌብነት ይፈጸምባቸዋል ።

ሕዝቡ በብዙ መንገድ መብቱን የተነፈገ ነው። ይህና ሌሎችም ይህንን የመሳሰሉ ዓመፅ ኮሚኒዝምን እንድጠላው አደረገኝ ።

አንድ ቀን ቀድሞ አብረውኝ ታሥረው የነበሩትን አምስት የእምነት አርበኞችን አገኘሁ ፤ ከእስር ቤት ከወጡበት ጊዜ አንስቶ ወንጌልን ለማስፋፋት ይተጉ ነበር ፤ እኔንም የሥራቸው ተካፋይ እንድሆን ጋበዙኝና በሚስጢር ወደሚያደርጉት ስብሰባ ሄድኩ ፤ እዚያም አብሬአቸው መጽሐፍ ቅዱስን አጠናና በእጅ ከተጻፈ የመዝሙር መጽሐፍ ዝማሬን ለአምላካችን እናቀርባለን ። ታላቁ ቅዱስ አንቶኒዮ የጾምና የጸሎትን ኑሮ ለመኖር ከሰው ተለይቶ ከነበረበት ምድረ በዳ ስለክርስቶስ መለኮታዊነት በአርዮስና በአትናትዮስ መካከል ክርክር እንደተነሣ በሰማ ጊዜ እውነት እንድታሸንፍ ለመርዳት ሲል እንደመጣ አስተዋልኩ ። የክርስቶስን የጳውሎስንና እንዲሁም የታላላቅ የእምነት ሰዎችን ፍለጋ በመከተል ስለእምነት እስከ መጨረሻው መዋጋት እንደሚኖርብኝ ተረዳሁ ፤ ለዕውነት መዋጋት አለብኝ ፤ ታዲያ ያ ምን ዓይነት ውጊያ ይሆናል?

ክርስቲያኖች በእስር ቤት ለሚያሰቃዩዋቸው ልብ ላይ ምን ያህል የፍቅር ሰዎች እንደሆኑ ፤ አስገንዝቦአቸዋል ፤ የክርስቲያኖች ታላቁ ዓላማ ኮሚኒስቶችን ክርስቲያን ሲሆኑ ማየት ነው ።

የኔ ምኞት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ በሆነው በወንጌል ሃይል ኮሚኒዝምን ስትገለባብጠው መመልከት

ነው ። ይህም ፍላጎቴ ፍጻሜ እንዲያገኝ የምፈልገው በሩማንያ ብቻ ሳይሆን በሞላው በኮሚኒስት አገሮች ነው ። ምዕራባውያን ክርስቲያኖች ግን በብዙ መንገድ ቸልተኞች ሆነው አገኘኋቸው ።

ሁለቱ የታወቁት የኮሚኒስት ጸሐፊዎች ዳንኤልና ስኒቪስኪ ስላደረጉት ጥፋት የሞት ፍርድ በተፈረደባ ቸው ጊዜ በዓለም ዙሪያ የነበሩ ጋዜጠኞች ነገሩን ነቀፉ ፤ በዓለም ዙሪያ ያለች ቤተክርስቲያን ግን በኮ ሚኒስቶች አገር በክርስቲያኖች ላይ የሚደረገውን በደል ባታውቁም ስለጉዳዩ እርምጃን ከመውሰድ ቸልተኛ ናት ።

ለመሆኑ! ክርስቲያናዊ ጽሑፎችን በትናችኋል በመባል እንዲታሠሩ የተፈረደባቸው ፤ እነኩዝየክ ፤ እነክራንቫልዲ ፤ እነፕሮኮፊቭ ፤ የመሳሰሉት የእምነት አርበኞች የት እንደገቡ ማን ያውቃል?

አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች ነን የሚሉ ምንም እንኳ በኮሚኒስት አገሮች ላሉ ክርስቲያኖች የእምነት ነፃነት እንደሌላቸው ቢያውቁም ሙሉ ነፃነት እንዳለ አድርገው ያወራሉ ፤ እኔ ወንጌልን መስበክ አውቅበታ ለሁ ለብዙ ዓመታትም ሰብኬዋለሁ ቢሆንም ማር ሲነሣ የእሬት መራርነትም መዘንጋት የለበትም ።

ታዲያ አንዳንዶች «ንጹሕ ወንጌል» ስበክ ይሉ ኛል ፤ ይህንንማ እራሳቸው የኮሚኒስት መሪዎች ወንጌ ልን በሌላ አገር ስበክ ብቻ ስለኮሚኒዝም እንዳታወራ ብለው መክረውኛል ። ለመሆኑ ይህ «ንጹሕ ወንጌል» የሚሉት ምን ዓይነት ነው? ለመሆኑ የመጥምቁ ዮሐ ንስ ስብከት ንጹሕ አልነበረም? «ንስሐ ግቡ መንግ ሥተ ሰማያት ቀርባለችና» ባለበት አፉ ሄሮድስን

ይሠራው ስለነበረው አመጽ ነቅፎታል ፤ ስለዚህ እራሱ እንዲቆረጥ ፈረደበት ።

ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ላይ ሐሰተኞች ጻፎችና ፈሪሣውያንንም «ወዮላችሁ! እናንተ ጻፎችና ፈሪሣውያን» ሲል የሚጠብቃቸውን ቅጣት ገልጾ አስረድቶአቸዋል ። ታዲያ ይህ ንጹሕ ወንጌል አይደለ ምን? ክርስቶስን ለመስቀል ያበቃው የእግዚአብሔርን ወንጌል መስበኩ ብቻ ሳይሆን የሃሰተኞችንና ከእግዚ አብሔር ቃል ይልቅ የራሳቸውን ወግ ማክበር የሚወ ዱትን የወገኞችን ሥራ በማውገዙ ነው ።

ስለዚህ እኛ በዘመኑ ወንጌልን የምንሰብክ ሁሉ ሃሰትን ማውገዝ ተገቢ ተግባራችን ነው ። የእሬትን መራርነት ለማያውቅ ሰው እንዴት የማርን ጣፋጭ ነትን ለማስረዳት ይቻላል ። ብርሃን ከጨለማ እሳት ከውሃ ሊዛመድ እንደማይችል ሁሉ ከኮሚኒዝም ጋር የሚዛመድ ወንጌል ንጹሕ አይደለም ፤ ኮሚኒዝም ኃይሉን ባሳረፈበት አገር ያሉ ክርስቲያኖች በቆራጥ ነት ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ኮሚኒዝምን ያወግ ዛሉ ። ይህንንም ማድረጋቸው በሕይወታቸው በልጆቻ ቸውና በንብረታቸው ምን እንደሚደርስባቸው በማ ወቅ ነው ።

እኔ ኮሚኒዝምን አወግዛለሁ ። ምክንያቱም ብርሃን የሆነው የወንጌሉ ምሥራች ቃል ተቃዋሚ ነውና። ኮሚኒዝምን አወግዛለሁ ስል ብዙ ጊዜ ፀረ ኮሚኒስቶች እንደሚያደርጉት አይደለም ።

ሂትለር ጸረ ኮሚኒዝም ስለሆነ ብዙዎችን ገደለ ። ተቃውሞውን በጦርና በመሣሪያ ብርታት ገለጸ ።

እኛ ግን እንዲህ አይደለንም ። ተቃውሞአችን በፍቅር ነው ፤ የሥጋ መሣሪያ ኃይልን ስለማናምንበት እንጠቀምበትም ።

ጌታችን እንዳደረገው ሁሉ «ኃጢአትን እንጠላለን ኃጢአተኞችን ግን እንወዳለን»

## ከእስር ቤት ይልቅ ያሰቃየኝ

በኮሚኒስቶች እስር ቤት ከተጐዳሁት ይልቅ በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አጉል ሥራ የተሰቃየሁት ይበልጣል ። ከሚያሳዝኑኝም ምክንያቶች ትልቁ ስለክርስቶስ የሚሰቃዩትን ክርስቲያን ወንድሞቻቸውን መዘንጋታቸው ነው ።

በአንዳንድ ቦታ የክርስቲያኖች ኑሮ ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ እንደሆነው ሁሉ እራሳቸውን የሚያስጠጉበት ቤት የላቸውም ። ክርስቲያኖች ቤትን ለመሥራት አይችሉም ፤ ለምን ሊረባቸው? ቢሠሩም እንኳ በኮሚኒስቶች እንደሚወሰድ ያውቃሉ ፤ በዚያ ያለች ቤተ ክርስቲያን የተጠቃች ብትሆንም ደካማ ምዕመን አልነበረባትም ፤ አንድ የላቲን ተረት እንዲህ ይላል ። «የተራቆቱ የተራቆተውን ክርስቶስ ይከተላሉ» በእርግጥ ክርስቲያኖችም ከዚያ ሁሉ ሥቃይ ይህንን ሁሉ መርቆ ይሰጣቸዋል ። ጌታቸውን ይከተላሉ እርሱ አስቀድሞ እንዲህ አለ ።

«ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም» እርሱ ጌታ መምህር ሲሆን ሳለ የቀመሰውን ተከታዮቹም መቅመስ እንዳለባቸው ሲያስረዳቸው ነው ።

የእነዚህ ክርስቲያኖች እምነት ጥንካሬ ከቀደሙት ክርስቲያኖች ጋር በብዙ መንገድ ተመሳሳይ ነው ። ሰባኪያኑ ከታወቀ የቲዎሎጂ ት/ቤት የተመረቁ ባይሆኑም የወንጌልን መልእክት አሰጣጣቸው መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ጥበብ የተሞላ ነው ፤ ምንም እንኳ «እግዚአብሔር ፍቅር» መሆኑን ቢያውቁም በእርሱም ታላቅ እምነት ቢኖራቸውም ብዙ ጊዜ ይራቡ ፤ ይጠሙ ፤ በልዩ ልዩ ሥቃይም ይሠቃዩ ነበር ። ቢሆንም የቀድሞው ኢዮብ «ቢገድለኝም እንኳ እሱን ከማመስገን አልቆጠብም» ብሎ እንደተናገረ ጌታ ኢየሱስም በመስቀል ላይ ተቸንክሮ በነበረበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔርን «አባት ሆይ» እንዳለው ሁሉ እነዚህም ክርስቲያኖች በደስታ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራና በጭንቀታቸው ጊዜ እንኳ ስለ ሁሉም ነገር «እግዚአብሔር ይመስገን» የማለት ድፍረት አላቸው ።

ምዕራባዊት ቤተክርስቲያን ግን እንዲህ አይደለችም ደክማለች ። አዝዋልድ እስፒንግሊር የምዕራባውያን ውድቀት በሚለው መጽሐፉ ምዕራባውያንን «ወድቃችኋል» እንዲያውም የመሞት ምልክት ታይቶባችኋልና ትሞታላችሁ ፤ ይህንንም ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ ። በመካከላችሁ ያለው ጥላቻ ፤ ካፒታሊዝም ፤ ጦርነት ፤ ብጥብጥ ፤ በመጥፎ ዓላማ ላይ የተመሠረተው ጋብቻችሁ ፤ የወጣቶቻችሁን አንጎል የሚመርዝ መጥፎ ትምህርታችሁ ፤ ሌብነት ፤ አመፅ የውነተኛ ፍርድ መጓደል ፤ በቅርቡ ምዕራባዊነት አገር እንደምትወድቅ ያመለክታል ። በታሪክ ውስጥ ገናና የነበሩት አገሮች እንደ አለክሳንደሪያ ፤ ግሪክና ሮምን የመሳሰሉት (የመሳሰሉ) ኃያላን መንግሥታት ከመውደቃቸው በፊት ዛሬ በምዕራባውያን አገሮች ላይ ገና በመታየት ላይ ያለው

ሁሉ ታይቶባቸው ነበር ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ወደቁ» ይላቸዋል ፡፡ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ነበር ፡፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በዕንቅልፍ ላይ ብትሆንም ኮሚኒዝም አልተኛም ፡፡ በሚያስደንቅ ኃይል የተኛችውን ቤተ ክርስቲያን ይዋጋታል ፡፡

በተለያዩ አገሮች ያሉ ቸልተኞች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የቲዎሎጂ ምሁራን ግን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማይረባ ክርክርን በመፍጠር ጌታ የጣለባቸውን አደራ ዘንግተዋል ፡፡

ማሆሜት ዳግማዊ በ፲፬፻፶፫ ዓ. ም. ኮኒስታንቲኖፕልን ከቦ ክርስቲያኑን ሕዝብ እስላም እንዲሆኑ በማስገደድ ብዙ ሕዝብን እያጠፋ ኃይሉን ሲያስፋፋ በዘመኑ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን በጊዜው አስፈላጊ ያልሆነ ክርክርን በመፍጠር «የቅድስት ድንግል ዓይን ምን ከለር አለው »

«መላእክቶችን ጾታቸው ምንድነው» በቅዱስ ውሃ ውስጥ ዝንብ ብትገባ ያ ቅዱስ ውሃ ዝንቢቱን ይቀድሳታል ፤ ወይስ የዝንቢቱ ርኩሰት ውሃውን ያረክሰዋል? እነዚህ የሃይማኖት መምህራን ይህን በሚመስል በጊዜው አስፈላጊ ያልሆነ ክርክርን በመፍጠር ባማረና በሞቀ አዳራሽ ውስጥ ሲነታረኩ እስልምና ኃይሉን ያስፋፋ ነበር ፡፡ በመጨረሻም ዛሬ ያቺ አገር ፈጽማ በእስልምና ትምህርት እስክትሞላ ድረስ የእስላም አገር ሆነች ፡፡

ዛሬም በብዙ የቲዎሎጂ ኮሌጆች ውስጥ ይህን የመሰለ አጉል ክርክርን አብዝተን እንሰማለን ፤ ይህም ኮሚኒዝም እግሩን ሰዶ እንዲንሰራፋ መልካም አጋጣሚ ሆኖለታል ፡፡ በአንድ ቤት ብዙ ሰዎች ተሰብስ

በው አንዳንድ ነገሮችን እያነሱ ሲከራከሩ አንዱ እንዲህ ያለ ጥያቄ ጠየቃቸው ። «ለምሳሌ በመርከብ ተሳፍራችሁ ስትሄዱ ወደአንድ ወደብ እንደደረሳችሁ መርከቢቱ በድንገት ልትወድም ሆነ ፤ በዚህ ጊዜ የመርከቡ ካፒቴን ተሳፋሪዎችን ከመርከቢቱ ቤተ መጽሐፍ የሚፈልጉትን መጽሐፍ እንዲወስዱና ባቅራቢያቸው ወዳለው ወደብ ሄደው ሕይወታቸውን እንዲያድኑ ፈቀደላቸው ። እናንተ በዚያች መርከብ ውስጥ ብትሆኑ የትኛውን መጽሐፍ ትወስዱ ነበር?» ቢላቸው አንደኛው መጽሐፍ ቅዱስን ፤ ሌላው የሼክስፒርን ድርሰት ፤ ሌላው የመድኃኒት ቅመማ መጽሐፍን በማለት ልዩ ልዩ መልስን ይሰጡ ነበር ። አንደኛው ግን ተነሥቶ እኔ እዚያ እመርከብ ላይ ብኖር ኖሮ የምመርጠው መርከብ ለመሥራት የሚያስችለኝን መጽሐፍ ነው ። ከዚያ በኋላ ወደሃገሬ ተመልሼ ያስፈለገኝን መጽሐፍ ለማንበብ እችላለሁ አለ ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በምትዋጋው ጠላቷ ላይ ኃይልን አግኝታ ድል የምታገኝበትን መንገድ መፈለጉ ከሌላው ሁሉ ተቀዳሚ ነው ። ጌታ «እውነትን ፈልጉ እውነትም ነፃ ያወጣችኋል» አለ ። ያንንም እውነት ለማግኘት ነፃነት ሊኖር ይገባዋል ። ቤተክርስቲያን ያንን የውነት ወንጌል እንዳትሰብክ ተከለከለች እንግዲህ እውነት ከወዴት ይምጣ?

በማያስፈልግ ነገር ከመከራከር ይልቅ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ኃይላቸውን አንድ አድርገው የቤተ ክርስቲያን ጠላት የሆነውን ሁሉ መዋጋት አለባቸው።

በሰኔ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ኢዜቬስታ የተባለው የሶቪየት ጋዜጣ አንድ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን መሪ የእርሱ በኃጢአት ስርየት ይገኝበታል በማለት ሕፃን ልጅን እንዲያርዱ አስተምረዛል ተብሎ እንደ

ተከሰሰ ገልጾ ነበር ። ይህም የክርስቲያኖችን ስም ለማ ጥፋት የተደረገ ከንቱ ወሬ ነው ።

በሩማንያ ውስጥ ታሥሬ በነበረበት ጊዜ ላዛር ሺስ የተባለ የ፴ ዓመት ሰው ልጃገረድ ገድለሃል ተብሎ ባልሠራውና ባላየው ወንጀል ይሠቃይ ነበር ። ከብዙ የሥቃይ ዘመን በኋላ ግን በነፃ እንዲወጣ ተደረገ ። ምንም እንኳ ከእስራት ቢፈታም እድሜውን ሁሉ በሽ ተኛ ሆነ ።

ማንም ጥሩ አስተዋይ የሆነ ሰው የሶቪየት ጽሑፍ ማደራጃ በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርገውን ክስ መሠ ረት የለሽ እንደሆነ ሊረዳ ይችላል ። ምዕራባዊት ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ በኮሚኒስት ዓለም ያለችውን ቤተክርስቲያን ጭንቀት ብታውቅም በጣም ቸልተኛ ነች ። በየቀኑ ብዙ ክርስቲያኖች በኮሚኒስቶች እየታሰሩ ወደማይታወቅ ቦታ ይወሰዳሉ ። ማንም ሊቀ ጳጳሱ ኒኮ ዲሞ ወንጌላዊው ኒኮላይና ጌለብ የት እንዳሉ አያው ቅም ።

በእስር ቤት በነበርኩበት ጊዜ ፋዘር ኢዮን የተ ባለ የሩማንያ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሃይማኖት እን ቅስቃሴ ፈቃድ መጠየቁ እንደጥፋት ስለተቆጠረበት አብሮኝ ታስሮ ነበር ።

በኮሚኒስት አገር ለሚጨነቁ ክርስቲያኖች በጣም አዝናለሁ ፤ የወንድሞቻቸውን ሥቃይ ለዘነጉት በሌላ አገር ስላሉ ቸልተኛ ክርስቲያኖች ደግሞ በጣም አድ ርጌ አዝናለሁ ።

ምንም እንኳ የሚደርስብኝን ባውቅም ቤተክርስ ቲያን ከኮሚኒስት ጋር በምታደርገው ውጊያ እኔ ራሴ

መሪ ልሆን ወስኜአለሁ ። ምናልባት አንድ ቀን ስለኔ መጥፋት ብትሰሙ የወሰዱኝ ኮሚኒስቶች እንደሆኑ እወቁ ። በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. በድንገት ጠልፈው እና ፓውከር የሚል የውሸት ስም ሰጥተው ወኅኒ አገቡኝ ።

ዛሬም ተመሳሳይ ድርጊት እንደሚፈፅሙብኝ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል ። ምንአልባት በአንድ ባልታወቀ ሰው ብገደል ያ ሰው በኮሚኒስቶች የተላከ መሆን አለበት ። ከአንድ ከታመነ የወሬ ምንጭ እንደሰማሁት ከተፈታሁ በኋላ ለአሜሪካ ጋዜጠኞች ባደረግሁት ግልፅ ንግግር በመቆጣት የሩማንያ ኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎች እንድገደል ትእዛዝ እንዳስተላለፉ ሰማሁ ። እንደገና ተይዤ ወኅኒ እንድገባና በዚያም ከቀድሞው የባሰ ቅጣት እንደተፈረደብኝም ከአንዳንድ ክርስቲያን ከሆኑ የሚስጢር ፖሊስ አባሎች ተነገረኝ ። አዎን ኮሚኒዝምን ማውገዝ ከቀጠልኩ የሚጠብቀኝን አውቃለሁ ። ቢሆንም የምሆነውን እስክሆን ድረስ ፀጥ አልልም ።

ከእናንተ ከአንባቢዎች የሚጠበቀው ግን ነገሩን በትክክለኛና በረጋ ልብ መመርመር ነው ። ብዙ ጥያቄዎች በአንባቢው አእምሮ ሊፈጠሩ ይችላሉ ። ለምንድነው ኮሚኒዝም ይህን ያህል የእምነት ተቃዋሚ የሆነው? ለምንድነው በምስራቅ ጀርመን ያሉ ሰዎች በሽቦ ከተከበበችው ከተማ ለመውጣት ሲጥሩ ከነቤተሰቦቻቸው የሚረሸኑት? የሚሰቃይ ሕዝብ መድኅንን ይሻል ።

በምዕራብ አገር ብዙ የቲዎሎጅ ት/ቤቶችን ጐበኘሁ ። እዚያ የሰማሁት የደወልና የቅዳሴ አመጣጥ

ታሪክን እንዲሁም አንዳንድ ሰው ሠራሽ ወግና ሥር ዓት ሲያስተምሩ ነው ።

በክርስቶስ ዘመን የነበሩ ፈሪሣውያን የሚደረገውን ተአምራት የሚያስተምረውን ሥራ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለይተው ሳያመዛዝኑ ሰንበትን በመሻሩ የስቅላት ሞት እንዲገባው እንደፈረዱ ሁሉ ፤ ዛሬም ብዙ ሰዎች ኮሚኒዝምን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ይመለከቱታል ። የነገሩን ምንነት ለማወቅ በአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት የለብንም ።

አንድ ጊዜ በሩማንያ ቀድሞ የቤተ ክርስቲያን መሪ አሁን ግን የሚስጢር ፖሊሶች ባልደረባ ከሆነ ሰው ጋር በግቢው ውስጥ ባለው አትክልት መሃል ተቀምጠን ስለእምነት ስንወያይ ሳለ እጁን ይዤ እንዲህ አልኩት ፤ ስለኰብላዩ ልጅና እንዴት አድርጎ ወደ አባቱ እንደተመለሰና አባቱም በልጁ ጥፋት ሳይቀየም በመመለሱ ብቻ ደስተኛ ሆኖ እንዴት እጁን ዘርግቶ በፍቅር እንደተቀበለው ከሚናገረው ክፍል አተርኩለት ነበር ። ያም ሰው ቃሉን በተመስጦ ያዳምጥ ነበር።

በዚህ ጊዜ እንዲህ አልኩት ፤ አስታውስ የፍቅር አምላክ በንስሐ ፊታቸውን ወደርሱ የሚመልሱትን ምንኛ በአክብሮት ይቀበላቸው? አባት ልጅ ስላጠፋው ጥፋት ይቅርታን ሲጠይቀው ሙሉ ምሕረትን ለመስጠት እንደሚፈቅድ ሁሉ እንዲሁ አምላካችን ጥፋተኛነቱን ተገንዝቦ ወደርሱ የሚቀርቡትን የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል (ኑዛዜ) እንዲያደርግና ወደ እግዚአብሔር ፊቱን እንዲመልስ ነገርኩት ። ጥቂት ክርስቲያናዊ መዝሙሮችንም ዘመርኩለት ። ያም ሰው ተናዝዞ ወደጌታ ተመለሰ ።

ደግሞ ሌላው አብሮኝ ታሥሮ ስለነበር ስለ አንድ ቄስ ታሪክ ልንገራችሁ ።

ይህ ቄስ ይህን ባደርግ እፈታለሁ በማለት እምነትንና የእግዚአብሔርን መኖርን የሚቃወም አንድ መጽሐፍን ጻፈ ። ነገር ግን ያ ጽሑፍ በማንም ሳይነበብ ወደዚያ ሰው ጠጋ ብዬ እምነቱን እንዲያድስና እንዲናዘዝ ባናገርኩት ጊዜ ያን ጽሑፍ ቀደደው ።

ብዙ የቅርብ ጓደኞቼ ይህን አሁን የያዝኩትን አገልግሎት ፈጽሞ አልተረዱልኝም ። በኮሚኒስቶች ላይ የምሰነዝረው ነቀፋ ሁሉ ከቂም በቀል እንደወጣ አድርገው ገምተውብኝ ነበር ፤ ይህም በልቤ የሌለ ነገር በመሆኑ ለኔ ለራሴ እንኳ አዲስ ነው ። አንድ ክላውዴ ሞንቲፌኖሬ የተባለ ፀሐፊ ክርስቶስ ጻፎችና ፈሪሣውያንን ስለመንቀፍ እንዲህ ጽፎአል ፤ ጻፎችና ፈሪሣውያንን በግልጽ መንቀፉ የራሱን ማለት «ጠላቶቻችሁን እንደራሳችሁ ውደዱ» ያለውን ትምህርቱን ያፈርሱበታል ብሏል ። ምን ማለቱ ነው? ራሱ ያስተማረውን ራሱ ይሽረዋል ። ማለቱ ነበር ።

ሌላው ደግሞ ዶክተር ደብልዩ አር ማቼውስ የተባለው ቀድሞ በሎንዶን ውስጥ የቅዱስ ጳውሎስ ዲን የነበረው ሰው ከሞንቲፊዮር ጋር በመተባበር ክርስቶስን ደደብ እንደ ነበርና ራሱ የተናገረውን ራሱ መልሶ እንደሚያፈርስ ጽፎአል ። በርግጥ የእነዚህ ሰዎች አባባል ማንም አመዛዛኝ አእምሮ ያለው ሰው ስህተት እንደሆነ ሊረዳ ይችላል ።

ምንም እንኳ መጥፎ ስራቸውን በግል በአደባባይ ቢያወግዝም ክርስቶስ የአይሁድን ካህናት ይወዳቸዋል ። ነቀፋው ሁሉ ከኃጢአት እንዲመለሱ ነበር ፤

ጌታ የኃጢአት ጠላት ቢሆንም የኃጢአተኞች ወዳጅ ነው ። እኔም ኮሚኒስቶችን በጣም እወዳቸዋለሁ ። መጥፎ ትምህርታቸውን ግን አብልጬ እቃወማለሁ ።

አንዳንድ መካሪዎች ነን ባዮች ኮሚኒዝምን መን ቀፍህን ትተህ ወንጌልን ብቻ አስተምር ይሉኛል ።

አንድ ጊዜ ከአንድ በሂትለር ጊዜ በናዚስቶች ብዙ መከራና ስቃይ ከተቀበለ ወዳጄ ጋር ስነጋገር ስለክርስቶስ አዳኝነት የማሰማው ስብከት መልካም እንደሆነና ኮሚኒዝምን ግን መንቀፍ እንደ ሌለብኝ ነገረኝ ።

እኔም በናዚስቶች ጊዜ በሂትለር የሚደረገውን አመፅ ይቃወሙ የነበሩ ክርስቲያኖች ተሳስተው ነበርን? አልኩት ። ፈጽሞ አልተሳሳቱም ሂትለር የ፤ ሚሊዮን አይሁዳውያን ገዳይ ነው አለኝ ። እኔም ምን ታስባለህ? ኮሚኒዝም የ፴ ሚሊዮን ፡ ሩሲያውያን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቻይናውያንና የአይሁዳውያንም ገዳይ ነው ። ታዲያ ሂትለርን የተቃወሙ ክርስቲያኖች የሂትለርን አርአያ የያዘውን ኮሚኒዝምን መቃወም የለባቸውም አልኩት ። ምንም መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም ።

በሂትለር ጊዜ ታሥሬ ነበር ፤ ዛሬም በኮሚኒስቶች ወህኒ ገብቼአለሁ ፤ ግን በኮሚኒስቶች የደረሰብኝ ስቃይ በሂትለር ጊዜ ከደረሰብኝ ጋር ሳወዳድረው ያሁኑ በጣም ከባድ እንደሆነ ለመረዳት ችዬአለሁ ። «ክርስ ትና ኮሚኒዝምን ብቻ ሳይሆን የኃጢአት ዘርያዎች የሆኑትን ሁሉ መቃወም አለበት» በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ያለእንቅልፍ የሚዋጋት ኮሚኒዝም ነው ፤ እሱንም ለመዋጋት ኃይላቸውን እንዲያደረጁ በልዩ ልዩ ስም የተከፋፈሉ ቤተ ክርስቲያኖች መተባበር አለባቸው።

የሕይወት መልካም ገድል ሰዎችን ወደሚደነቅ ሰማያዊ ደስታ መምራት ነው ኮሚኒዝም ግን ይህን መቃወም ዋናው ተግባሩ ሆኗል ። ፀረ ሃይማኖት ነው ።

ናውካይ ሬሊጂን «ሣይንስና ሃይማኖት» የተባለው የሶቪየት ጋዜጣ አንድ ጊዜ ባወጣው እትሙ «ሃይማኖት የኮሚኒዝም ጠላት ነው ፤ ሃይማኖት ባለበት በዚያ ኮሚኒዝም እግሩን ዘርግቶ ሊንሰራራ አይችልም ። ስለዚህ የኮሚኒዝም ዋና ዓላማ ሃይማኖትን መዋጋት ነው ። ያን ጊዜ ሰዎች ከሃይማኖት ባርነት ነፃ ይወጣሉ። ሲል ጽፎአል ።

አንድ ጊዜ አንድን ሰው እንዲህ አልኩት ፤ ለመሆኑ ሃይማኖትና ኮሚኒዝም አብረው ሊኖሩ ይችላሉን? ያም ሰው ሲመልስ ሃይማኖትና ኮሚኒዝም «እሳትና ጭድ ናቸው» አለኝ ።

## ምዕራፍ ፳

አሁን ደግሜ በኮሚኒስት አገር በብዙ ስደትና መከራ ወንጌልን ስለምታስፋፋው ቤተክርስቲያን ልናገር እወዳለሁ ። በአካባቢዋ የሞላው እግዚአብሔር ያለ መኖሩን የሚያምን ሕዝብ ነው ። ሕፃናት ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ ስለሃይማኖት ወይም ስለ እግዚአብሔር እንዲያውቁ አይደረጉም ። «ሃይማኖት ለሽማግሌ» የሚል እምነት ስላላቸው ወጣቶቹ ከቤተ ክርስቲያን የተገለሉ ናቸው ። ቴሌቪዥን ፣ ሬዲዮ ፡ ሲኒማና ቲያትር ዋናው ዓላማቸው ሃይማኖትን መቃወም ነው ። ምንም እንኳ ይህን የመሰለ እምነት ባላቸው አካባቢ ብትኖርም ወንጌልን በሚገባ በማዳረስ ላይ ናት ። የሌሎች ቤተ ክርስቲያኖችና ክርስቲያኖች ድጋፍ ቢጨመርበትማ ሥራው ምንኛ ይከናወን ይመስላችኋል! በዚህ የጥፋት ሠራዊት ኃይላቸውን ባስተባበሩበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን እምነትን ለማስፋፋት ያላት ነፃነት በጣም የተወሰነ ነው ።

በአንዳንድ ቦታ እንዴት እንደሚከኑ ልንገራችሁ? የሚክናቸው እውነተኛ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ የላቸውም ። የክህነቱ ሥርዓት የሚፈጸመው በኮሚኒስቶች መሪዎች ነው ። ምንኛ ዝብርቅርቅ ነው? እግዚአብሔር የለም ብለው ያምናሉ እሱን ለማገልገል ለሚሹ ግን ክህነት ይሰጣሉ ። አንድ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ጋር ስወያይ ለመሆኑ ማን ነበር የሾመህ? ስል ጠየቅሁት? ሲመልስልኝም የሚክነን ጳጳስ የለንም የምንካነው እግዚአብሔር የለም በሚሉ የኮሚኒስት መሪዎች ነው ስለዚህ እኔና ጓደኞቼ በቅርቡ ወደ ሞተው ጳጳስ መቃብር ሄደን እጃችንን መቃብሩ ላይ ጭነን መንፈስ ቅዱስ የክህነትን ሥልጣን

እንዲሰጠን ፀለይን ። በርግጥ በዚያችን ጊዜ ክርስቶስ የተወጉ እጆቹን በላያችን ጭኖ ካህናት የመሆንን ሥል ጣን እንደሰጠን አመንን ።

እንደእኔ ግምት የዚህ ወጣት ክህነት በእግዚአብ ሔር ፊት የፀና ነው ። ይህን በመሳሰሉ ቆራጥ ክርስቲ ያኖች ነው የመንግሥቱ ምሥራች የሚሰበከው ። በብዙ መንገድ ይህች ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን ትመስላለች ። እነዚያ «ዓለምን በትም ህርታቸው በጠበጣችኋት ይላሉ» የነበሩት ክርስቲያ ኖች ከየትኛውም ሰሚናር ወይም የቲዎሎጂ ት/ቤት የተመረቁ አልነበሩም ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ማን በብ እንኳን የማይችሉ ነበሩ ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር የሚናገሩትን ሁሉ በአፋቸው ስለሚያደርግ በትምህ ርታቸው ብዙዎች ይነኩ ነበር ። ሁሉን የሚችል የአ ምላክ ክንድ በጉባዔያቸው በሚያስደንቅ ኃይል ይንቀ ሳቀስ ነበር ።

እነዚህ የሚሰደዱ ክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ያማረ ካቴድራል አልነበራቸውም ። ካቴድራል ምንስ ቢያምር ምንስ ውብ ቢሆን አምላክ ካስጌጣት ከሰ ማያዊት ኢየሩሳሌም ይበልጣልን? ለዚህም ብቁ እንዲ ሆኑ እምነታቸውን እየፀኑ ይጠብቃሉ ። ፒያኖ አልነበ ራቸውም ። የሚሰሙት የጫካ ወፎችን ዝማሬ ነው ። እጣን አልነበራቸውም ። የሚያሸቱት ዱር ያፈራውን የፅጌረዳ መዓዛ ነው ። ምዕመናኖችዋ አዋቂ ከሆኑ በኋላ ወይስ በልጅነት መጠቀም በሚለው ኦይከራከ ሩም ። በወግና በሥርዓት የታሠሩ አልነበሩም ። ስለትን ቢት ትርጓሜ ሲያጠኑ ያንዱን ሃሳብ አንደኛው አይን ቅበትም ። እኔን የሚያስደንቀኝ ግን እግዚአብሔር የለም ብሎ ሊከራከራቸው የሚመጣውን ሰው አፉን

የሚያስይዝ መልስ መስጠታቸው ነው ። መልሶቹም ቀላል ናቸው ። አንድ ጊዜ አንዱ እግዚአብሔር የለም በማለት ክርስቲያን ወንድማችንን ይከራከረው ነበር ።

ያም ወንድማችን በቀላል መንገድ የእግዚአብሔ ርን መኖር ሊያስረዳው ፈልጎ የሚከተለውን ምሳሌ ሰጠው ።

ለምሳሌ እኔ ቤት የምሳ ግብዣ ባደርግልህ የቀረ በልህን መብልና መጠጥ ሁሉ ተፈጥሮ ሰጠኝ ትላለ ህን? በርግጥ በተፈጥሮ ሕግ የሚበላና የሚጠጣው ሁሉ ከተፈጥሮ የተገኘ ነው ። ግን እንዲስማማ አድርጎ አቀነባብሮ ለመብል ማቅረቡ ግን አንድ ይህን ያዘ ጋጀ ሰው መኖሩን ያሳያል ።

በዓለም ላይ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ ብዙ ነገ ሮች አሉ ፤ ማን ፈጠራቸው? ተፈጥሮ? ተፈጥሮስ እውር ነው ። የዚህን ዓለም የተፈጥሮ ሕግ የሚቆጣጠር ታላቅ ጠቢብና አዋቂ የሆነ ፈጣሪ መኖር አለበት ። ክርስቲያኑን ለተከራከረው የተሰጠው መልስ የሚከተ ለው ነው ። ለምሳሌ ከአንድ በእናቱ ማኅጸን ውስጥ ካለ ሽል ጋር ለመነጋገር ብንችል እሱ ካለበት ጠባብ ዓለም ሌላ እጅግ ሰፊ የሆነ ዓለም እንዳለ ብንነግረው ምናልባት መልሱ ዛሬ እናንተ እግዚአብሔር የለም የምትሉት ሰዎች የምትናገሩትን ሊሆን ይችላል ። ከዚህ «አሁን ካለሁበት ሌላ ዓለም የለም» ያች ያለ ባት ዓለም ጠባብ ከመሆኗ ሌላ ጥሏት የሚወጣና እዚህ መሰሎቹ ከሞሉበት ሰፊ ዓለም ውስጥ እንደሚ ደባለቅ አያውቅም ። ነገር ግን እያደር እጅ ሲያወጣ እንዴ! ይህ እጅ ለምን ወጣ ምናልባት ሰዎች አለ ወደሚሉት ዓለም ስሄድ ሥርቼ የምበላበት ይሆን?

እግርም ሲያወጣ እንዴ! ይህ እግር ለምን ወጣ? ምና ልባት አሁን ከዚህ ወጥቼ ወደምኖርበት ዓለም ስሄድ ከቦታ ወደቦታ የምንቀሳቀስበት ይሆን? ዓይንና ጆሮም ሲወጡለት ይህ ዓይንና ጆርስ ጥቅሙ ምንድነው? ወደፊት በምኖርበት ዓለም የማይበትና ከሰዎች ጋርም እንድግባባ የምስማማበት ይሆን? ይህንና ይህን የመሳ ሰሉትን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከዚያች ካለባት ጠባብ የእናቱ ማሕፀን ይልቅ የሰፋ ዓለም መኖሩን ይረዳል ። ስለወደፊቱም ኑሮው ይዘጋጃል ። ይህንንም የሚያደር ገው ሳያይ ነው ። እኛም ለ፸ ገፋ ቢልም ለ፹ ዓመታት በዚህ ዓለም ውስጥ የምንኖር የሰው ልጆች ዘመናችንን ከዘለዓለም ጋር ስናወዳድረው በጣም ሕፃን እንደሆንን እንረዳለን ። ከምናውቀው የማናውቀው ይበልጣል ። ስለ ዚህ ከሞትን በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ራሳችንን በእግ ዚአብሔር ቃል እያነፅን እንዘጋጃለን ።

ኮሚኒስቶች እንደሚያምኑትና እንደሚያስተም ሩት ክርስቶስ የሚባል ሰው ፈፅሞ እንዳልነበረ ነው ። አንድ ጊዜ አንድ ክርስቲያን ወደኮሚኒስቱ ጠጋ ብሎ ስለክርስቶስ ሊመሰክርለት ፈለገና ቢያናግረው እንዲ ያው ም ክርስቶስ የሚባል ሰው በዓለም ታሪክ ውስጥ እንዳልነበረ ነገረው ። በዚህ ጊዜ ያ ክርስቲያን ወን ድም በጥበብ መጠቀም እንዳለበት አውቆ ነገሩን ችላ እንዳለው በማስመሰል እስቲ በእጅህ የያዝከው ጋዜጣ የመቼ ነው ። አይ! እንደሚለው ይህ የያዝከው ጋዜጣ የወጣው ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. ነው ፤ ግን ይህ ፲፱፻፳፩ ከየት ተነስቶ ነው ዛሬ ብዙ ሰዎች የቀን መቁጠሪያ ያደረጉት? እንዴ! ክርስቶስ አልነበረም አልተወለደም የምትሉ ስትሆኑ እንዴት ካልነበረና ካልተወለደ ሰው ልደት የቀን መቁጠሪያ ካላንደራችሁ

ይጀምራል? የክርስቶስን መኖር የናንተ ጋዜጣ ፕራ ቭዳ እንኳ ያምናል ፤ ራሱ ምስክር ነው አለው ።

ኮሚኒዝም በተስፋፋ ቁጥር ቤተክርስቲያን ትጠፋ ለች ዛሬ የምታንቀላፋው ቤተ ክርስቲያን ነፃነቷ በኮሚኒስቶች ከተወሰደባት ፈጽሞ ልታስመልሰው አት ችልም ። ቤተ ክርስቲያን በትጋት መሥራት በሚኖርባት ዛሬ ነው ።

## የክርስቲያኖችና የኮሚኒስት ጽሑፎች ።

እግዚአብሔር የለም የሚሉ አላማኞች መጽሐፍ ቅዱስን ለመቃወም ብዙ ነገርን ይናገራሉ ። ይጽፋሉ ። ለምሳሌ «አስቂኙ መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኞችና ላላ ማኞች» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ለአንባብያን መሳቂያና መዘባበቻ እንዲሆኑ በማለት ብዙ የመጽ ሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ታትመዋል ። ይህም መጽሐፍ በውስጡ ካሉት ተስፋዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኮፒ ተሸጠዋል ። ቢያነበው ምንም እንኳ የመጽሐፉ ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን ለመቃወም ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎቹ መጽሐፎች ይልቅ ልዩ በሚያደርጉት ውስጡ ባሉት ኃይለ ቃላት ይደነቃል ። አዎን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ፤ በዲያብ ሎስ አፍ ቢነገሩ እንኳ ኃይለኞች ናቸውና የሰዎችን ልብ ሊወጉ ይችላሉ ። ይህን መጽሐፍ ላሳተመው ድር ጅት መጽሐፉ ይበልጥ እንዲታተም ብዙ ደብዳቤዎች ደረሱት ። ቢሆንም እነዚያ ደብዳቤዎች መጽሐፍ ቅዱ ሳቸው ከተነጠቀባቸውና የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ሌላ የሚያገኙበት መንገድ ከሌላቸው ክክርስቲያኖችና መጽ ሐፍ ቅዱስን ከሚያምኑ የተላኩ ነበሩ ።

አንድ ጊዜ በአንድ ታላቅ ስብሰባ ላይ አንድ ፕሮፌሰር ለጉባዔው የኢየሱስ ክርስቶስን ውሸተኛ ነት ለማስረዳት ጌታ በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወይን አደረገ የሚለውን ታሪክ ካነበበ በኋላ እንዲህ አለ ፡፡ «እያችሁ! ይህ አላዋቂዎች የዓለም አዳኝ የሚሉት ምንኛ አታላይ እንደነበር? ያ ሞኝ ሠራዊት ውሃውን ወይን አደረገ ብሎ ያመነው እንዴት ይመስላችኋል? ውሃው ውስጥ በድብቅ ሊያቀላው የሚችል ቅመም በመ ጨመር ነው ፡፡ ከፈለጋችሁ ዛሬም እኔ ውሃውን ወይን ላድርግላችሁ ፡፡» አለና ውሃ በትልቅ ጠርሙስ አስቀ ርቦ አንድ ያልታወቀ መርዛም ቅመም ጨመረበት ውሃውም ሰዎቹ እያዩ ልክ ጥሩ የወይን ጠጅ መሰለ ፤ ያም ፕሮፌሰር ራሱን በማኩራራት እዩ! እንዲያውም እኔ ከክርስቶስ ይበልጥ ተአምር ላደርግ እችላለሁ ፡፡ ወይኑን እንደገና ውሃ ላድርገው አለና ሌላ ቅመም ጨመረበት ፡፡ ያ አንድ ወይን ቀልቶ የነበረው ውኃ የቀ ድሞ መልኩን ያዘ ፡፡ እንዲህ እያመላለሰ ብዙ ጊዜ አደ ረገ ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ አስተዋይ ሰው ተነሥቶ ለፕሮፌሰ ሩና የፕሮፌሰሩን ንግግር ለሰሙት ሰዎች እንዲህ አለ ፡፡ «ክቡር ፕሮፌሰር ስለ ሠራኸው ተአምራት በጣም እናደንቃለን ፡፡ ኢየሱስም ምንኛ አታላይ እንደነበር ነግረኸናል ፡፡ ግን እኮ የኢየሱስን ታሪክ እንዳነበብክ ልን እሱ ያደረገው ውሃውን ወደ ወይን መለወጥ ብቻ አይደለም» ፡፡ «ሠርገኞች ሁሉ ጠጡ» ይላል ፡፡ አሁን ካንተ የምንጠብቀው ውሃውን ለውጠህ ወይን ካደረ ግኸው አንዴ እንድትቀምስና ይህን ሁሉ ሕዝብ እን ድታጠጣ ነው ፡፡ ከዚያ በኋላ በርግጥ ክርስቶስ አታላይ እንደነበር እንረዳለን ፡፡ ያም ፕሮፌሰር ያላሰበውንና ያልጠረጠረውን ጥያቄ በመጠየቁ በድንጋጤ አ—አ— እ— ይህን ላደርግ አይልችልም! ይህ እኮ መርዝ ነው!

አለው ። ያም ሰው መልሶ ይኸውልህ ያንተና የክርስቶስ ልዩነቱ እዚህ ላይ ነው!

ክርስቲያኖች በኮሚኒስቶች ፊት ራሱን በሚያኩራራው በጐልያድ ፊት እንደነበረው እንደ ዳዊት በጣም አነስተኞች ናቸው ። ቢሆንም ታላቅ ሥራን ይሠራሉ ።

በሚያስደንቅ ሁኔታ ሃይማኖትን ለመቃወም ለሚያደርጉት ንግግሮች ሁሉ መልስን ይሰጣሉ ።

በእስር ቤት በነበርኩበት ጊዜ አንዱ በቁጣ እስከ መቼ ይህን ደደብ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብህን አትተውም? አለኝ ። እኔም ዛሬ በሕይወት እያሉ ሰዎች ምንም እንኳ እግዚአብሔር የለም ቢሉም በሞታቸው ጊዜ የነ ማርክስ ፣ ሌኒን ፣ ስታሊንና የሌሎችን መሪዎች ስም ሳይሆን አምላክ የለሽ በመሆናቸው እየተፀፀቱ እግዚአብሔር ሆይ! ማረን ፤ ጌታ ሆይ! ይቅር በለን ሲሉ እንሰማቸዋለን ። ታዲያ አሁን ብክደው እንኳ በሞቴ ጊዜ እሱኑ መማጸኔ ካልቀረ እምነቴን ማጽናት ይኖርብኛል እንጂ እንዴት እክዳለሁ አልኩት ። በማፌዝ ከት ብሎ ሳቀብኝ ።

ሌላ እንዲህ ያለ ምሳሌ ደግሞ ሰጠሁት ። አንድ ኢንጅኔር የሠራውን ድልድይ ጽኑነቱን የሚያስመሰክረው ድመት እንድታልፍበት በማድረግ አይደለም ። ነገር ግን ጽኑነቱን ለማሳየት ባቡር በላዩ ማሳለፍ አለበት ። እናንተም አምላክ የለም የሚያሰኛችሁ ፍልስፍናችሁ በደህና በሰላም ቀን እንጂ በጭንቀታችሁ ጊዜ ምንም ሊፈይድላችሁ አይችልም ። በችግራችሁ ቀን የለም ያላችሁትን አምላክ ስትማጸኑ ትገኛላችሁ ።

ለዚህም መረጃ የሚሆነን ሊኒን ራሱ የሶቪየት ጠ/ሚኒስቴር ከሆነ በኋላ መጸለዩ ነው ። አዎን የሰው ልጆች አምላክን ሊዘነጉት የፍቅር ክንዱንም ዘርግቶ ሲጠራቸው ቸል ሊሉት ይችላሉ ። ነበር ግን አስከፊ ቀን ሲመጣ በየትም ሆነ በየት ሁሉ የብረት መዝጊያ ሲሆንባቸው የረድኤት ክንዱን እንዲዘረጋላቸው ይማጸኑታል ። ታዲያ! አምላካችን ሰው ስለበደለው በደል ቁጡ ቢሆንም ምሕረቱ እጅግ ታላቅ ነውና ይቀበላቸዋል ።

ቅዱስ አውጉስጢኖስ እንዲህ አለ ፤ «አቤቱ ጌታ አምላካችን ሆይ ልባችን አንተን እስኪያገኝ ድረስ ምንኛ የተቅበዘበዘ ነው!»

## ለምን ኮሚኒስቶች በእግዚአብሔር ያምናሉ?

ይህች በኮሚኒስት አገር የወንጌልን ብርሃን የምታበራው ቤተ ክርስቲያን በናንተ በውጭ ባላችሁ ክርስቲያኖች ከተረዳች የኮሚኒስት አገሮችን ሁሉ ልትለውጥ ትችላለች ። ሰው ምንጊዜም ምንም ጨካኝ ቢሆን ሰው ነው ። እርግጥ ሊበድልና ሊያጠፋ ይችላል ቢሆንም አንድ ሰው ስላጠፋው ጥፋት መጸጸቱ አይቀርም። ለዚህም መረጃ የሚሆነን ናዚስቶች የብዙ ንጹሐንን ደም ካፈሰሱ በኋላ ግማሾቹ ስላጠፉት ጥፋት ሕሊና እየወቀሰ ሌት ተቀን ቢያሰቃያቸው በገዛ እጃቸው ሕይወታቸውን አጠፉ ። ብዙዎቹ ግን የለም ያሉትን እግዚአብሔርን እባክህን ጌታ ሆይ ያደረግነውን በደል ይቅር በለን ብለው ተጸጽተዋል ። ሰው ከአውሬ ይለያል ፤ አውሬ ስለበደለው በደል ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ነው ። ሰው ግን ሕሊናው ይወቅሰዋል ፤ ይከሰዋል ።

ይህም ለክፋት ሳይሆን ስለበደለው በደል የኃጢአትን ስርየት ፡ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ከሚችል አምላክ እንዲጠይቅ ነው ። ሰው ሥጋዊ እንደ መሆኑ መጠን የሥጋን ያስባል ፤ ሰው ደግሞ መንፈሳዊ ነውና በሥጋ ብቻ አይወሰንም ። ለዚህ ነው ኮሚኒስቶች ወንጌልን የሚነግራቸው ካገኙ በደስታ የሚቀበሉት ። ኮሙኒዝም በዚህች በተወሰነችው ዓለም የተወሰንን ሆነን የምንኖርበትን ጥበብ ያስተምረናል ።

ከሥጋ ባርነት ለመውጣት እውነተኛ «ሃይማኖት ያስፈልጋል ። ጌታ ኢየሱስ «እውነትን ፈልጉ ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል» ብሏል ።

ታዲያ እኮ ያን ነፃ የሚያወጣውን እውነት ለማግኘት ነጻነት ያስፈልጋል ። ምንም እንኳ በክፉዎች ፍልስፍና የተመረዙ ቢሆኑም ሁሉም ኮሚኒስቶች ለምሥራቹ ቃል ልባቸውን የዘጉ አይደሉም ። ቃሉን ሊሰሙ ለደህንነት ውሳኔ ሊያደርጉ ይወዳሉ ።

ኮሙኒዝም ተከታዮቹን ሰው በአልኮል ኃይል ሥር እስካለ ድረስ እንደሚደሰት የአልኮሉ ኃይል ከበረደ በኋላ፣ ግን እንደሚያስጸጽት ወይን ነው ።

ተከታዮቹን ሊያስደስታቸው ይችላል ። ከውስጣዊ ሰብእናቸው የሚመጣውን የሕይወት ጥያቄ ግን ሊመልስና ሊያረካቸው አይችልም ። አንድ ቀንም በኮሚኒዝም ተደሳች ሆነው ከኖሩበት ከዚህ ዓለም ኮንትራታቸውን ሲጨርሱ ወደናቁትና የለም ወደ አሉት አምላክ በመቃተት ይመለሳሉ ። ቢሆንም የምሕረት ጊዜ አሁን ነው ።

ኮሚኒስቶች ኃይላቸውን በቡካሬስት በሚያስፋፉ በት ዘመን አንድ ቀን ከሚስቴ ጋር ሆነን በካምፕ ውስጥ ወዳጆቻችንን ለማነጋገር ሄድን ። በዚያ አንድ ካፒቴን በጣም ስክር ብሎ ሲንጀባረር አየን ። አብዝቶ ለመጠጣት ሌላም ስጡኝ ይል ነበር ። ግን እሱን ከጉዳት ለመጠበቅ ሲባል ሊጨምሩለት አልፈቀዱም ። እኔም ወደ አንድ ወደማውቀው ሰው ጠጋ ብዬ ስላ ምታ ከሰጠሁት በኋላ በራሱና በሌሎቹም ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እጠባበቀዋለሁና ስጡት ይጠጣ አልኳ ቸው ። ወዲያው ዓይኔ እያየ አከታትሎ ሶስት ብርጭቆ ወይን ጠጣ ። ምንም በጣም ቢሰክር እንኳ ንግግሩ ዝንፍ አይልም ነበር ።

ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ ስለክርስቶስ እሰብክለት ጀመር ። በእርግጥ የምለውን ለመስማት ያለው ጉጉት ከፍ ያለ ነበር ። ሁሉን በትእግሥት ካዳመጠኝ በኋላ እንዲህ አለኝ ። «እስካሁን የምትናገረው ሁሉ ትክክል ነው ። የተማርኩትና ያመንኩበት ነው ፤ ምንም እንኳ አሁን በሚስጢር ፖሊሶች ማኅበር ውስጥ የካፒቴን ነት ማዕረግ ባገኝም ቀድሞ ቄስ ነበርኩ ። ነገር ግን ስታሊንና ተከታዮቹ በክርስቲያኖችና በሌሎችም ለሃሣቡ ተቃራኒ በሆኑ ላይ ስደትን ባነሣ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ተገንጥዬ ወጣሁ ። እግዚአብሔርንም እንደሌ ሎቹ እሰብክ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ወደ ሚስጢር ፖሊሶች ስብሰባ ተጠርቼ ማዕረግ ተሰጠኝ ። ክርስቲያኖችንና ቤተ ክርስቲያንን ማሳደድ ዋና ተግባሬ ሆነ ። ብዙ ክር ስቲያኖችን በሚስጢር ተሰብስበው ጸሎት ከሚያደር ሱበት ቦታ አስይዤ አስገደልኳቸው ። አሁን ይህ ሹመት የተሰጠኝ ያኔ ለሠራሁት ግፍ ዋጋ እንዲሆን ተብሎ ነው። ምንም እንኳ እንደምታየኝ የተፈራሁና የተከበርኩ

ሹም ብሆንም ሕሊናዬ በሠራሁት ወንጀልና ባጠፋ ሁት ጥፋት ሌት ተቀን እየወቀሰ እየከሰሰ ቢያስቸግ ረኝ ከገዛ ሕሊናዬ ወቀሳ እንዲያድነኝ በማለት ይኸው እንደዚህ እንደምታየኝ በወይን ጠጅ መስከርን ጀመ ርኩ ። ቢሆንም ከሕሊና ወቀሳ ሊያድነኝ አልቻለም»።

ብዙ ኮሚኒስቶች ራሳቸውን ይገድላሉ ። ለምሳሌ ያህል ታላላቅ የኮሚኒስት ገጣሚዎች ኤዝኒን እና ሚያኮቭስኪ እንዲሁም ታላቁ ኖቭሊስት «ደስታ» የሚባለውን መጽሐፉን ጽፎ ከጨረሰ በኋላ ራሱን በሽጉጥ ገደለ ።

ይህ ደራሲ በዚያ መጽሐፉ ውስጥ ደስታ እን ዴት ሊገኝ እንደሚችል ሲያስረዳ እንዲህ ብሎአል ። «ደስታ ሊገኝ የሚችለው ኮሚኒዝምን በማስፋፋትና ሊስፋፋ የሚችልበትን መንገድ በመፈለግ እንደሆነና ይህም እሱን እንዴት ደስተኛ እንዳደረገው ገልጾአል ።» ቢሆንም ያን የኖቭል ጽሑፉን ከጨረሰ በኋላ ራሱን መግደሉ ደስታ እንዳልነበረው መረጃ ነው ። ኮሚኒስ ቶችና መሪዎቻቸው ደስተኞች አይደሉም ። ስታሊንም ደስታ የሌለው ተቅበዝባዥ ነበር ። ብዙ ሰዎችንና እንዲሁም የሥራ ጓደኞቹ የነበሩትን ስላስገደላቸውና በዚሁም ምክንያት ብዙ ጠላቶች ስለነበሩት አንድ ቀን ይገድሉኝ ይሆናል የሚል ታላቅ ሥጋት ነበረው ። ስለዚህም መኖሪያ ቤቱ ከባንክ ይልቅ በጥብቅ የሚ ጠበቅ ስምንት ክፍሎች ነበሩት ። ማንም ከስምንቱ ክፍሎች በየትኛው እንዳለ አያውቅም ፤ መኝታውንም ዛሬ ካንደኛው ነገ ከሌላኛው ያደርግ ነበር ። ድርሶ ከገዛ ሕሊናው ወቀሳ ያድነው ይመስል!

ይገርማችኋል ስታሊን የቀረበለትን ምግብ እንኳ ወጥቤቷ እራሱዋ ቀርባ ደጋግማ ካልቀመሰችለት በቀር አይበላም ። ታዲያ ደስታ ይህ ነው? ይህን በመሰለ መንገድስ ይገኝ ይመስላችኋል? አይደለም ። ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋል ።

ቀድሞ የቤተክርስቲያን መሪ የነበረ አሁን ግን ጅርጅ በሚባል ስም የሚጠራ ሰው ከጻፈው ከአንድ መጽሐፉ ላይ የሚከተለው ተወስዶአል ። «አንድ ቀን የሩሲያ ወታደሮች ካፒቴን የሆነ ሰው ወደ አንድ የሃይማኖት ሰባኪ ቤት ሂዶ ስለ እምነት አንስተው ሲነጋገሩ ሳለ ያ ካፒቴን ከሰባኪው ቤት ተሰቅሎ የነበ ረውን መስቀል በማሾፍ እያየ እንዲህ አለ ። «እናንተ እኮ የምታስተምሩት ሁሉ ውሸት ነው ፤ ዓላማችሁ እግዚአብሔር አለ እያላችሁ በማስፈራራት ድሃ ሁል ጊዜ ለሃብታም ተገዥ እንዲሆን ማድረግ ነው ።» ብዙ ከተናገረው በኋላ አንድ ሽጉጥ ከኪሱ አውጥቶ ወንጌላዊው ደረት ላይ ደገነና «አሁን ይህ ክርስቶስ የምትለውን ካድ ፤ አለበለዚያ ላዳፍንብህ ነው» አለው። ያም ሰባኪ የተደገነበትን ሽጉጥ ሳይፈራ ጌታ ኢየሱስ እውነት ነው ያስተማራቸውም ትምህርቶች እውነት ናቸውና ስለ እምነቴ መሞትን መርጫለሁ ቢለው ያ ካፒቴን እያለቀሰ ሽጉጡን ወደኪሱ እየከተተ አዎን የምታምኑበት አምላክ ተረት ሳይሆን እውነት ነው ። ስለሱ ፍቅር ሞትን እንኳ እንዳትፈሩ ኃይልን ሰጥቶ አችኋል ብሎ አቀፈው ። ክርስቲያን ሊሆንና ስለ ክር ስቶስ ሊሞት እንኳ ፈቃደኛ እንደሆነ ነገረው ። ሰባኪ ውም ስለክርስቶስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ ብዙ ካስረዳው በኋላ ራሱ የጌታን ወንጌል የሚያስፋፋ ሆነ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ሁለት ድግን መትረየስ የያዙ ወታደሮች ወደ አንድ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች እንዲህ አሉ ። «አሁን ልንረሽናችሁ ከመንግሥቱ ተልከን መጥተናል ግን እድል እንሰጣችኋለን ፤ ስለእምነታችን እንሞታለን የምትሉ ካላችሁ በቀኝ በኩል ሁኑ ። ሕይወታችሁን ለማዳን የምትፈልጉ ግን ወደቤታችሁ ለመሄድ ተፈቅዶላችኋል» በዚህ ጊዜ በእምነታቸው ገና ያልፀኑ ቤተ ክርስቲያኑን ትተው ወደቤታቸው ሄዱ ። በዚያ ቆራጥ የእምነት አርበኞች ብቻ ቀሩ ። እነዚያም ወታደሮች እንዲህ አሉ «ስሙ! እኛ ራሳችን ክርስቲያኖች ነን ልንተባበርም የምንፈልገው በእምነታቸው ማዕበል እንደመታው መርከብ ከሚያወላውሉት ጋር ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ሞትን እንኳ ለመጋፈጥ ፈቃደኞች ከሆኑት ጋር ነው ። ክርስቶስ እንዲህ ያሉ ቆራጥ አርበኞች በኮሚኒስት አገሮች አሉት ።

ክርስትና ኮሚኒዝምን ማሸነፍ አለበት ምክንያቱም ክርስትና የእግዚአብሔር ኃይል ነው ። ክርስትና ሰውን ሊያረካ የሚችል ትምህርት ነው ። ምንም እንኳ ዛሬ በኮሚኒስት አገሮች ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ጽሑፎችን ለማደል ባንችልም በሩሲያ የቶልስቶይና የዶስቶይ ቪስኪ በምሥራቅ ጀርመንም የጉቴይ በፖላንድ የሲዚ ይንኪዊክዝ በሩማንያም ደግሞ የሶቪየት መጽሐፍ ዛሬም በኮሚኒስቶች ይነበባሉ ። እነዚህ ሁሉ ክርስቲያን ፀሐፊዎች ነበሩ ።

ኮሚኒስቶች «የቅዱሳን ታሪክ» የሚለውን መጽሐፍ ርእሱን በመቀየር «የቅዱሳን ተረት» ብለው ዛሬም ቢሆን በመታተም ላይ ይገኛል ። ቢሆንም ይህ መጽሐፍ ምንም ዓይነት መጥፎ ስም ቢሰጡትም ዛሬም

ቢሆን ኃይል ያለው መጽሐፍ ነው ። የታወቁ ሠዓሊዎች እንደ ማይክል ኤንጀሎ ሊዎናርዶ ዳቪንቺ የመሳሰሉት ታላላቅ ሠዓሊዎች ስለክርስቶስ የሳሉ ናቸው ። ብዙ ሥዕሎች ዛሬም ቢሆን የታሪክ ትዝታን የሚቀሰቀሱ ሆነው ተገኝተዋል ።

እኔ ራሴ እግዚአብሔር የለም ከሚሉ ከማርካሲዝም ፕሮፌሰሮች ብዙዎቹ አማኞች እንደሆኑና መጽሐፍ ቅዱስንም በድብቅ እንደሚያነቡ በተስፋውም የሚያምኑ እንደሆኑ አውቃለሁ ። አዎን ሰዎች ስለሆኑ የሚመኩበት የሚታመኑበት ከነሱ በላይ የሆነ አፍቃሪ መመኪያ አባት ያስፈልጋቸዋል ። ክርስቶስ ኮሚኒስቶችን ይወዳል ፤ ስለዚህ እርሱ ለሰው ልጆች የሠጠውን ተስፋ ከኛ ክርስቲያኖች ነን ከምንል መስማት ይኖርባቸዋል ። ኮሚኒስቶችን ክርስቲያን ካደረግናቸው እነሱ ደግሞ ኮሙኒዝምን ባስፋፉበት ቀናት ክርስትናን ሲያስፋፉ ዓለም በክርስትና ትምህርት ልትጥለቀለቅ ትችላለች ። ክርስቲያኖች ክርስቶስን ቢያምኑ እንኳ የተናገርነውን (ያዘዘውን) አሚልተው አልተገኙም ። እሱ «አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» ብሎ አዞአል ። እነሱ ግን ለሌላው ዓለም ብዙ ሚሲዮናውያንን ሲልኩ ኮሙኒስቶችን ግን ዘንግተዋቸዋል ። እኛ ክርስቶስን እንወዳለን የምንል እሱ ያለውን እንስማ! እሱ «ብትወዱኝ ትእዛዛቴን ጠብቁ» አዎን የሱ ጭንቀት የሱ ታላቅ ምኞት አሕዛብን ሁሉ ደቀመዛሙርቱ እንድናደርግለት ነው ።

ታዲያስ! ክርስቲያኖች ይህን ለማድረግ የክርስቶስ ፍቅር ግድ አይላችሁም ። ይህንንም ለማድረግ የምትችሉት ኃይላችሁን በማስተባበር ነው ።

# በኮሚኒስት አገር ያለችው ቤተክርስቲያን ሦስት ክፍሎች

የዚህች ቤተክርስቲያን አካላት የሆኑ ሦስት ክፍ ሎች አሉ ። የመጀመሪያዎቹ ቀድሞ የቤተክርስቲያን መሪዎች የነበሩና ዛሬ ግን እምነታቸውን የሚያስፋፉ ትጉህ ሠራተኞች መሆናቸው ስለታወቀ ከቦታቸው ተወግደው በወኅኒ ቤት ብዙ የሥቃይ ዓመታትን ካሳለፉ በኋላ ከእስር ቤት ተፈትተው እንደ ቀድሞው የቤተ ክርስቲያን መሪ ባይሆኑም የክርስቶስን ሥራ በሚስጢር የሚያስፋፉ በሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ናቸው ። ቀድሞ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በነበሩበት ሥፍራ ዛሬ ለሁለት ጌታ አዳሪዎች ማለት የኮሙኒዝም ደጋፊዎችና ክርስቶስን ደግሞ እናመል ካለን በሚሉ ተይዞአል ።

ታዲያ ዓላማቸው ቤተክርስቲያን እንድታድግ ሳይሆን በውጭ ቀናተኛ የሃይማኖት ሰው መስለው እግዚአብሔር የለም የሚሉ በኮሚኒስቶች መሪዎች የተ ካኑ ናቸው ።

ይመስላችኋል! ቤተ ክርስቲያን በእንደዚህ ዓይነት መሪዎች ስር እድገትን የምታገኝ? አይደለም ። እነ ዚህ አንዲትን ልጃገረድ እወድሻለሁ ብሎ አባብሎ እሜካ ወስዶ ፈቃዱን ከፈጸመ በኋላ በአጋም እሾህ ሙልጭ አድርጎ ገርፎ በኋላም ገደል ገፍቶ እንደሚ ጨምራት ጨካኝ አረመኔ ጐረምሳ ናቸው ። ክርስቲያ ኖች ሆይ! ንቁ ።

## ሁለተኛው ክፍል

እነዚህ ደግሞ የቅስና ማዕረግ ሳያገኙ ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ በምንም ሥራ ተካፋዮች ያል ሆኑ ተራ ምዕመናን ናቸው ። የሚገርማችሁ ነገር ቢኖር እነዚህ ተራ ምዕመናን የጠለቀ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ባይኖራቸውም ሁልጊዜ ደስተኞች ፣ ሞቃት ፣ ልበ ሙሉ ፣ ስለወንጌሉ ታላቅ ቅናት ያላቸው ናቸው ። ምን ጊዜም ሞረድ ቢላን እንደሚስለው እሳ ትም ወርቅን እንደሚያጠራው እንደዚሁ ስደትና መከራ ክርስቲያኖችን ይበልጥ ያዘጋጃቸዋል ። በቅ ርቡ የሚመለስ ጌታቸውን ነቅተው እንደጠበቁት የአ ዋጃቸው ድምፅ ነው ። ሬድ ስታር የተባለው የሶቪየት ጋዜጣ ክርስቲያኖችን ሲነቅፍ እንዲህ ብሎአል ፤ «የክ ርስቶስ ተከታዮች ዓለምን ሁሉ በትምህርታቸው ለማጥለ ቅለቅ የሚጥሩ ሰውን የሚያጠምዱ ስግብግቦች ናቸው» ። ይላል አዎን ጌታም እነ ጴጥሮስን አሣ ከማጥመድ ሲጠራ ቸው ኑ እና ተከተሉኝ ሰዎችን የምታጠምዱ አደርጋ ችኋለሁ ብሎአል ። ታዲያ በእንደዚህ ያለ የጭንቅ አገር የክርስትና ትምህርት የተጠላ ቢሆንም የሕይወታ ቸው ምስክርነት ከሰዎች ጋር በሰላም እንዲኖሩ ተወ ዳጅና ተናፋቂ አድርጎአቸዋል ።

ለምሳሌ ብዙ ልጆች ያላቸው የኮሚኒስት ቤተ ሰቦች በጉረቤታቸው ቢኖሩና የሰዎቹም የወር ገቢ ቤተሰቡን ለመቀለብ አነስተኛ መሆኑን ከተረዱ ጠጋ ብለው ምነው ከልጆቻችሁ ጥቂቶቹ እኛ ጋ ቢኖሩ ብለው ፈቃድ ከጠየቁዋቸው በኋላ በሚገባ ከሕይወታ ቸው መሠረት ጀምሮ ስለክርስቶስ እያስተማሩ ከማሳ ደጋቸውም ሌላ በሥጋዊውም መንገድ በማጥናቸው

ምንም ተቀማጭ ገንዘብ ሳያደርጉ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አሟልተው ያሳድጓቸዋል ። ከወላጆቻቸው ቤት ይልቅ ፍቅርን እያገኙ በክርስቶስም ትምህርት እየተ መሠረቱ ያድጋሉ ።

ሰው ለሚደረግለት ውለታ ሁሉ ምክንያቱን ለማወቅ ይፈልጋልና ለምንድነው ይህን ሁሉ ፍቅር ያደረጋችሁልን? የሚል ጥያቄ ከወላጆቻቸው ሲሰነዘር ባቸው «ክርስቶስ ፍቅርን እንድናሳይ አዞናል» የሚል መልስ ይሰጡዋቸዋል ። ይህን በመሰለ መንገድ የክር ስቶስ ወንጌል ይስፋፋል ። አንድ ጊዜ የኮሚኒስቶች መጽሔት የክርስቲያን ነጋዴዎች የሚሸጡትን እቃ በወንጌል ወረቀት ከመጠቅለላቸውም ሌላ ሌሊት ሌሊት እየሠራ ጥቂት ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ሥራ ውን የሚያቆም ማተሚያ ባልታወቀ ሥፍራ እንዳላ ቸውና ከት/ቤት የሚወጡ ሕፃናት ከማን እንደተቀ በሉ ሳይታወቅ ብዙ ወንጌሎችን ተሸክመው ወደቤታ ቸው ይመጣሉ ። ስለዚህም የስለላ ጓድ በየቦታው ተልከዋል» የሚል ጽሑፍ ነበር ። እነዚህ ክርስቲያኖችን ከሌሎች በስም ብቻ ክርስቲያን ከሆኑት ይልቅ ሠራተኞችና ብርቱዎች እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምን ይመስላችኋል)? ኮሚኒስቶች እነሱን ለማጥፋት ብለው የሚያስነሱባቸው የስደት ሰደድ እሳት ነው ።

አንድ ታላቅ ተናጋሪ «ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ቢቻል ኖሮ ኔሮ ባጠፋቸው ነበር ፤ ዳሩ ክርስቲያኖች ቢገደሉም ደማቸው ክርስቲያኖች ያፈራል» በማለት ተናግሯል ።

# ሶስተኞቹ ክፍሎች

ሦስተኞቹ ክፍሎች ደግሞ ማለት ፍቃድ ያላትና ፈቃዱ የተሟላ ሳይሆን እንዲያው ቤተ ክርስቲያን አለ ተብሎ ለወሬ እንዲመች በኮሚኒስቶች ሥር የምትተዳደር አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ብቻ እንጂ ሕፃናትና ጎልማሶች እንዲመጡ የማትፈቅድ ቤተክርስቲያን ናት ።

ይህች ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የለም በሚሉ በኮሚኒስቶች ስለምትተዳደር በመንግሥት፡ እውቅ ናት። ያች የምትሳደድ እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን በሕብረት ያቋቋሙት የወንጌሉን ብርሃን በትጋት የሚያስፋፉ አንድ ማኅበር አለ ።

ይህን በመሰለ ቆራጥነት የክርስቶስ ተከታዮች በጭንቅ ምድር ክርስትናን ያስተምራሉ ። ከተያዙ እሥራት ፣ ግርፋትና ሞት እንዳለባቸው ቢያውቁም የክርስቶስ ፍቅር መከራን እንዲንቁ ኃይል ሰጥቶአቸዋል ።

አንድ ስለምድር በታች ቤተ ክርስቲያን የሰማ ይህችን ቤተክርስቲያን ለማየት አንዳንድ ጥያቄዎችን ጠይቆ ለመረዳት የፈለገ ሰው በመላው የኮሚኒስት አገር ከዞረ በኋላ ይችን ቤተ ክርስቲያን እንዳላገኘ ወደሃገሩ ከተመለሰ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ገልጾአል ግን ያ ሰው ያደረገው ያልተማሩ ሰዎች ወደሞሉበት ወደ መካከለኛው አፍሪካ ሄዶ ከጐበኘ በኋላ «አገሩን በሞላ ጐበኘሁ ፣ ነገር ግን "ፕሮዝ" የሚናገርን አላገኘሁም» እንደሚል ሰው ነው ። ቢያስተውል ግን እነዚያ ሰዎች የሚናገሩት ፕሮዝ ነው ። ነገር ግን የሚናገሩት ቋንቋ መሆኑን እንጂ ምን ዓይነት ቋንቋ እንደሆነ አያውቁም? ።

ለምሳሌ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ክርስቲያኖች ምንድናችሁ ብንላቸው «እኛ እስራኤላውያን ነን» ይሉናል ። ክርስቲያን የሚለው ስም ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጣቸው በአንጾኪያው ጉባዔ ነበር ። በሪፎርሜሽን (ተሃድሶ) ጊዜ ሉተርን ተከትለው ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተገንጥለው የወጡ ሁሉ ሉተራውያን መሆናቸውን አያውቁም ፤ ሉተር ራሱ ማንም በሱ ስም እንዳይጠራ ይቃወም ነበር ። በኋላ ግን ሉተራውያን የሚለው ስም እየፀና ሄደ ፤ ይህም ከምድር በታች ያለችው ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስም የተሰጠው በኮሚኒስቶች ነው ። ማንም የዚች ቤተክርስቲያን አባል የሆነውን ሰው አንተ ምንድነህ ቢሉት ክርስቲያን መሆኑን እንጂ የምድር በታች ቤተ ክርስቲያን ምዕመን መሆኑን አይገልጽም ። በውቅያኖስ ውስጥ አንድ ሰው ዓሣ ነባሪን ሳያገኝ ቢቀር ዓሣ ነባሪ ውቂያኖስ ውስጥ ፈጽሞ የለም ማለት ነውን? በሚቀጥለው ምዕራፍ የታወቁ የሶቪየት ሕብረት ጋዜጦችና መጽሔቶች ስለነዚህ ቤተክርስቲያን ምን እንዳተቱ ከየጋዜጦች ላይ አንዳንድ ቁም ነገርን በመውሰድ ጽፌአለሁ ፤ ይህም ለታሪኩ እውነተኛነት ማስረጃ ሊሆን እንደሚችል በማመን ነው ።

## ምዕራፍ ፲

የክርስትናን ትምህርት በኮሚኒስት ሩማንያ እን ዳስፋፋን ሁሉ በሶቪየት ሕብረት ወታደሮች መካ ከል ሁሉ እንዴት እንዳስፋፋን ነግሬአችሁ ነበር ። እንዲሁም ኮሚኒስቶችንና በነሱ ሥር ያሉትን ሕዝብ ከቁሳቁስ ባርነት ነፃ ለማውጣት የናንተ የክርስቲያ ኖች እርዳታም እንደሚያስፈልገን ገልጬላችሁ ነገሩ ሲታይ ብዙ ሠራተኞችን ሊያሰማራ የሚችል ሰፊ የሥራ መስክን ይመስላል ። የሚዋጋ ኃይል ደግሞ አለ።

እውን ይህች አሁን ስናገርላት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አሁን በሩሲያና በሌሎችም ኮሚኒስት አገ ሮች አለች? ይህም ግሩም በሆነ መንገድ ከራሳቸው ከኮሚኒስቶች መጽሔትና ጋዜጦች መልስ ልናገኝለት እንችላለን ። አስተውሉ ፤ ይህች ቤተክርስቲያን መሬት ውስጥ ተቀብሮ ግማሽ ጐኑ ብቻ እንደሚታይ ነገር ናት ፤ የሚቀጥሉትም ማስረጃዎች ከልዩ ልዩ ምንጮች የተወሰዱ ናቸው ።

በኅዳር ፯—፲፱፻፷፮ ዓ. ም. በሱሁሚ (ካውካስስ) የዚች ቤተክርስቲያን መሪዎች በአንድ ሚስጢራዊ ገላጣ ጫካ ላይ ታላቅ ሃይማኖታዊ ስብሰባን አድር ገው ነበር ። ይህን ስብሰባ ለመካፈል ብዙ ክርስቲያ ኖች ከተለያዩ አገሮች መጥተው ነበር ። በዚህ ስብሰባ ላይ ፵፯ ወጣቶች ጌታን እንደግል አዳኛቸው ተቀበ ሉና እንደሐዋርያት ዘመን በአንድ ወንዝ አጠመቅና ቸው ። የዚህች ቤተክርስቲያን መሪዎች በምዕራብ ያሉት እንደሚያደርጉት ከዩኒቨርስቲ ወይም ከልዩ ልዩ ሰሚ ናሪ የተመረቁ አይደሉም ። ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ያጠመቀው ዲያቆኑ ፊሊጶስ ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተመረቀ አልነበረም ። ፊሊ

ጶስ ለዚያ ሰው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በነገረውና ወደውኃ ምንጭ በደረሱ ጊዜ ጃንደ ረባው እንዲህ አለ ፤ «እይ! ውኃ እዚህ አለ እንዳልጠ መቅ ማን ይከለክለኛል» ።

ፊልጶስም መለሰ «በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈ ቅዶልሃል» አለውና ዉዲያውኑ ወደውኃው ወስዶ አጠ መቀው ። እንግዲህ የንግግራቸውን ርዝመት መገመት ቢያስፈልግ አንድ ሰዓት ነው ። ስለዚህ እነዚያ ፶፺ ወጣቶች እንዳመኑ ወዲያውኑ ቢጠመቁ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ውጪ አይሆንም ።

ግንቦት ፩ ቀን በየዓመቱ ኮሚኒስቶች ማንም ሰው እንዲሰበሰብበት ይገባል የሚሉት ታላቅ ትዕይ ንት በአደባባይ ላይ ያሳዩበት ቀን ነው ።

ክርስቶስ ታምራቱን ለመግለፅና ተቃዋሚዎቹን ፈሪሣውያንን ለማስደነቅ የሠርጋቸውን ቀን እንደመ ረጠ ሁሉ እኛም የሚደነቅ ብርሃን የሆነውን የወንጌ ሉን ኃይል ለሚያሳድዱት ለኮሚኒስቶች ለመስበክ ይህንን የበዓላቸውን ቀን መረጥን ።

የመምሕራን መጽሔት በመባል የታወቀው (በጳ ጉሜ ፳፫ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የወጣ) በሮስቶቮን ዶን ያሉ የባቢቲስት ቤተክርስቲያን መሪዎች በኮሚኒስት መሪ ዎች በተሾሙና የቤተክርስቲያን እድገት ተቀናቃኞች በሆኑ በአፍ ብቻ የሃይማኖት ደጋፊዎች ለሙምስል ፕሮፓጋንዳን ለሚያበዙ የውሸት ካህናት ሥር እንዲ ሆኑ ምዕመናን አናስመዘግብም በማለት ታላቅ ትዕ ይንተ ሕዝብ አድርገው እንደነበር አትቷል ። ኮሚ ኒስቶች ታላላቅ ከሆኑ ቦዓላቶቻቸው አንዱን ግንቦት ፩ ቀን ለማክበር ተሰብስበው ሳለ በኮሚኒስቶችና በተ

ከታዩቻቸው ያልታሰበ ሌላ 1500 ሰዎች ያሉበት ሰ ልፍ በአደባባይ ላይ ታዩ!

የነዚህ ሰዎች ዓላማ ቤተክርስቲያን በኮሚኒስት በተሾሙ የሃይማኖት መሪዎች ሥር እንድትሆን የታ ዘዘውን ትእዛዝ ለመቃወም ነበር ፤ በርግጥ ሞት እንደ ሚጠብቃቸው ያውቃሉ ፤ ቢሆንም ሁሉን በድፍረት ያደርጉት ዘንድ የክርስቶስ ፍቅር ግድ አላቸው ። መጽ ናኛቸው የነበሩትም ጥቅሶች ጳውሎስ «ለኔ መኖር ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና» እንዲሁም ጌታ ኢየ ሱስ «ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን ሊገድሉ የማ ይችሉትን አትፍሩ» ያለውና እንዲሁም ዮሐንስ በራ ዕዩ «እነሆ ከመሠዊያው በታች ስለእግዚአብሔር ቃል የተገደሉት ሰዎችን ነፍሳት አየሁ» የሚሉት ጥቅሶች ነበሩ ። በዚህ ጊዜ እነዚያ ክርስቲያኖች በዚያ ታላቅ ጉባዔ ውስጥ ተበታተኑ ፤ ግማሾቹ አዛፍ ላይ ወጡ ፤ ግማሾቹም ከፍታ ላይ ሆነው የወንጌሉን የምሥራች በድፍረት ለከበባቸው ሕዝብ ያሰሙ ጀመር ። በዚህም ስብከት ኮምዞሞልስ በመባል ከታወቀው የወጣት ኮሚኒስቶች ፓርቲ አባል ከሆኑ ወጣቶችና ከሌላውም ሠራተኛ ሕዝብ ብዙዎቹ ክርስቶስን እንደግል አዳ ኛቸው አድርገው ተቀበሉ ።

ወዲያው ሌላ ያልታሰበ ሽብር በዚያ ታላቅ ጉባዔ መሃል ተፈጠረ ብዙ የኮሚኒስት ወታደሮችን የያዙ አውቶሞቢሎች ክርስቲያኖችን ከበቡዋቸው ፤ ቢሆንም በዚያ ስብከት ያመኑትን ወንድሞች ቀደም አድርገው «ዮንሃ» ወደሚባለው ወንዝ ወስደው አጥምቀዋቸው ነበር ።

አቺቴልስካይ ጋዜጣ» ወይም የመምሕራን መጽ ሔት የተባለው በሌላው እትሙ «ሕገወጡ የባፕቲ

ስት ቤተክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጽሑፎችን የሚያ ትም ማተሚያ ቤት በሚስጢር አቋቁሟል ሲል ከሰሰ ። (በሩሲያውያን አነጋገር ባፕቲስት ሲባል ሌሎች የክ ርስትና እምነት ክፍሎችንም ይወክላል» ።

እነዚህ 1500 ሰዎች ስለሃይማኖት ነፃነት ሲሚ ገቱ ዋሉ ፤ በአጠገባቸው በመኪና ያልፉ የነበሩ ሰዎች ከመኪናቸው ውስጥ አንዳንድ ቆሻሻ ነገርን ይጥሉ ባቸውና ይሰድቧቸው ነበር የተሰበሰቡት በኮሚኒስት ፓርቲ ምክር ቤት ፊት ለፊት ነበር ። በማግሥቱ እነ ዚህ ሰዎች ወደሕንፃው ገብተው አንዳንድ ዝቅተኞ ች የኮሚኒስት ባለሥልጣኖችን እንዲያነጋግሩ ተፈ ቀደ ። እነዚህም ሹማምንት ጉዳዩን ከተረዱ በኋላ ጉዳዩ ለብሬዥኔቭ እንዲተላለፍና መልስ እስኪመጣ እንዲ ጠብቁ ተወሰነ ፤ ነገር ግን በድንገት በሰባት ሰዓት ከ፵፩ (በሩሲያ ሰዓት አቆጣጠር) በውስጣቸው ፖሊሶች የሞ ሉባቸው ፳፭ አውቶቡሶች መጥተው የክርስቶስ አር በኞች ዝነኛና ተወዳጅ የሆነውን «የጌታን መስቀል መሸከም ምንኛ ደስ ይላል» የሚለውን መዝሙር ይዘ ምሩ ነበር ። ፖሊሶችም እነሱን ፀጥ ለማሰኘት ባለኃይ ላቸው ቀጠቀጡዋቸው ፤ የዝማሬም ድምጽ በአውቶቡስ ከሞሉት ክርስቲያኖች ይሰማ ነበር ፤ ይህም የሆነው ብዙ ሕዝብ እያዩና እየሰሙ ነው ። እነዚህ ክርስቲያ ኖች ወዳልታወቀ ቦታ ከተወሰዱበት ቀን አንስቶ ቆራጥ የቤተክርስቲያን መሪዎችና የክርስቶስ በጐች እረኞች የነበሩት ወንድሞችን ጂ. ቤንስ እና ሆሮብ መጥምቁ ዮሐንስ ከታሠረ በኋላ ክርስቶስ «መንግ ሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» በማለት የመ ጥምቁ ዮሐንስን ስብከት በመስበክ እንደመሰለው ሁሉ እነዚህም ሰዎች ስለእምነት ሲከራከሩ ያለም

ክንያት ለታሠሩት ክርስቲያኖች መብት ወደ ኮሚኒ ስት ሹማምንት ቢሮዎች በመሄድ ይከራከሩ ጀመር ። ቢሆንም ማንም የሚሰማቸው ሰው አጡ ። ከፉኛ ከተ ደበደቡ በኋላ ወዴት እንዳደረሱዋቸው ሳይታወቅ እንኳ ብዙ ጊዜ አለፈ ፤ በኋላ ግን «በሴፎርቶብስካይ» እስር ቤት እንዳሉ ተገለፀ ። ይህን የሰሙ ክርስቲያኖች ሁሉ የደከመ እምነታቸው ታደሰላቸው ፤ ጳውሎስ በፊ ልጵስዮስ ፩ ፡ ፳፱ «የተጠራነው በክርስቶስ ለማመን ብቻ ሳይሆን ስለእርሱ መከራንም ለመቀበል ነው» ያለው ቃል ይበልጥ ትርጉም አገኘ ፡ ሌሎች ደግሞ ያላንዳች ፍራቻ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴን መምራት ቀጠሉ ። ከሕዝቡ አእምሮ ሃይማኖትን ለመደምሰስ ና እግዚአብሔር የለም የሚል ጽሑፍ በየጊዜው ይበ ተን ጀመር ። በአንዳንዱም በክርስቶስ አዳኝነት የሚያ ምኑ ያልታሰሩ ክርስቲያኖች ሁሉ የጌታን ሥራ በት ጋት ይሠሩና ኮሚኒዝምንና አንዳንድ ቀድሞ የሃይማ ኖት መሪዎች የነበሩትን ከዳተኞች ያወግዙ ነበር ።

ፕራዎዳ ቦስቶካ የሚባለው መጽሔት ደግሞ እነ አሌክሲስ ኒቪሮቭ ፡ እነ ቦሪስ ጋርማስሆቭ እነ አክሴን ዙቦበን የወንጌል መልእክት ከአሜሪካ እንዲተላለፍ ና እንዲያው በቴፕ እየቀረጹ ለብዙ ሰዎች ከማሰማ ታቸውም በላይ ስለማኅበራዊ ኑሮ እንወያያለን በማ ለት የድብቅ የፀሎትና የዝማሬ ስብሰባ ያደርጋሉ በማ ለት ከሰዋቸው እንደነበር ይታወሳል ።

መስከረም ፫/፲፱፻፷፯ የወጣው ሶቪየትስካይ ሞል ዳቪያ የሚባለው መጽሔት ደግሞ በባቡር ተሳፍረው ከሬኒ ወደቺስናው ይመጡ የነበሩት ሶስት ጉልማሶች «የወጣትነት ጊዜያችንን ለጌታ እንስጥ» የሚለውን የክርስቲያኖች መዝሙር እየዘመሩ ያለአንዳች ፍር

ሃት ስለክርስቶስ ወንጌልና ስለመንግሥቱ ምሥራች ያሰሙ እንደነበር አትቷል ። እንደዚህ ስለሃይማኖታዊ ጉዳይ መሰብሰብ አስቸጋሪ በሆነበት ቦታ ክርስቲያኖች የልደት በዓላቸውን እንደሚያከብሩ በማስመሰል በየቤታቸው በመገናኘት መጽሐፍ ቅዱስን ያጠኑና ለሚሰቃዩ ወንድሞቻቸው ይጸልዩ ነበር ።

ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ. ም. የወጣው ፕራቭዳ ኡክሬኒ የተባለው መጽሔት በሩሲያ ያለችውን ቤተክርስቲያን ይመራ ስለነበረው ስለወንድማችን ፕሮኮፊብ እንዲህ ብሎአል ። «ፕሮኮፊብ ከአሁን በፊት ደጋግሞ ወንጌልን ሲሰብክ ስለተያዘ ለሶስት ጊዜ በማከታተል ታሥሮ የእሥራት ጊዜውን ጨርሶ ከወጣ በኋላ እንደገና በሚስጢር የሰንበት ት/ቤት ከፍቶ ሲሰብክ በመገኘቱ ወህኒ እንዲገባ ተፈረደበት ይላል»።

በ፲፱፻፸፮ የወጣው ቁ. ፱ የሆነው ናውካይ ሬሉጂያ የተባለው መጽሔት ደግሞ ክርስቲያኖች የታላላቅ የኮሚኒስት መሪዎችን ፎቶ በመጽሐፋቸው ሽፋን ላይ በማድረግ በውስጡ ግን የክርስቶስንና የሐዋርያቱ ትምህርት የሞሉባቸው መጽሐፍት ያሠራጫሉ በማለት አመለከተ ።

ባኪንስኪ ራባሁ የተባለው አንድ የባኩ ሠራተኞች መጽሔት ደግሞ የአንዲት ቀድሞ የወጣቶች ኮሚኒስት ፓርቲ አባል የነበረችና በኋላ ግን የክርስቶስ ተከታይ የሆነች ልጃገረድ ለአክስቷ የጻፈችውን ደብዳቤ ይህን በሚመስል መልእክት አወጣ «..... ውድ አክስቴ እጅግ አፍቃሪ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ስም ሰላም እልሻለሁ ..... አክስቴ ታዲያ ይህ አዳኝ እኔንና አንቺን እንዴት እንደሚወድ ልገልጽ አልች

ልም..........እሱ ተከታዮቹን ጠላቶቻችሁን ውደዱ ስለሚያሳድዱዋችሁም ፀልዩ የሚረግማችሁንም መርቁ ብሎ አስተምሯል» ይኸውም መጽሔት ሐተታውን በማስረዘም ፒተር የተባለው አንድ ወጣትን ስብከት እንዲህ አድርጎ አውጥቶታል «የቀደሙ ክርስቲያኖች እንዳደረጉት ለክርስቶስ በስደትና በመከራ ልንቆም ይገባል ። መመሪያችንም ሌላ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ነው.....ወጣቶችንም ወደርሱ ለማምጣት ይበልጥ ተግተን መሥራት አለብን « ጥር ፳፯/፲፱፻፳፯ ዓ. ም. የወጣ) ።

ካዛክታንስካይ ፕራቭዳ በሰኔ ፴/፲፱፻፳፯ የወጣው መጽሔት ደግሞ በተማሪዎች መካከል ውድድር ሲደረግ ከፍተኛ ውጤት የሚያገኙ ከክርስቲያን ቤተሰብ የሚገኙ እንደሆኑ ጽፎአል ።

ሲሊያሲንክ የተባለ መጽሔት ደግሞ አንዲት ኒና የተባለች የወጣቶች ኮሚኒስት ፓርቲ አባል የነበረች ክርስቲያኖች በሚስጢር ወደሚሰበሰቡበት ጉባዔ ሄዳ ስብከቶችን ከሰማች በኋላ እንዴት ወደክርስቶስ እንደተመለሰች አትቷል ።

ካዛክስታን ስካይ ፕራቭዳ ደግሞ (በጳጉሜ ፲፱፻፳፯ የወጣ) ደግሞ ክርስቲያኖቹ ክላሴንና ንዳር ቴሌጊን ሕፃናትን ስለክርስቶስ ማስተማራቸው እንደ ወንጀል ስለተቆጠረባቸው እሥራት እንደተፈረደባቸው ጻፈ ። ምን ያህል ጊዜ እንደተፈረደባቸው ግን አልጠቀሰም ።

የካቲት ፳፭/፲፱፻፳፫ የወጣው ፕራቭዳ ደግሞ በሺህ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች በቀበቶዎችና (በሪባንስ (ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እየጻፉ እንዲ

ጠቀሙ ይህን እቅድ ያወጣው ስታስዮክ ሆኖ ስለተ ገኝ ወህኒ ወረደ ይላል ።

ክርስቲያኖች ወህኒ ወርደው ብዙ ሥቃይን ያለ ፍርድ ከተቀበሉ በኋላ እንደገና ለፍርድ በዳኛ ፊት ይቀርባሉ ። በዚህ ጊዜም ቢሆን ምንም የፍርሃት ምል ክት አይታይባቸውም ።

እንዲያውም በአንድ ዳኛ ፊት ክርስቲያኖችን ወክሎ ለጥያቄ ቀርቦ የነበረውን ሰው ዳኛው «ለምን ድነው ስብሰባችሁ በሕግ የተከለከለ ሲሆን ሰውን ሁሉ ወደዚያ ወዳልተፈቀደ ስብሰባችሁ የምትስቡት? ቢለው ቢቻልስ ዓላማችን ዓለምን ሁሉ ክርስቲያን ለማድረግ ነው ሲል መልሶለታል ። አንድ ጊዜ ደግሞ ክርስትና ከሳይንስ ጋር አይስማማም ብሎ ሲናገር የሰማች አንዲት ክርስቲያን ልጃገረድ እንዲህ አለ ችው ፤ ለመሆኑ አንተ ከነአንስታይንና ከኒውተን ይበ ልጥ ስለሳይንስ ታውቃለህን? እነሱ በእግዚአብሔር መኖር የሚያምኑ ነበሩ ።

«በነቢያቱ የተመሰከረለትን ሐዋርያቱም የሰበ ኩትን ክርስትናን ክርስቶስ እንዳስተማረው ብናስተ ምር ዓለምን ከማኅበራዊ ችግር ነፃ እናወጣት ነበር ። ያለዚህ ሃይማኖት ከልዩ ልዩ ፍልስፍናዎች ጋር በሚ ያደርገው ውጊያ ድል እንዲያገኝ መርዳት የእያንዳን ዳችን የተቀደሰ ተግባር ሊሆን ይገባዋል» እስቲ ታላቁ ፊዚዎሎጂስት ፓቭሎቭን አሳቡ የራሳቸው መጻሕፍ እርሱ ክርስቲያን እንደነበረ ያስረዳ የለምን?

ማርኮስ ራሱ ዳስ ካፒታል በተባለው መጽሐፍ መቅድም ላይ «ክርስትና በተለይም የፕሮቴስታንትን ፎርም የያዘው በኃጢአት ምክንያት ለጠፋው ጠባይ

ተሃድሶን ሊያመጣ ይችላል ። እኔ ራሴም በኃጢአት ምክንያት የጠፋ ጠባይ አለኝ ሲል ጽፎ የለምን? ታዲያ እናንተ የማርክስ ተከታዮች ነን የምትሉ ለምን ክርስቲያኖች ሆናችሁ ብላችሁ ትከሱናላችሁ?

ሌላ ቀን ደግሞ በሌላ ፍርድ ቤት ለቀረበው አን ድ ክርስቲያን ዳኛው ሃይማኖታችሁ ከሳይንስ ጋር አይስማማም ላለው እንዲህ ብሎ መለሰለት ።

«ክቡር ዳኛ ሆይ ምንም ያህል በሳይንስ የተራ ቀቅህ ብትሆን ክሎሮፎርምንና ሌሎችም ብዙ መድ ሃኒቶችን ከቀመመው ከታላቁ ሳይንቲስት ከሲምፕስን አትበልጥም ። አንድ ቀን ታዲያ ከተረዳሃቸው ነገ ሮች ሁሉ ይበልጥ ቁም ነገር ይዞአል ብለህ የምትገ ምተው ምንድነው ቢሉት እኔ ሃጢአተኛ መሆኔንና በእግዚአብሔር ፀጋና በመስቀል ላይ በፈሰሰው በጌታ ኢየሱስ ደም የኃጢአት ስርየት ማግኘቴን ማወቄ ትልቅና አስፈላጊ ቁም ነገር ያለበት ነው ። ይህ ሰው ምንም ያህል በሳይንስ ቢራቀቅ ሳይንስ አምላኩን እንዲክድ አላደረገውም ።

ከአንዲት ክርስቲያን ደብዳቤ ላይ የተወሰደው ቃል ደግሞ እንዲህ ይላል «ጥሩ ክርስቲያን እንድን ሆን ብቻ አንጸልይም ፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ፊት መሪያችን ክርስቶስን በመምሰል እርሱ መስቀሉን በፈቃደኛነት እንደተሸከመና እኛም መስቀላችንን ተሸክመን እንድንከተለው እንዳዘዘን በበጐ ፈቃድ እኛም የርሱን አርአያ ለመከተል እግዚአብሔር ኃይ ልን እንዲያበዛልንም ነው ። በፍቅር ሰንሰለት የተሳሰሩ ክርስቲያን ወንድሞች ስለእምነታቸውና ስለጌታቸው ክብር ደማቸውን ያፈሳሉ ፤ መከራንም ሁሉ ይታገሳሉ።

ጥር ፲፰ ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. የወጣው ፕራቭዳ ቦስ ቶካ የተባለው መጽሔት ደግሞ እንዴት ሲቪሲዮክ የተባለች ሴት ክርስትናን ስታስፋፋ ስለተያዘች ተከሳ ፍርድ ቤት በቀረበችበት ጊዜ ዳኛው «ለመሆኑ ክር ስቲያን እንድትሆኚ የመከረሽ ማነው»? ቢላት «እግዚ አብሔር በፍቅር ገመድ ሳበኝ እንጂ ማንም ሰው አል መራኝም» አለችው ። መሪያችሁስ ማነው ፤ ለሚለው መጠይቅ ደግም «እኛ የሰው መሪ የለንም በማለት እንደመለሰችለት ጽፎአል ። ይህ ብቻ ሳይሆን ሕፃናቱን የኮሚኒስቶች ዓርማ የሆነው ቀይ ከረባት እንዳታደ ርጉ የመከራችሁ ማነው ቢባሉ ማንም አልመከረ ንም እኛ ራሳችን በፈቃዳችን አደረግነው» ማለታቸ ውን አትቷል ።

የክርስቲያኖች ስደት አሁንም አልበረደም ። እውነ ተኞቹ ክርስቲያኖች አሁንም በመሳደድ ላይ ናቸው ። እንዲያውም ስደቱ ከመቸውም ይልቅ እየባሰ ሄዷል ። በየጊዜው የሚወጣውን የሶቪየት ሕብረት ጋዜጣ የብዙ ክርስቲያኖችን መታሠር ያወራል ።

የተባበሩት መንግሥታት በሶቪየት ሕብረት የሚ ኖሩ ወላጆች ልጆቻቸውን ሃይማኖታዊ ትምህርት እን ዲያስተምሩ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ደብዳቤ መላኩ ቢታወስም በመንግሥቱ ፈቃድ ያላት የባፕቲስት ቤተክርስቲያን አባል የሆነችው ማክሪን ኮና ስድስት ልጆቿን ክርስቲያናዊ ትምህርት ከማስተማርዋም በላይ የኮሚኒዝም መለዮ የሆነውን ቀይ ከረባት እንዳያስሩ በማስተማርዋ ስለተረጋገጠ ልጆችዋ ተነጥቀው ወዳልታወቀ ቦታ ተወሰዱባት ። እናትዮዋም የልጆችዋን ወደ አልታወቀ ቦታ መወሰዳ ቸውን በሰማች ጊዜ የተናገረችው «ይህን ሁሉ ስቃይ

ስለእምነቴ ስል መቀበል አለብኝ» የሚል ነበር ሲል ጽፎአል ።

በኋላ ግን በእምነት ምክንያት ልጆችዋ የተነጠቁባት ምስኪን እናት ለልጆችዋ ማሳደጊያ የሚሆን ካቅሟ በላይ የሆነ ገንዘብ እንድትከፍል ተገደደች ፤ ቢሆንም ከልጆችዋ ከተለየች አያሌ ጊዜያት አልፈዋል ። ምናልባት የነዚያ ጨቅላ የሆነው የሕፃናት አእምሮ በአጉል ፍልስፍና ተሞልቶ የእምነቷ ተቃራኒዎች ሆነው ይሆናል ፤ ክርስቲያን የሆናችሁ እናቶች እስቲ በአርምሞ የዚህችን ሴት ጭንቀት አስቡት?!

አክቴልስካይ ጋዜጣ ደግሞ ተመሳሳይ ታሪክን ጽፎአል ። ክርስቲያን የሆነው አግናቼ ሙሊንና ሚስቱ ስለእምነታቸው ዳኛ ፊት በቀረቡ ጊዜ ዳኛው አሁን ከልጅህና ከእምነትህ የቱ እንደሚበልጥብህ ምረጥ ቢለው እምነቴ ይበልጥብኛል የሚልን መልስ ሰጠ ፤ ጋዜጣው በልጁ ላይ ምን ውሳኔ እንደተላለፈ ግን አልገለጸም ። ጳውሎስ እንዲህ አለ «እግዚአብሔርን ለሚወዱ ነገር ሁሉ ለበጐ እንዲሆን እናውቃለን «እኔ ራሴ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተገኙት ሕፃናት ከወላጆቻቸው ተነጥቀው በኮሚኒስት ት/ቤት ብዙ ከተማሩ በኋላ ያየተማሩት የእምነት ተቃራኒ ትምህርት በምነታቸው ላይ ምንም ለውጥ ሳያመጣባቸው ትምህርታቸውን ፈጽመው ከመውጣታቸውም በላይ ብዙዎቹን የእምነታቸው ተከታዮች እንዳደረጉዋቸው አውቃለሁ በጣም ያስደንቃል!

አንድ ጊዜ ጌታ እንዲህ አለ «ማንም ልጁን.... ወይም..... ከኔ ይልቅ የሚወድ ለኔ ሊሆን አይገባ

ው·ም» ያንን የፈጸሙ ቆራጥ ክርስቲያኖች ዛሬም ቢሆን በኮሚኒስት ምድር ይገኛሉ ።

እስቲ ወላጆች የሆናችሁ ከምትወዷቸው ልጆቻችሁ ተለይታችሁ ለመኖር ሞክሩ ፤ ያኔ ስለእምነታቸው ከልጆቻቸው የሚነጠሉ የክርስቲያኖች ጭንቀት ሊሰማችሁ ይችላል ።

የካቲት ፳፱/፲፱፻፳፯ የወጣው ዝናሚያ ኢዮኖስቲ የተባለው መጽሔት ደግሞ ሚስስ ሲትስ የተባለች ሴት ልጅዋ ፈሪሃ እግዚአብሔር ስላስተማረችው ቪሴቴበላብ የተባለው የምትወደው አንድ ልጅዋ እንደተነጠቀባት ጽፎአል ።

ሌላው ሶቪየት ስካይ ሮዚያ የተባለው ጥር ፲፫ ፲፱፻፳፰ የወጣ መጽሔት ደግሞ ዛቡቢያ የተባለች ሴት ልጅዋን ታኒያን የክርስትና ትምህርት ስላስተማረቻት ከርሷ ተነጥላ እንደተወሰደች አትቷል ።

በሩሲያ ያሉ ቆራጥ የኦርቶዶክስ ካህናት ብዙዎቹ ስለእምነታቸው በወህኒ ናቸው ። በዚያ ውብ በሆኑት ቤተክርስቲያኖቻቸው ውስጥ ያሉት መቁጠሪያ የቅዱሳን ቅብዓ ሚሮን ስዕል እጣን ጧፍና ሌሎችም ንዋየ ቅዱሳት ያሏቸውም ምዕመናኑ ያለካህናቶቻቸው ናቸው ። ቄሶችም የክህነት ልብስ የላቸውም ፤ ቅዱሳን የፀሎት መጻሕፍቶቻቸውንም ተነጥቀዋል ። ታዲያ በወህኒ በከባድ ስቃይ ውስጥ እያሉ እምነታቸው ከድሮው ይልቅ ምንኛ ያየለ ይመስላችኋል? ምንም እንኳ አንዳንዶቹ ክርስቶስን ክደው ለሁለት ጌታ አዳሪዎች ቢሆኑም እውነተኛይቱ የኦርቶዶክስ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ዕኑ የክርስቶስ ምስክር ናት ።

ከዚህች ቤተክርስቲያን ታላላቅ የሃይማኖት አስፋ ፊዎችና ሰማዕታት ተገኝተዋል ።

አዎን የወንጌልን ዘር በሚስጢር ይዘራሉ ፤ ዳሩ ፍሬው በሕዝብ ፊት ይታጨዳል ። ክርስቲያኖች ከተባ በሩ የቀድሞዎቹ እንደነበሩትም ትጉ ሠራተኞች ከሆነ ፅኑ የሆነ የክርስቶስ ፍቅር ካስተሳሰራቸው መላውን ዓለም ወደ ወንጌሉ ምሥራች ሊያመጣቸው የመምህ ራቸውም ደቀ መዛሙርት ሊያደርጉዋቸው ይችላሉ ።

ወንድሞቻችው ወህኒ ቢገቡም ምን ያህል ፅናት እንደነበራቸው ማስረጃ እንዲሆን ቀጥሎ ባሉት ገጾች ከአንዲት ቫሪያ የተባለችውን ልጃገረድ ወደ ክርስቶስ ከመራች ማሪያ ከምትባል ልጃገረድ የተላኩትን ደብ ዳቤዎች እንመልከት ። ምንም እንኳ እነዚህ ደብዳቤ ዎች የተላኩት ከሩሲያ ቢሆንም የመጨረሻው ግን የተላከው ከኮሚኒስት እስር ቤት ነው ማለት ቫሪያ በማሪያ ምስክርነት ጌታን ከተቀበለች በኋላ በኮሚኒ ስቶች ጉባዔ ጌታን በግልጽ በመስበክዋ ምክንያት ወኅኒ ገብታ የላከችው ደብዳቤ ነው ።

## ፩ኛ ደብዳቤ

ያለሁት በሩሲያ ነው ፤ ባለሁበት አካባቢ በተለ ይም በወጣቶች ኮሚኒስት ፓርቲ አባሎች ዘንድ አድ ናቆትን አግኝቼአለሁ ። ምንም እንኳ ብዙዎች ቢሰድቡ ኝና በሌላም መንገድ ቢጐዱኝም እኔ ግን ለሁሉም የጌታን ፍቅር አንጸባርቃለሁ ። በዚህም ምክንያት ቀድሞ ትጠላኝ ፤ ትሰድበኝና ትቃወመኝ የነበረች አንዲት ቮሪያ የምትባል ልጃገረድ ወደኔ ቀርባ «ምን ዓይነት

ሰው ብትሆኚ ነው ሁልጊዜ ለሚጠሉሽና ለሚሰድ ቡሽ ፍቅርን የምታሳይው» አለችኝ ። እኔም መምህራ ችንና አዳኛችን የሆነው ክርስቶስ ለሚወደኝ ብቻ ሳይ ሆን ለሚጠሉኝም ፍቅርን እንድናሳይ አዞናል ።

ምንም እንኳ ይህች ልጅ ከሚቋወሙኝና ከሚያ ንጓጥጡኝ ወገን ብትሆንም ሁሉን የሚችል አምላክ ለሰው ልጆች መዳኛ ያዘጋጀው መንገድ ግልጽ ይሆ ንላት ዘንድ ስለርሷ ብዙ ሰዓቶችን በጸሎት አሳል ፋለሁ ።

እንዲያውም አንድ ቀን አፍ አውጥታ «ሁሉን ስትወጂ እኔንስ ትወጂኛለሽን? ብትለኝ ክንዶቼን በአንገቷዋ ዙሪያ አድርጌ እያለቀስኩ እንደምወዳት ገለጽኩላት ። ዛሬ አብረን እንጸልያለን አሁንም የማ ሳስብሽ ይህችን እህት በጸሎትሽ እንድታስቢያት ነው ።

ውድ እህቴ ሆይ ምንም እንኳ አንዳንዶች ከፍ ባለ ድምፅ የእግዚአብሔርን ያለመኖር ቢያውጁም አታድንቂ ። ልባቸው መመኪያ የሚሆናቸውን አምላክ ለመሻት በታላቅ መቃተት ትጨነቃለች እነዚህ ሰዎች የውስጣዊ ልባቸውን መሻት ተቃራኒ የሆነ ነገርን በመናገር ሊሸፍኑት ይሞክራሉ ። በእግዚአብሔር ላይ አጸያፊ ስድብን ቢሰነዝሩም በልባቸው ውስጥ ፍርሃት ነግሦአል ።

በክርስቶስ እህትሽ የምትሆን

ማሪያ

## ፲፪ኛ ደብዳቤ

በመጀመሪያው ደብዳቤዬ ስለአንዲት የወጣቶች ኮሚኒስት ፓርቲ አባል የሆነች ልጃገረድ ጽፌልሽ እንደነበር ታስታውሻለሽ ። አሁን ግን ታላቅ ስለሆነ ደስታዬ ስጽፍልሽ በድጋሚ በጣም ደስ እያለኝ ነው። ቫሪያ ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኟ ተቀበለች ደስ ይበልሽ ።

እርሷ ያገኘችውን ደስታ ተካፋዮች እንዲሆኑ ለብ ዙዎች የቀድሞ ጓደኞቿ ስለጌታ አዳኝነት በመመስ ከር ላይ ናት ።

ይህቺ ልጅ ቀድሞ ማለት ጌታን ከመቀበልዋም በፊት እግዚአብሔር እንደሌለ የምታምን በመሆንዋ ብዙዎችን ተከራክራ አስክዳቸዋለች ዛሬ ግን ለቀድሞ ጥፋቷ ካሣ ይሆን ዘንድ ስለክርስቶስ ወንጌል አዳኝ ነት ሕይወቷን ለመስጠት እንኳ ፈቃደኛ እንደሆነች ገልጻልኛለች ።

አንድ ቀን እኔና ቫሪያ እግዚአብሔር የለም ወደ ሚሉ ወጣት ኮሚኒስቶች ስብሰባ ሄደን ሳለ እንደተ ለመደው ጥቂት የኮሚኒስት መዝሙሮች ከተዘመሩ በኋላ ቫሪያ ለመናገር ፍቃድ እንዲሰጣት ጠየቀችና ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኟ እደተቀበለች ከመግ ለጽዋም ሌላ ቀድሞ የነበረችበት ሕይወት የእውር ነት ስለነበር ብዙዎችን ወደ ጥፋት መምራቷን ገልፃ አሁን ግን መንፈሳዊ አይኖቿ ስለተገለጡ መንገዷን መቀየሯን በድፍረት አስታወቀች ።

ቫሪያ ያሰማችው የራሷን ምስክርነት ብቻ ሳይ ሆን በጉባዔው ውስጥ የነበሩትንም እሷ የተቀበለች ውን አዳኝ እንዲቀበሉ ጋበዘች ።

ንግግሯን ለማዳመጥ ታላቅ ጸጥታ ነበር ፤ ማንም ሊያቋርጣት አልደፈረም። ከዚህ በኋላ ውብ በሆነ ድምጿ ብዙዎችን ክርስቲያናዊ መዝሙሮችና «ለብዙዎች ኃጢአት ስለሞተው ክርስቶስና ስለመስቀሉ ኃይል ለመናገር አላፍርም» የሚለውን ተወዳጅ መዝሙር አሰማች ።

ከዚህ በኋላ ግን ቫሪያን ወሰዱአት ወዴት እን ደሆነ ግን የሚያውቅ የለም ። ነገር ግን በሚያጽናና መንፈሱ እንደሚደግፋት አውቃለሁ ጌታ ኃይሉን እን ዲያበዛላት በጸሎትሽ አስቢያት ።

ያንቺው ማሪያ

## ፫ኛ ደብዳቤ

ትናንት ማለት ጳጉሜ ፪ ቀን ተወዳጅ እህታችን ቫሪያንን ለማናገር እድል አግኝቼ ነበር ። ስለርሷ ሳስብ ልቤ በታላቅ ኃዘን ይወጋል ፤ እርግጥ በዕድሜዋ በጣም ልጅ ናት ፤ ከ፲፱ ዓመት አይበልጣትም ፤ በጌታም ማመን ከጀመረች ጥቂት ጊዜያት ቢያልፋትም መንፈሳዊ ሕፃን መሆንዋ አይካድም ፤ ቢሆንም በዚያ የጭንቅ ኑሮዋ ጌታን እንዴት አድርጋ እንደምትወድ ለመግ ለጽ ቃላት ያጥረኛል ። ከኛ ከተወሰደች ከጥቂት ጊዜ ያት በኋላ እስር ቤት መሆንዋን ስንሰማ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አዋጥተን ላክንላት ። ቢሆንም ከላክ ንላት ውስጥ የሚደርሳት አነስተኛው ክፍል ነው ። ከተ ለያየን ጀምሮ ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ አየኋት ፤ በጣም ከስታለች ፤ ጠቊራለች ፤ ገርጥታለች ፤ ቢሆንም አይኖቿ ዓለም ሊሰጥ በማይችለው አምላካዊ ደስታ ያበራሉ ።

በውስጥም ያለው የአምላካችን ሰላም በግንባሯዋና ገፅዋ በጉልህ ይነበባል ።

እምን ውድ እህቴ ሆይ ታላቁ አምላክ በርሱ ለሚያምኑ በችግርና በመከራ መፅናኛ ይሆናቸው ዘንድ የሚሰማቸውን ሰላም ላልቀመሰት ለማስረዳት ምንኛ ያስቸግራል? ሰብዓዊ አእምሮ ከሚገምተው በላይ ጥልቅ ነው ።

ይህንንስ በጌታ የሚገኘውን ደስታ የተለማመዱ ምንኛ ብፁዓን ናቸው ። እኛ በክርስቶስ ያለነውን ሁሉ አዳኝነቱንና ሁሉን ስለሚይዝ ፍቅሩ ከመናገር ምን ያግደናል? መከራ? ችግር? እስራት? ግርፋት? አንድም ስንኳ አይችልም!

ቫሪያን ለማናገር ሄጄ ሳለሁ በመካከላችን በነበረው የብረት አጥር «ለመሆኑ እስካሁን በደረሰብሽ መከራና በተያዝሽበትም ቀን በኮሚኒስቶች ጉባዔ ስላሰማሽው ምስክርነት ተጸጸተሻልን? ብላት እንዲያውም አሁን ከዚህ ወህኒ እንድወጣ ብደረግም እንኳ ታላቅ ስለሆነው የክርስቶስ ፍቅር መናገሬን አላቆምም ።

ውጫዊ አካሌን በማየት ብቻ እንደተጐዳሁ አይምሰልሽ የጌታ ፍቅር ያፅናናኛል ። በመንፈሱም ያበረታኛል አለችኝ ። ዛሬም ላሳስብሽ የምፈልገው ስለ ዚህች እህታችን በርትተሽ እንድትጸልይ ነው ።

ምናልባት በቅርቡ ይበልጥ ፍዳ ወዳለበት ወደ ሳይቤሪያ ሳትወሰድ አትቀርም ። ማንም የሚጠይቃት ዘመድና ወገን ስለሌላት ያለናት እኛ በጌታ እህቶቿ የምንሆን ብቻ ስለሆንን የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ አዋጥተን መላኩ ፋንታችን ይሆናል ፤ ታላቅ አምላክ

በችግሯና በመከራዋ ሁሉ በቀኝዋ ቆሞ ያበረታታል እባክሽ ጸልይላት ።

ያንቺው ማሪያ

«እነዚህ ሁለት ደብዳቤዎች ማለት አራተኛውና አምስተኛው ቫሪያ በማርያ ምስክርነት ጌታን ከተቀበለች በኋላ በኮሚኒስቶች ጉባዔ ባሰማችው ስብከት ምክንያት ወህኒ ከወረደች በኋላ የላከቻቸው ናቸው ። እነዚህን ደብዳቤዎች ከላከች በኋላ ስለቫሪያ የተሰማ ምንም የለም»

## ፬ኛ ደብዳቤ

እህቴ ማሪያ ሆይ...ከብዙ ጉዞ በኋላ ወደተዘጋጀልን ካምፕ በደህና ደርሰናል ፤ ያለንበት ቦታ በግምት አሥር ማይሎችን ያህል ከከተማው ወጣ ያለ ነው ።

እኔና አንዲት በጌታ እህቴ የምትሆን ሴት በየቀኑ የተመደበልንን ከባድ ሥራ እንሠራለን ፤ ቢሆንም የዚያች እህቴ ጤንነት በሥራው ከባድነት ስለተጐዳ እስከአሁን የርሷንም የኔንም ሥራ አጠናቅቄ ለአለቆቼ የማቀርብ እኔው ብቻ ነኝ ። በቀን ውስጥ ከ፲፪—፲፫ ሰዓቶችን ያህል በከባድ ሥራ እሰቃያለሁ ።

አምላኬንና ጌታዬን በአንቺ በኩል የመዳኛውን መንገድ ስለገለጽሽልኝ በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ ። ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕይወቴን በዓላማ እመራለሁ ፤ ብሞትም እንኳ ወዴት እንደምሄድ ስለማውቅ አልጨነቅም ።

ለማን እንደምሰቃይ ሳስብ ወሰን የሌለው ደስታ በልቤ ይነግሣል ። ስላለኝ ደስታና ወደር ስለሌለው የአ ምላካችን ፍቅር አብዝቶ መናገር ደስ ይለኛል ። በክ ርስቶስ ካለን የእግዚአብሔር ፍቅር ማን ይለየናል? ስለክርስቶስ ፍቅር የምንቀበላቸው መከራዎች ሁሉ በአምላካችን ላይ ያለንን እምነት ብማጽናት በቀር ሌላ ምንም ሊያደርጉን አይችሉም ።

ስለክርስቶስ ከመመስከር የተቆጠብኩ ባለመ ሆኔ ከተመደበልኝ ሌላ ብዙ ሥራ በመጨመር ጸጥ ሊያሰኙኝ ይሞክራሉ ።

ጸጥ አልልም! አንድ ቀን የጥፋት ልጅ የነበር ኩትን እኔን ስለስሙ አዲስ ፍጥረት ስላደረገኝ ስለክብሩ የመሰቃየትም እድል ስለሰጠኝ ስለአምላኬ ኃይል ከመናገር ጸጥ አልልም!

የሕይወት እስትንፋስ እስካለኝ ድረስ አንደበቴ አምላኬን ከማመስገን አይቆጠብም ፤ ጸጥ አልልም ።

ወደተመደበልኝ ካምፕ ለመሄድ መንገድ ላይ ሳለን በክርስቶስ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ከሚ ሆኑ ብዙ ክርስቲያኖች እስረኞች ተገናኝተን በመን ፈስ ወንድሞቼ መሆናቸውን ሳስብ ምንኛ ደስ ያለኝ ይመስልሻል! በመንገድ ላይ ሳለን ከአንዲት ሴት ጋር ተገናኘንና ምግብ ሰጠችኝ ፤ የሚያስደንቀኝ ነገር ቢኖር ከዚህች ሴት ጋር ስንገናኝና ስንለያይ የተናገረቻቸው ሁለት ቃላት ናቸው ። እነሱም «እግዚአብሔር ሕያው ነው» የሚሉ ነበሩ ። አዎን የክርስቲያኖች አምላክ ዛሬም ቢሆን ሕያው ነው ። አልሞተም ፤ ሕዝቡንም አል ረሳቸውም ፤ ከቶም አልጠላቸውም ፤ ስሙ ይከበር ፤ ከብዙ ጉዞ በኋላ ወደተመደበልን ካምፕ ደረስን ፤ በዚያ ስለ

እምነታቸው ሲሰቃዩ ከነበሩት የእግዚአብሔር ልጆች ጋር ተቀላቀልን «የደረስነው በምሽት ነበር»

የእስረኞች መታጐሪያ ወደሆነው ቤት ስንገባ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን «ሰላም ለናንተ ይሁን» አልናቸው ፤ እነሱም «መልሰው «ሰላም ለናንተ ይሀን» በማለት ለሰላምታችን አጸፋውን መለሱልን ።

ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሆን ምንኛ ደስ ይላል ። ደስታችን ልክ በዘመዶቹ መሃል እንዳለ ልጅ ነበር ።

ከእስረኞቹ ከግማሽ በላይ ጌታን እንደግል አዳ ኛቸው የተቀበሉ ክርስቲያኖች ናቸው ። ታላላቅ ሰባ ኪያንና ዘማሪያንም አብረውን ናቸው ። በየምሽቱ በታ ላቁ አምላካችን ዙፋን ዙሪያ ተሰብስበን እንጸልያለን ፤ ዛሬ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ልሔም የተ ወለደው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በልቤ ተወለደ ።

በእግዚአብሔር ቃል የበሰሉ ወንድሞች እንደ ጌታ ትእዛዝ መሠረት እኔና ሌሎች ሰባት ሰዎችን አጠመቁን ።

ማሪያ ሆይ ምነው አጠገቤ በሆንሽና ቀድሞ ስለ በደልኩሽ ይቅርታን በጠየቅሁሽ እህቴ ሆይ ለምታው ቂያቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ሰላም በይልኝ በተረፈ ከእብራውያን መጽሐፍ ከምዕራፍ ፲፪ ። ከ፩—፫ ያሉ ትን አንብቢ «ኪትቻለም በቃልሽ አጥኚአቸው»

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ሰላም ይሉሻልና በሰማቸው ይድረስሽ

አሜን
ያንቺው ቫሪያ

## ፩ኛ ደብዳቤ

እህቴ ማሪያ ዛሬ ደግሞ እንደገና እንድጽፍልሽ እድል በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል ።

በእግዚአብሔር ፀጋ እኔና መታመሟን ገልጬልሽ የነበረችው እህቴ በመልካም ጤንነት ላይ መሆናችንን ስገልጽልሽ ደስ እንደሚልሽ በማመን ነው ።

የላክሽልን መልካም ስጦታ ሁሉ ደርሶናል ፤ እግዚአብሔር ይስጥልን ። በተለይም ስለላክሽልኝ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሜ ላመሰግንሽ እወዳለሁ ።

ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር መለማመድ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ በዚህች ዓለም ላይ የኔን ያህል ደስታ ያለው ሰው ያለ አይመስለኝም ።

በሚደርስብኝ መከራ ሁሉ ለጌታ ታማኝ አገልጋይ ሆኜ እቆም ዘንድ ኃይሉን እንዲሰጠኝ ጸልይልኝ ፤ በተረፈ በአቅራቢያሽ ያሉትን ክርስቲያኖች ሰላም በይልኝ ።

ያንቺው ቫሪያ